# አማርኛ

## እንደአፍ መፍቻ ቋንቋ

### የተማሪ መጽሐፍ

## 7ኛ ክፍል


**አዘጋጆች**

ትጃኒ ምትኩ

መላኩ ጽጌ

**አርታኢ**

ግሩም ጥበቡ

**የጥራት ተቆጣጣሪዎች**

ይልፋሸዋ ጥላሁን

በርናባስ ደበሎ

ታምሩ ገለታ

**ግራፊክስ እና ምስል ገለፃ**

ሰለሞን አለማየሁ ጉተማ

© የኦሮሚያ ክልል ትምህርት ቢሮ 2014 ዓ.ም.

ይህ መፅሐፍ በ2014 ዓ.ም. በኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ እና በነቀምቴ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ በትብብር የተዘጋጀ ነው። የመጽሐፉ ህጋዊ የቅጂ ባለቤት ©2014 ዓ.ም. የኦሮሚያ ክልል ትምህርት ቢሮ መብት በህግ የተጠበቀ ነው። የዚህን መጽሐፍ ክፍል በተለያዩ መሳሪያዎች ያለባለቤቱ የቅድሚያ ፈቃድ እንደገና ማሳተም፣ ማሰራጨት፣ ማከማቸትና መልሶ መጠቀም አይቻልም።
የቅጂ መብቶችን ለማክበር በተቻለን መጠን የሚፈለግብንን ጥረት ሁሉ አድርገናል። ሳናውቅ በስህተት ሳንጠቅሳቸው የተዘለሉ ካሉ በቅድሚያ ይቅርታ እየጠየቅን በሚቀጥሉት ህትመቶች አስፈላጊውን እውቅና እንደምንሰጥ ለመግለጽ እንወዳለን።

# ማዉጫ


ማውጫ ........ iii

መቅድም ........ iv

መግቢያ ........ v

ምእራፍ አንድ ተፈጥሮን ማድነቅ ........ 1

ምዕራፍ ሁለት የቤተሰብ ምጣኔ ........ 15

ምዕራፍ ሶስት የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ........ 27

ምእራፍ አራት የታዋቂ ግለሰቦች ህይወት ታሪክ ........ 40

ምዕራፍ አምስት ውሃና ጠቀሜታው ........ 57

ምእራፍ ስድስት የሰዎች ዝውውር ........ 68

ምዕራፍ ሰባት ማህበራዊ ግንኙነት ........ 81

ምእራፍ ስምንት ሱሰኝነት ........ 95

ምእራፍ ዘጠኝ አርበኝነት ........ 109

ምእራፍ አስር ቃላዊ ግጥም ........ 110

## መቅድም

ትምህርት ሚኒስቴር "ጥራቱ የተጠበቀና እኩል ተደራሽነት ያለው ትምህርት ለሁሉም ማዳረስ" በሚል ትኩረት ሰጥቶ አዲስ ሥርዓተትምህርት ቀርጾ አቅርቧል። በዚህም መሠረት ቀድሞ በነበረው ሥርዓተትምህርት ላይ ታይቶ የነበረውን ክፍተት ለመሙላት ምርምር ተደርጓል። ከምርምሩ የተገኙ አቅጣጫዎችም የተማሪዎቹን ደረጃ አለመመጠን፣ የትምህርቱ አንኳር ጽንሰሀሳቦች ግልጽ አለመሆን፣ ከይዘቱ መታጨቅ የተነሳ ለዓመቱ ከተመደበለት ክፍለጊዜ ጋር አለመመጣጠን እና ከተጓዳኝ ሥርዓተትምህርቶች አማራጭ ግብዓቶችን አለመጠቀም ናቸው። ስለሆነም ስርዓተትምህርቱ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ልህቀትን ለማሻሻል፣ በአውድ የተደገፈ ለማድረግ፣ እና በተግባራዊ መማር ላይ የተመሠረተ የመማር ስኬታማነትን ለማረጋገጥ ተቀርጿል።

ሥርዓተትምህርቱን መሠረት በማድረግም የትምህርት መሣሪያዎች ተዘጋጅተዋል። ከእነዚህም ውስጥ የተማሪው መማሪያ መጽሐፍ አንዱ በመሆኑ ይህ አማርኛን እንደአፍመፍቻ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ በኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ ሊዘጋጅ ችሏል። መጽሐፉም ተማሪዎች ቢያንስ መጎናጸፍ ያለባቸውን ብቃት (Minimum Learning Competency)፣ የሚጠበቁ የመማር ውጤቶች፣ እንዲሁም ተግባቦታዊ የመማር ዘዴን መሠረት አድርጎ የተዘጋጀ ነው። ከዚህ አንፃር መጽሐፉ በቀድሞው የተማሪ መማሪያ መጽሐፍ የተስተዋሉ ክፍተቶችን ይሞላል ተብሎ ይጠበቃል።

## መግቢያ

ይህ መማሪያ መጽሐፍ አስር ምዕራፎች አሉት። እያንዳንዱ ምዕራፍ ደግሞ በሥሩ ስድስት ንዑሳን ትምህርቶችን አካቷል። እነዚህም ትምህርት አንድ ማዳመጥ፣ ትምህርት ሁለት መናገር፣ ትምህርት ሶስት ማንበብ፣ ትምህርት አራት መጻፍ፣ ትምህርት አምስት ቃላት እና ትምህርት ስድስት ሰዋስው ናቸው። እያንዳንዱ ትምህርት በመርሃ-ትምህርቱ በተደለደለው መሠረት በክፍለጊዜ ተከፋፍሎ የቀረበ ሲሆን በሥሩ መመሪያዎችን፣ ትዕዛዛትን፣ መልመጃዎችን እና ተግባራትን አካቷል። ከዚህ አኳያ የቋንቋ ክሂሎች የተደራጁት በቅድመ ተግባር፣ በጊዜ ተግባር እና በድህረ ተግባር ሂደታዊ አቀራረብ ነው። የቋንቋ የዕውቀት ዘርፎች ደግሞ ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ እና ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር አቀራረብ ዘዴን ተከትለዋል። ከዚህ አንጻር የመማሪያ መጽሐፉ ማስተማሪያ ዘዴ ተማሪ ተኮር እንዲሆን ተደርጓል።

# ምእራፍ አንድ

# ተፈጥሮን ማድነቅ

## የሚጠበቁ ውጤቶች

**ከዚህ ምእራፍ ትምህርት በኋላ፡**

- ምንባቡን በማዳመጥ የተገነዘባችሁትን ቁም ነገር ትናገራላችሁ፡፡
- የተፈጥሮን ምንነት ትገልጻላችሁ፡፡
- የተለያዩ የተፈጥሮ ገጽታዎችን ታደንቃላችሁ፡፡
- ቋንቋን በተለመዱ ሁኔታዎች ትጠቀማላችሁ፡፡
- የተለመዱ አገላለጾችን በመጠቀም አንቀጽ ትጽፋላችሁ፡፡
- የአፍ መፍቻ ቋንቋ መሰረታዊ መዋቅሮችን ትገልጻላችሁ፡፡

**ክፍለጊዜ አንድ**

## ትምህርት አንድ ፡ ማዳመጥ

**በዚህ የትምህርት ይዘት የማዳመጥ ክሂላችሁን ለማዳበር የሚረዱ መልመጃዎችና ተግባራት ቀርበዋል፡፡ ስለሆነም በትኩረት በማዳመጥ መልመጃዎቹንና ተግባራቱን በተገቢው መንገድ ስሩ፡፡**

## የወንጪ ሀይቅ



## የቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች

**መምህራችሁ የሚያነቡላችሁን ጽሁፍ ከማዳመጣችሁ በፊት ለቀረቡት ጥያቄዎች በቃል መልስ ስጡ፡፡**

1. ከላይ ስለቀረበው ስዕል የምታውቋቸውን መረጃዎች ለጓደኞቻችሁ አጋሩ፡፡
2. በኦሮሚያ ክልል የምታውቋቸውን ሀይቆች ስም ተናገሩ፡፡

## የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎች

**ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቄዎች እስካሁን ሲነበብ ባዳመጣችሁት መሰረት በቃል መልስ ስጡ፡፡**

1. የወንጪ ሀይቅ መገኛ ቦታ የት ነው?
2. የወንጪ ሀይቅ የተፈጠረው እንዴት ነው?
3. ወንጪ ሀይቅ የሚገኝበት ቦታ የአየር ንብረት ምን አይነት ነው?
4. ሀይቁ በውስጡ ስንት ደሴቶችን ይዟል?

## የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች

### መልመጃ አንድ

**ሀ. ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቄዎች ባዳመጣችሁት ጽሁፍ መሰረት መልሱን ለክፍል ጓደኞቻችሁ በቃል ተናገሩ፡፡**

1. በቀረበው ምንባብ መሰረት በወንጪ ሀይቅ አካባቢ የሚገኘው ምንጭ ምን ዓይነት ነው?
2. ከሀይቁ በተጨማሪ በአከባቢው የሚገኙ የተፈጥሮ ሀብቶች ምን ምን ናቸው?
3. የወንጪ ሀይቅን ማራኪ የሚያደርጉትን ገጽታዎች አብራሩ፡፡

4. "ወንጪ ሀይቅ በእሳተ ገሞራ የተፈጠረና ከባህር ጠለል በላይ በ3386 ሜትር ከፍታ ላይ በደንና በተራሮች ተከቦ ይገኛል፡፡" የዚህን ዓረፍተነገር ሀሳብ በራሳችሁ አገላለጽ አስረዱ፡፡
5. ጽሁፉ ሲነበብ ያገኛችሁትን መረጃ አሳጥራችሁ አቅርቡ፡፡

**ለ. ከዚህ በታች በቀረቡት ሀሳቦች ላይ በመመስረት ጽሁፍ ካዘጋጃችሁ በኋላ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አንብቡላቸው፡፡**

1. የሀይቆች እንክብካቤና የተጋረጠባቸው አደጋ
2. አገራችንን ወደፊት ከሀይቆች ተጠቃሚ ሊያደርጓት የሚችሉ ጉዳዮች

**ክፍለጊዜ ሁለት**

## ትምህርት ሁለት፡ መናገር

**ከዚህ በታች የቀረቡት ተግባራት የመናገር ክሂላችሁን ለማዳበር የሚረዱ ናቸው፡፡ ለተግባራቱ ተገቢ መልስ ስጡ፡፡**

### ተግባር አንድ

**ሀ. ከዚህ በታች ለውይይት መነሻ የሚሆኑ ሀሳቦች ቀርበዋል፡፡ ስለዚህ የቀረቡትን ሀሳቦች መሰረት በማድረግ በቡድን ከተወያያችሁ በኋላ ዘገባውን ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ፡፡**

1. ሀይቆች መጠናቸው እንዳይቀንስ፣ ሙሉ በሙሉ እንዳይደርቁና መስህብነታቸው እንዲጨምር ምን መደረግ እንዳለበት ተወያዩ፡፡
2. ከሀይቆች የሚገኝ ገቢ እንዲጨምር ምን መሰራት እንዳለበት ተወያዩ፡፡

### ተግባር ሁለት

**ሀ. ከዚህ በታች የቀረቡትን ተግባራት በተጠየቀው መሰረት ስሩ፡፡**

1. በአካባቢያችሁ የሚገኙ ማራኪ ቦታዎችን ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ፡፡
2. ቦታዎቹ ማራኪ እንዲሆኑ ያደረጓቸውን ምክንያቶች አስረዱ፡፡
3. ማራኪ ስፍራዎችን የመጎብኘት ልምድ ለማዳበር የሚረዱ ሀሳቦችን ተናገሩ፡፡

**ክፍለጊዜ ሶስት**

## ትምህርት ሶስት፡ ማንበብ

**ከዚህ በታች የቀረበው ምንባብ እና መልመጃዎች የማንበብ ክሂላችሁን ለማዳበር የሚያግዙ ናቸው፡፡ በመሆኑም ምንባቡን በትኩረት በማንበብ የቀረቡትን መልመጃዎች ስሩ፡፡**

### ቅድመማንበብ ጥያቄዎች



የባሌ ተራራዎች ብሄራዊ ፓርክ

1. ብሄራዊ ፓርክ ማለት ምን ማለት ነው?
2. በአገራችን ከሚገኙ ፓርኮች የምታውቋቸውን ለመምህራችሁ ተናገሩ፡፡
3. በአንድ ፓርክ ውስጥ ምን ምን ነገሮች የሚገኙ ይመስላችኋል?

## የባሌ ተራራዎች ብሄራዊ ፓርክ

በኢትዮጵያ ከሚገኙ አንጋፋ ፓርኮች መካከል የባሌ ተራራዎች ብሄራዊ ፓርክ አንዱ ነው፡፡ ፓርኩ በኦሮሚያ ክልል በባሌ ዞን ውስጥ ይገኛል፡፡ የባሌ ተራራዎች ብሄራዊ ፓርክ 2220 ካሬ ኪሎ ሜትር ስፋት ያለው ሲሆን በፓርክነት የተከለለው እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር በ1970 ነው፡፡

የባሌ ብሄራዊ ፓርክ የአየርንብረት ቀዝቃዛ ነው፡፡ፓርኩ ከባህር ወለል በላይ ከ1442 እስከ 4377 ሜትር ከፍታ አለው፡፡ የባሌ ተራራዎች ብሄራዊ ፓርክ ከፍተኛው የሙቀት መጠን ከ10 እስከ 20 ዲግሪ ሰልሺየስ ይደርሳል፡፡ ዓመታዊ የዝናብ መጠኑም 650 እስከ 1300 ሚሊ ሜትር እንደሆነ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡

የባሌ ተራራዎች ብሄራዊ ፓርክ አስገራሚ መልክዓምድራዊ ገጽታዎች አሉት፡፡ የተደላደሉ ኮረብታዎች ይበዙበታል፡፡ ኮረብታዎቹ ግዙፍና እንደሰንሰለት ተያይዘው ከሰማይ ጋር የተጋጠሙ ይመስላሉ፡፡ በተለያዩ ቁሳቁስ አምሳል ተጠፍጥፈው የተሰሩ የሚመስሉ ውብና አስገራሚ መስህብ ያላቸው የመሬት ገጽታዎችና ጭልጥ ያሉ ገደላገደሎች የባሌ ብሄራዊ ፓርክ ዋነኞቹ መለያዎች ናቸው፡፡

### የንባብ ጊዜ ጥያቄዎች

1. የባሌ ብሄራዊ ፓርክ መገኛ ቦታ የት ነው?

2. የባሌ ተራራዎች ብሄራዊ ፓርክ ምን አስገራሚ ነገሮች አሉት?
3. ቀጣዩ የምንባቡ ክፍል ስለምን የሚናገር ይመስላችኋል?

የባሌ ተራራዎች ብሄራዊ ፓርክ ልዩ የተፈጥሮ ትዕይንት የሚታይበት ስፍራ ነው፡፡ በፓርኩ ውስጥ በኢትዮጵያ ብቻ የሚገኙ እንስሳት አሉ፡፡ 20 የሚደርሱ አጥቢዎች በዚሁ ፓርክ ብቻ የሚገኙ ናቸው፡፡ በፓርኩ ውስጥ ከሚገኙት እንስሳት ውስጥ ኒያላ፣ ቀይ ቀበሮና ከርከሮ ተጠቃሽ ናቸው፡፡ በተጨማሪም ከ160 የሚበልጡ የአእዋፍ ዝርያዎች ይገኛሉ፡፡

በአጠቃላይ የባሌ ተራራዎች ብሄራዊ ፓርክ በአስገራሚ መልክዓ ምድራዊ ገጽታዎችና በእንስሳት ስብስብ ይታወቃል፡፡ በዚህም የተነሳ ፓርኩ በበርካታ የውጭና የሀገር ውስጥ ቱሪስቶች ስለሚጎበኝ ለሀገሪቱ ከፍተኛ ገቢ በማስገኘት ላይ ይገኛል፡፡

*(የኢ.ፊ.ድ.ሪ ትምህርት ሚኒስቴርና የኦሮሚያ ትምርት ቢሮ፡፡2007፡፡ ለአማርኛ ቋንቋ ማስተማሪያ የተዘጋጀ መጽሀፍ ተሻሽሎ የቀረበ)*

**ክፍለጊዜ አራት**

## የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች

**መልመጃ ሁለት**

**ሀ. ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች ምንባቡን መሰረት በማድረግ ተክክል ከሆነ "እውነት" ካልሆነ ግን "ሀሰት" በማለት መልሱ፡፡**

1. የባሌ ተራራዎች ብሄራዊ ፓርክ ከሚታወቅባቸው አንዱ ሞቃታማነቱ ነው፡፡
2. "...ኮረብታዎች ግዙፍና እንደሰንሰለት የተያያዙ ናቸው፡፡" ሲል የተራራዎቹን ትልቅነትና የተያያዙ መሆናቸውን መግለጹ ነው፡፡

3. የባሌ ተራራዎች ብሄራዊ ፓርክ ከፍተኛ ገቢ ከሚያስገኙ የሀገራችን ተፈጥሯዊ ሀብቶች አንዱ ነው፡፡
4. በአራተኛው አንቀጽ “በተጨማሪም…” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ከአእዋፍ ሌላ የተዘረዘሩ ሌሎች እንስሳት ቀደም ብለው መዘርዘራቸውን ነው፡፡
5. በመጨረሻው አንቀጽ “በዚህም የተነሳ…” የሚለው ሀረግ በአገባቡ የሰጠው አገልግሎት ምክንያትን ማመልከት ነው፡፡

**ለ. ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ቃላት ከምንባቡ የወጡ ናቸው፡፡ በ ‘ሀ’ ስር ለቀረቡት ቃላት በ ‘ለ’ ስር ከተሰጡት ተመሳሳያቸውን አዛምዱ፡፡**

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. አንጋፋ | ሀ. ወፎች |
| 2. ግዙፍ | ለ. እይታ |
| 3. ትእይንት | ሐ. የመሬት አቀማመጥ |
| 4. አእዋፍ | መ. የዝናብና የሙቀት ሁኔታ |
| 5. ብሄራዊ | ሠ. ተዘጋጅተው |
| 6. መልክዓምድር | ረ. አገር አቀፍ |
| 7. የአየር ንብረት | ሰ. መስህብ |
| 8. ገጽታ | ሸ. ቀዳሚ |
| 9. ማራኪ | ቀ. መልክ |
| | በ. ትልቅ |

**ሐ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ከላይ የቀረበውን ምንባብ መሰረት በማድረግ በጽሁፍ መልስ ስጡ፡፡**

1. በአገራችን ፓርኮች ውስጥ የሚኖሩ የዱር እንስሳት ወደጎረቤት ሀገር ይሸሻሉ ይባላል፡፡ይህ ለምን የሚሆን ይመስላችኋል?

2. አንድ ሀገር ከፓርኮች ልታገኛቸው የምትችላቸውን ጥቅሞች ዘርዝሩ፡፡
3. በአቅራቢያችሁ በብሄራዊ ፓርክ ስር የተጠቃለለ የተፈጥሮ ሀብት ካለ ያለበትን ሁኔታ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አብራሩ፡፡

**ክፍለጊዜ አምስት**

## ትምህርት አራት፡ መጻፍ

**ከዚህ በታች የቀረበው ማስታወሻ እና ተግባራት የመጻፍ ክሂላችሁን ለማዳበር የሚረዱ ናቸው፡፡ስለዚህ ለጥያቄዎቹ ትኩረት ሰጥታችሁ ተገቢውን መልስ ጻፉ፡፡**

### ተግባር ሶስት

ከዚህ በታች የቀረበውን ማስታወሻ ከማንበባችሁ በፊት ስለ አንቀጽ የምታውቁትን ከቡድን አባላት ጋር ተወያይታችሁ የደረሳችሁበትን ሀሳብ ለመምህራችሁ በጽሁፍ አቅርቡ፡፡

### ማስታወሻ

#### አንቀጽ መጻፍ

አንድን ሀሳብ ከሚያብራሩ፣ ከሚተርኩ ወይም ከሚገልጹ ወዘተ አረፍተነገሮች የተገነባ፣ የራሱ የሆነ አንድነትና ጥምረት ያለው የድርሰት አነስተኛ ክፍል አንቀጽ ይባላል፡፡ በአንቀጽ ውስጥ ያለውን ሀሳብ አጠቃሎ የያዘ፣በእሱ ዙሪያ የሚያጠነጥኑ ሌሎች ዝርዝር አረፍተነገሮችን ያሰለፈ ዓረፍተነገር ሃይለቃል ተብሎ ይጠራል፡፡ ሀይለቃል በአንቀጹ ውስጥ በአንቀጹ መጀመሪያ፣ መሀከል፣መጨረሻ፣ እንዲሁም መጀመሪያና መጨረሻ ሊገኝ ይችላል፡፡

ምሳሌ፡

**ፍቅር በሁለት ደረጃዎች የተከፈለ ነው፡፡ ከፍቅር ሁለት ደረጃዎች የመጀመሪያው ጥልቀት የሌለውና ወረታዊ ሲሆን ሁለተኛው ግን ስር ሰደድ የማይለወጥና ዘላቂነት ወይም ህያውነት ያለው ነው፡፡**

ከላይ የቀረበውን አንቀጽ ስንመለከት ደምቆ የተጻፈው ዓረፍተ ነገር የአንቀጹ ሀይለቃል ሲሆን ሌሎቹ ዝርዝር ዓረፍተ ነገሮች ናቸው፡፡

**ክፍለጊዜ ስድስት**

**መልመጃ ሶስት**

**ከዚህ በታች የቀረቡት ዓረፍተነገሮች ቅደም ተከተላቸው የተዘበራረቀ ነው፡፡ በመሆኑም የዓረፍተ ነገሮቹን ቅደም ተከተል ከአስተካከላችሁ በኋላ ፍሰቱን በጠበቀ ሁኔታ በአንድ አንቀጽ አደራጅታችሁ ጻፉ፡፡**

1. ከዚያም እጇንና ፊቷን በሳሙና ትታጠባለች
2. በጥዋት ተነስታ መጸዳጃ ቤት ትሄዳለች፡፡
3. ፋጡማ ሁልጊዜ ሳይረፍድባት መማሪያ ክፍሏ ትገኛለች፡፡
4. ቁርሷን በልታ፣ ጓደኛዋን ጠርታ ወደትምህርት ቤት ትሄዳለች፡፡

**ተግባር አራት**

በአከባቢያችሁ የሚገኝ ተፈጥሯዊ መስህብ ጎብኙ፡፡ በጉብኝቱም ወቅት ስላያችሁት ነገር በአስተዋጽኦ መልክ የጉዞ ማስታወሻ ያዙ፡፡ በመጨረሻም በጥንድ በመቀጋገዝ አስተዋጽኦውን በአንቀጽ አደራጅታችሁ በመጻፍ ለክፍል ጓደኞቻችሁ በንባብ አቅርቡ፡፡

ክፍለጊዜ ሰባት

## ትምህርት አምስት፡ ቃላት

ከዚህ በታች የቀረበው ማስታወሻና ተግባራት የቃላት እውቀታችሁን ለማጎልበት የሚያግዙ ስለሆኑ ለጥያቄዎቹ ትኩረት በመስጠት ተገቢውን መልስ ስጡ፡፡

### ተግባር አምስት

የተዘውታሪ ቃላት ምንነት ለመምህራችሁ ተናገሩ፡፡

### ማስታወሻ

**ቃል፡** ቃል ትርጉም የሚሰጥ ነገሮችን፣ ጽንሰ ሀሳቦችን እና ስሜቶችን የሚወክል ነው፡፡ ምሳሌ፡-

1. ነገሮችን የሚወክሉ ፡ ቤት፣ መኪና፣ ወንበር
2. ጽንሰሀሳቦችን የሚወክሉ፡ መጻፍ፣ ማንበብ፣ መወዳደር
3. ስሜቶችን የሚወክሉ፡ ደስታ፣ ፍቅር፣ ሀዘን

**ተዘውታሪ ቃላት**፡- ተዘውታሪ ቃላት የምንላቸው በዕለት ተዕለት ህይወታችን የምንጠቀምባቸው ቃላት ናቸው፡፡ምሳሌ፡- ቤት፣ ውሃ፣ እናት፣በላ፣ ፈለጠ፣ አጠበ… ወዘተ

## መልመጃ አራት

ሀ. ከዚህ በታች በቀረበው የቢጋር ሰንጠረዥ ውስጥ የተሰጣችሁን ምሳሌ መሰረት በማድረግ በተዘውታሪ ቃላት አሟሉ፡፡

| ነገሮችን የሚወክሉ ቃላት | ስሜትን የሚወክሉ ቃላት | ጽንሰሀሳብ የሚወክሉ ቃላት |
|---|---|---|
| 1. ኳስ | ሀዘን | ደግ |
| 2. | | |
| 3. | | |
| 4. | ፍቅር | |
| 5. ደብተር | | |
| 6. | | ቸር |

ለ. በሚከተሉት ተዘውታሪ ቃላት አረፍተነገር መስርቱ፡፡

ሀ. ቸር

ለ. ደብተር

ሐ. ፍቅር

መ. ሀዘን

ሠ. ኳስ

ሐ. ለእርስ በእርስ ትውውቅ የሚያገለግሉ ተዘውታሪ ቃላትን ከለያችሁ በኋላ ቃላቱን ተጠቅማችሁ ጥንድ ጥንድ በመሆን የመተዋወቅ ተግባርን አከናውኑ፡፡ (ስም፣ ክፍል፣ እድሜ፣ የመኖሪያ ቦታ፣ የቤተሰብ ስም፣ የትምህርት ቤት ስም ወዘተ)

ምሳሌ፡ ስም ተማሪ 1. ስምህ ማን ይባላል?

ተማሪ 2. አለሙ እባላለሁ፡፡

ክፍለጊዜ ስምንት

## ትምህርት ስድስት፡ሰዋስው

**ከዚህ በታች የሰዋስው ችሎታችሁን ለማጎልበት የሚያግዙ ማስታወሻ እና ተግባራት ቀርበዋል፡፡በመሆኑም ለጥያቄዎቹ ተገቢውን መልስ ስጡ፡፡**

### ተግባር ስድስት

*የአፍ መፍቻ ቋንቋ መሰረታዊ መዋቅር ማለት ምን ማለት እንደሆነ በቡድን ሆናችሁ ተወያዩና ሀሳባችሁን ለመምህራችሁ ተናገሩ፡፡*

**ማስታወሻ**

***የአፍ መፍቻ ቋንቋ መሰረታዊ መዋቅሮች***

*የቋንቋ መሰረት የንግግር ድምጾች ናቸው፡፡ እነዚህም ተናባቢና አናባቢ ተብለው በሁለት ይከፈላሉ፡፡*

በአማርኛ ቋንቋ 26 ተናባቢ ድምጾች አሉ፡፡ለምሳሌ /ብ፣ ት፣ ድ፣ ጥ፣ ስ፣ ቅ፣ ጭ፣ / ይጠቀሳሉ፡፡ አናባቢዎች ደግሞ በቁጥር 7 ሲሆኑ እነሱም፡- /ኧ፣ ኡ፣ ኢ፣ ኣ፣ ኤ፣ እ፣ ኦ/ ናቸው፡፡

ከላይ የቀረቡት የቋንቋ መሰረት የሆኑት ድምጾች ተቀናጅተው ቃላትን ይመሰርታሉ፡፡እነዚህ ቃላትም በአማርኛ ቋንቋ በአምስት ይመደባሉ፡፡ እነሱም፡- ስም፣ ግስ፣ ቅጽል፣ መስተዋድድና ተውሳከ ግስ ናቸው፡፡

ቃላትም ተቀናጅተው ሀረጋትን ይመሰርታሉ፡፡እንደቃል ክፍሎች ሁሉ የአማርኛ ቋንቋ ሀረጋት አምስት ናቸው፡፡እነሱም፡- ስማዊ ሀረግ፣ ግሳዊ ሀረግ፣ ቅጽላዊ ሀረግ፣ መስተዋድዳዊ ሀረግና ተውሳከ ግሳዊ ሀረግ ናቸው፡፡

ሀረጋትም ተቀናጅተው ትልቁን የቋንቋውን መዋቅር ዓረፍተነገርን ይመሰርታሉ፡፡ በአማርኛ ቋንቋ  አይቀሬ የአረፍተነገር ተዋቃሪዎች የአረፍተ ነገሩ ባለቤት (ስም)ና ማሰሪያ አንቀጽ (ግስ) ሲሆኑ ሊቀር የሚችለው ተዋቃሪ ደግሞ ተሳቢ የሚባለው ነው፡፡

## መልመጃ አምስት

**ማስታወሻውን መሰረት በማድረግ ከዚህ በታች ለቀረቡ ጥያቄዎች ከተሰጡት አማራጮች ትክክለኛውን መልስ የያዘውን ፊደል ምረጡ፡፡**

1. ከሚከተሉት ድምጾች መካከል አናባቢ የሆነው የትኛው ነው?

   ሀ. /ድ/ ለ. /ኤ/ ሐ. /ክ/ መ. /ፍ/

2. ከዓረፍተነገር ተዋቃሪዎች መካከል ሊቀር የሚችለው______ነው፡፡

   ሀ. ባለቤት ለ. ማሰሪያ አንቀጽ ሐ. ተሳቢ መ.ግስ

3. የቋንቋ መነሻ መሰረቱ_____ነው፡፡

   ሀ. ዓረፍተነገር ለ. ሀረግ ሐ. ቃል መ. ድምጽ

4. ድምጾች ተቀናጅተው የሚመሰርቱት የትኛውን መዋቅር ነው?

   ሀ. ድምጽ ለ.ዓረፍተነገር ሐ. ሀረግ መ. ቃል

5. ትልቁ የቋንቋ መዋቅር የትኛው ነው?

   ሀ. ሀረግ ለ. ዓረፍተነገር ሐ. ድምጽ መ. ቃል

**ክፍለጊዜ ዘጠኝ**

## መልመጃ ስድስት

**ሀ. የሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ባለቤታቸውና ማሰሪያ አንቀጻቸው የተስማሙ ስላልሆኑ እንደገና አስተካክላችሁ ጻፏቸው፡፡**

1. ቶላ ወደቤቱ ሄዱ፡፡
2. አሰገደች መጣ፡፡
3. ሜቲና ማርቆስ ወደሱቃቸው ገባ፡፡
4. ለእርሳቸው ጉዳዩን ነገርኳት፡፡
5. መሐመድ እና ሞሚና ወንድምና እህት ነው፡፡

ለ. ከሚከተሉት አረፍተነገሮች ውስጥ ባለቤት፣ ተሳቢና ማሰሪያ አንቀጾችን ለይታችሁ አመልክቱ፡፡

ምሳሌ፡ ሾፌሩ አህያውን መታው፡፡

ባለቤት፡ ሾፌሩ

ተሳቢ፡ አህያውን

ማሰሪያ አንቀጽ፡ መታው

1. ፍጹም በጉን አባረረች፡፡
2. ልጁ መጣ፡፡
3. ጫላ ኳሱን አነጠረ፡፡
4. አባቴ ይወደኛል፡፡
5. እሷ በሬውን ሸሸች፡፡

# ምዕራፍ ሁለት

# የቤተሰብ ምጣኔ

## የሚጠበቁ ውጤቶች

**ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ፡-**

- የሚነበብላችሁን ምንባብ በጥሞና ካዳመጣችሁ በኋላ ከምንባቡ ለወጡ ጥያቄዎች መልስ ትሰጣላችሁ፡፡
- ቀላል ሁነቶችን በቅደም ተከተል ትተርካላችሁ፡፡
- የቀረበውን ምንባብ መሰረት በማድረግ ለተለያዩ ተግባራት መልስ ትሰጣላችሁ፡፡
- አስረጅ ድርሰት ትጽፋላችሁ፡፡
- ለአዳዲስ ቃላት ፍቺ ትሰጣላችሁ፡፡
- የቋንቋውን መሰረታዊ መዋቅሮች ጠብቃችሁ ዓረፍተ ነገር ትመሰርታላችሁ፡፡

**ክፍለጊዜ አንድ**

## ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

**በዚህ የትምህርት ይዘት የማዳመጥ ክሂላችሁን እንድትጠቀሙ የሚረዱ ምንባብና የመልመጃ ጥያቄዎች ቀርበዋል፡፡ምንባቡን በትኩረት በማዳመጥ ለጥያቄዎቹ ተገቢውን መልስ ስጡ፡፡**

### ቤተሰብን ያለመመጠን ጉዳት

### የቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች

**ሀ. ቤተሰብን አለመመጠን የሚያመጣው አሉታዊ ተጽእኖ ተናገሩ፡፡**

**ለ. ከዚህ በታች ለቀረቡት ሀረጋት ፍቺያቸውን ለመምህራችሁ በቃል ተናገሩ፡፡**

1. የቤተሰብ እቅድ አገልግሎት
2. መሰረታዊ ልማት
3. የኢኮኖሚ እድገት
4. የህዝብ ብዛት
5. አራርቆ መውለድ

## የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎች

1. በ1984 የኢትዮጵያ የህዝብ ብዛት ስንት ነበር?
2. ቤተሰብን አለመመጠን በየትኞቹ ዘርፎች ላይተጽእኖ ያመጣል ?

## የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች

### መልመጃ አንድ

**ሀ. ያዳመጣችሁትን ምንባብ መሰረት በማድረግ ለሚከተሉት ጥያቄዎች በቃል መልስ ስጡ፡፡**

1. የቤተሰብ እቅድ አገልግሎት በአንድ ሀገር ውስጥ በተግባር ላይ ማዋል የሚያስገኘውን ጥቅም ግለጹ፡፡
2. በየአመቱ የሚወለዱት ህጻናት ቁጥር መጨመር ምን ሊያስከትል እንደሚችል አስረዱ፡፡
3. የአንድ ሀገር ህዝብ ብዛት በጣም ካደገ በኢኮኖሚ፣በተፈጥሮ ሀብት እና በማህበራዊ ህይወት የሚያስከትለውን ተጽእኖ ዘርዝሩ፡፡
4. የቤተሰብ እቅድ ተጠቅሞ አራርቆ መውለድ ለአንድ ቤተሰብ የሚያስገኘውን ጥቅም አብራሩ፡፡
5. አሁን ባለው ሁኔታ የዛሬ አስር አመት የአገራችን የህዝብ ብዛት ቁጥር ስንት የሚደርስ ይመስላችኋል?

ክፍለጊዜ ሁለት

## ትምህርት ሁለት፡ መናገር

**በዚህ የትምህርት ክፍል ጭውውትና ተግባራት ስለቀረቡ ጭውውቱንና ተግባራቱን በሚቀርበው ትእዛዝ መሰረት አከናውኑ፡፡**

### ተግባር አንድ

**ሀ. ቀጥሎ የቀረበውን ጭውውት ጥንድ ጥንድ በመሆን ከተለማመዳችሁ በኋላ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ፡፡**

ሴና፡ እንዴት አደርክ ወዳጄ?

ከበደ፡ ደህና አደርሽ ሴና

ሴና፡ ምነው ትተክዛለህሳ?

ከበደ፡ ትንሿ ልጄ ታማብኝ ሀኪቤን ወሰደችው ባክሽን፡፡

ሴና፡ ምነው ምን አገኛት?

ከበደ፡ ሰውነቷ ከፍተኛ ትኩሳት አለው፡፡

ሴና፡ ጤና ጣቢያ ወሰድካት?

ከበደ፡ አዎ ወዳጄ ሀኪሞች "ቤተሰብ መጥናችሁ ውለዱ" ብለው ሲመክሩን አልሰማ ብለን ቤተሰቤና ገቢዬ አልመጣጠን ብሎ ልጄን ማሳከም እስኪያቅተኝ ደረስኩ፡፡

ሴና፡ እውነት ነው ቤተሰብን ብንመጥን ልጆቻችንን በአግባቡ ለማሳከም እንኳ እስከሚያቅት የሚደርስ ችግር አያጋልጥም::

ከበደ፡ እንግዲህ ሰው ከእኔ ይማር፡፡ በሚያገኘው ገቢ ልክ ቤተሰቡን መጥኖ ይውለድ፡፡

ሴና፡ ትክክል፣ ካንተ ህይወት ብዙ ትምህርት ወስጃለሁ፡፡ በል ና እኔ ጋር ልጄ በቀደም የላከልኝ ብር አለ ልጅህን ጤና ጣቢያ ወስደን እናሳክም፡፡ ስታገኝ ትሰጠኛለህ፡፡

ለ. ከላይ በቀረበው ጭውውት መሰረት በቡድናችሁ ተወያይታችሁ ሌላ መሰል ጭውውት አዘጋጅታችሁ ከተለማመዳችሁ በኋላ ለክፍል ተማሪዎች አቅርቡ፡፡

**ክፍለጊዜ ሶስት**

### ተግባር ሁለት

**ከዚህ በታች የቀረቡትን ተግባራት በተገቢው መንገድ አከናውኑ፡፡**

1. በቅድሚያ በአከባቢያችሁ ወደሚገኝ ጤና ጣቢያ ሂዱ፡፡ በመቀጠል ስለቤተሰብ እቅድ አገልግሎት የህክምና ባለሙያ በመጠየቅ መረጃዎችን አሰባስቡ፡፡ በመጨረሻም በቡድን በመሆን መረጃዎችን አደራጅታችሁ ዘገባውን ለክፍል ጓደኞቻችሁ በቃል አቅርቡ፡፡
2. እናንተ ወደፊት ቤተሰብ ስትመሰርቱ የቤተሰብ እቅድ አገልግሎት ተጠቃሚ ብትሆኑ የምታገኙትን ጥቅም ለጓደኞቻችሁ ተናገሩ፡፡

**ክፍለጊዜ አራት**

## ትምህርት ሶስት፡ማንበብ

**ቀጥሎ የቀረቡት ምንባብ እና መልመጃዎች አንብባችሁ እንድትረዱ የሚያግዙ ናቸው፡፡ በመሆኑም ምንባቡን በትኩረት በማንበብ ለቀረቡት ጥያቄዎች ተገቢውን መልስ ስጡ፡፡**

## ቅድመማንበብ ጥያቄዎች

**ሀ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች በቃል መልስ ስጡ፡፡**

1. የቤተሰብ እቅድ ማለት ምን ማለት ነው?
2. የቤተሰብ እቅድ አገልግሎት የሚሰጠው በየትኞቹ ተቋማት ይመስላችኋል?
3. የቤተሰብ እቅድ አገልግሎትን በተመለከተ ከምንባቡ ምን ምን ቁምነገሮች የምታገኙ ይመስላችኋል?

# የቤተሰብ ምጣኔ

እንደምንናችሁ ውድ እናቶችና አባቶች? ደህና ሰነበታችሁ? ኧ … ወይኒቱ እባላለሁ፡፡ በዚህ ቀበሌ የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያ ነኝ። ኧ … በጥሪያችን መሠረት ሰዓቱን አክብራችሁ በመገኘታችሁ ከልብ አመሰግናለሁ። በጋራ የተገናኘነው ዛሬ ለመጀመሪያ ጊዜ አይደል? መቼም ከሌሎች ባለሙያዎች ጋር በየጊዜው ውይይት እንዳደረጋችሁ እገምታለሁ።እሺ! እናቶቼና አባቶቼ! ዛሬ ደግሞ ጤና ነክ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ለውይይት መነሻ የሚሆኑ ሃሳቦችን አቀርብላችኋለሁ።

የቤተሰብ ምጣኔ ማለት በአንድ ቤተሰብ ውስጥ ሊኖሩ የሚገባቸውን የልጆች ቁጥር የመመጠን ልምድና በውልደት መካከል ያለውን የጊዜ ርዝመት የመወሰን ጉዳይ ማለት ነው። ለማብራራት ያህል በቤተሰብ ውስጥ የልጆች ቁጥር መመጠን ማለት ወላጆች በእንክብካቤ ማሣደግ የሚችሏቸውን ልጆች ብቻ ወስነው መውለድ ማለት ነው። አይደለም እንዴ? ኧ…ብልህ የሆኑ ባልና ሚስት እኮ ስለኑሯቸው ይወስናሉ። እንዲያውም ሰዎች በህይወታቸው ከሚወስኗቸው ጠቃሚ ውሣኔዎች መካከል ስንት ልጆች መውለድ እንዳለባቸው መወሰን አንዱና ዋነኛው ነው። እናንተስ? ኧ… በየቤታችሁ

የልጆቻችሁን ቁጥር ወስናችሁ ታውቃላችሁ? እንዳልኳችሁ ይህ እኮ ትልቅ ነገር ነው። እስቲ በጥሞና ተከታተሉኝ።

ኃላፊነት የሚሰማቸው ወላጆች እኮ… ለሚወልዷቸው ልጆች የሚያስፈልጓቸውን እንክብካቤ፣ ፍቅርና ድጋፍ መስጠት ይፈልጋሉ። እናንተስ? እናንተም ኃላፊነት እንደሚሰማችሁ እተማመናለሁ። ለማንኛውም የልጆችን ቁጥር ለመወሰን ስለሚያስችሉ ዘዴዎች እንነጋገራለን። እንግዲህ ስለቤተሰብ ምጣኔ ስናነሳ የልጆችን ቁጥር ለመመጠንና አራርቆ ለመውለድ የሚያስችሉ ሁለት ዘዴዎች እንዳሉ ማወቅ ይኖርብናል።እነሱም ተፈጥሯዊና ዘመናዊ ዘዴዎች ይባላሉ። ሁለቱም እርግዝናን ይከላከላሉ።

## የንባብ ጊዜ ጥያቄዎች

1. እስካሁን ካነበባችሁት ምን ቁምነገር እንዳገኛችሁ ለመምህራችሁ ተናገሩ፡፡
2. ቀጥለው የሚመጡት አንቀጾች ስለምን የሚያስረዱ ይመስላችኋል?

ተፈጥሯዊ ዘዴዎች የሚባሉት ከግንኙነት መታቀብ፣ ቀን መቁጠርና ጡት ማጥባት ናቸው። ዘመናዊ የእርግዝና መከላከያ ዘዴዎች ደግሞ ኮንዶም (የወንድና የሴት)፣ ዳያፍራም (ብራንፊ)፣ እንክብል፣ ሉፕ፣ በመርፌ የሚሰጥ መከላከያ (ዳይፖፕሮቬራ) እና በክንድ የሚቀበር (ኖርፕላንት ኮንትራሴፕቲቭ ኢምፕላንት) እና የመመሳሰሉት ናቸው። አያችሁ? እንግዲህ እናንተም ከነዚህ ዘዴዎች አንዱን መርጣችሁ እንደምትጠቀሙ ተስፋ አደርጋለሁ። እንግዲህ ሀሳቤን ላጠቃል።

እናንተ መገንዘብ የሚገባችሁ ዋናው ጉዳይ ኧ… የቤተሰብ ምጣኔ ማለት ኧ… ወላጆች መቼ ልጅ ይ…ኑረን? እና ኧ… ስንት ልጅ ይኑረን? ብለው ምላሽ የሚሰጡበት ዕቅድ መሆኑ ነው። ይህንንም ተረድታችሁ ከዛሬ ጀምሮ

ከባለቤታችሁ ጋር ተወያዩና ወደጤና ጣቢያ በመምጣት ኸ... አገልግሎቱን በሕክምና ባለሙያ ድጋፍ መጠቀም ትችላላችሁ። በተረፈ ዛሬ በውይይቱ ላልተካፈሉ ለምታውቋቸው እናቶች ሁሉ ፍሬነገሩን ባገኛችሁት አጋጣሚ እንድታስረዱ ኸ... አደራ እያልኩ ለዛሬ ገለፃዬን በዚሁ አበቃሁ። ስላዳመጣችሁኝ አመሰግናለሁ። በሌላ ጊዜ እስከምንገናኝ ደህና ሁኑ።

*(የኢ.ፌ.ድ.ሪ ትምህርት ሚኒስቴርና የኦሮሚያ ትምርት ቢሮ፡፡2007፡፡ ለአማርኛ ቋንቋ ማስተማሪያ ከተዘጋጀ መጽሀፍ የተወሰደ)*

**ክፍለጊዜ አምስት**

## የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች

### መልመጃ ሁለት

**ከዚህ በታች የቀረቡትን ጥያቄዎች ምንባቡን መሰረት በማድረግ ትክክል ከሆነ "እውነት" ካልሆነ ግን "ሀሰት" በማለት በጽሁፍ መልሱ፡፡**

1. በቀረበው ምንባብ ለወላጆች ስለጤና ነክ ጉዳዮች ትምህርት የሰጠችው የግብርና ባለሙያ ነበረች፡፡
2. ሀላፊነት የሚሰማቸው ወላጆች ልጆችን በእድላቸው ይደጉ በማለት የሚወልዱ ናቸው፡፡
3. በቤተሰብ ውስጥ የልጆችን ቁጥር መመጠን ማለት ወላጆች በእንክብካቤ ማሳደግ የሚችሏቸውን ልጆች ብቻ መውለድ ማለት ነው፡፡
4. በአገራችን ሁሉም ወላጆች ስለቤተሰብ ምጣኔ አስፈላጊውን እውቀት የጨበጡ ናቸው፡፡
5. ከቤተሰብ እቅድ መርሆዎች አንዱ ያልተፈለገ እርግዝና ለመከላከል የሚያስችሉ ዘዴዎችን መጠቀም ነው፡፡

6. ባለሙያዋ ስለቤተሰብ እቅድ ምንነት የገለጸችው በአንደኛው አንቀጽ ነው፡፡
7. ስለቤተሰብ ሀላፊነት በስፋት የቀረበው በአንቀጽ ሁለት ነው፡፡
8. “ኧ... ወላጆች መቼ ልጅ ይ...ኑረን?” የሚለው የንግግር ባህሪ መገለጫ ነው፡፡
9. በመጨረሻው አንቀጽ በመጀመሪያው ዓረፍተነገር “እናንተ...” በሚል የቀረበው ቃል የሚወክለው ታዳሚዎችን ነው፡፡
10. “እሺ! እናቶቼና አባቶቼ!” በሚለው ውስጥ አገልግሎት ላይ የዋለው ስርዓት ነጥብ ባለሙያዋ በስሜት እየተናገረች መሆኗን ያመለክታል፡፡

**ክፍለጊዜ ስድስት**

## ትምህርት አራት፡ መጻፍ

በመቀጠል በሳጥኑ ውስጥ ስለአስረጅ ጽሁፍ የሚገልጽ ማስታወሻ ቀርቦላችኋል፡፡ የቀረበውን ማስታወሻ በትኩረት በማንበብና ለአስረጅ ጽሁፍ የቀረበውን ምሳሌ መሰረት በማድረግ እናንተም አንቀጽ ትጽፉላችሁ፡፡

**ማስታወሻ**

**አስረጅ ጽሁፍ**

አስረጅ ጽሁፍ፡- አስረጅ ጽሁፍ ለአንባቢያን ስለአንድ ጉዳይ በማብራራትና መረጃ በመስጠት ወይም እውነታን በማስጨበጥ ላይ የሚያተኩር የድርሰት መጻፍያ ስልት ነው፡፡ አስረጂ ጽሁፍ በሚከተሉት ስልቶች ሊጻፍ ይችላል፡፡

- በማወዳደርና በማነጻጸር
- በምክንያትና ውጤት
- ተራኪ

ድርሰት ሲጻፍ መከተል ያለባችሁ ቅደም ተከተል የሚከተሉት ናቸው፡፡

**አንድን ጽሁፍ ለመጻፍ የሚያስፈልጉ ቅደምተከተሎች**

የመጻፍ ሂደት ቅደም ተከተሎች የሚባሉት የሚከተሉት ናቸው፡፡ እነሱም፡-

1. **ቅድመ መጻፍ፡-** ይህ ከመጻፋችን በፊት የሚከናወን ተግባር ሲሆን የሚከተሉትን ያጠቃልላል፡፡
   - ርእስ መምረጥ
   - ርእስ ማጥበብ
   - መረጃ መሰብሰብ
   - መረጃ ማደራጀት
   - ቢጋር ማዘጋጀት
2. የመጀመሪያውን ረቂቅ ማዘጋጀት
3. ረቂቁን መከለስ
4. አርትኦት/እንደገና ማስተካከል/
5. የመጨረሻውን ጽሁፍ መጻፍ ናቸው፡፡

**ክፍለጊዜ ሰባት**

**ተግባር ሶስት**

**በትምህርት ሶስት የቀረበላችሁን አስረጂ ጽሁፍ (ምንባብ) ከዚህ በታች ለሚቀርብላችሁ ተግባር በምሳሌነት በመጠቀም በሚቀርቡት ትእዛዞች መሰረት በግል አንድ አንቀጽ ጻፉ፡፡**

1. ከዚህ በታች አስረጂ አንቀጽ ሊያጽፉ የሚችሉ ሀሳቦች መካከል አንዱን ምረጡ፡፡

   ትጉህ ገበሬ እና ነጋዴ

   በጥዋት እና በከሰዓት ፈረቃ መማር

   ቤተሰብ መመጠንና አለመመጠን

2. የመረጣችሁትን ሀሳብ አንቀጽ ሊያጽፍ በሚያስችል መልኩ ርእሱን አጥብቡ፡፡ (ለምሳሌ ቤተሰብን መመጠንና አለመመጠን በቤተሰብ ኢኮኖሚ ላይ የሚያደርሰው ተጽእኖ)
3. መረጃ ከተለያዩ ምንጮች (የራስ ልምድ፣ ባለሙያ፣ መጣጥፎች ወዘተ) ሰብስቡ፡፡
4. መረጃችሁን አደራጅታችሁ አስተዋጽኦ ንደፉ፡፡
   ምሳሌ፡ የምግብ እጥረት፣ የመማሪያ ቁሳቁስ እጥረት፣ ልብስ፣ ጤና በመሳሰሉት ዙሪያ ሀሳባችሁን አደራጁ፡፡
5. የመጀመሪያውን ረቂቅ በመጻፍና ደጋግማችሁ በማረም አንቀጹን ጻፉና ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡

**ክፍለጊዜ ስምንት**

# ትምህርት አምስት፡ ቃላት

**በዚህ ትምህርት ክፍል የተለያዩ ቃላትን በአገባብ እንድትጠቀሙ የሚያስችሏችሁ መልመጃዎች ስለቀረቡ መልመጃዎቹን በትኩረት ስሩ፡፡**

**መልመጃ ሶስት**

**ሀ. ከዚህ በታች የቀረቡት አረፍተነገሮችና ሀረጋት የቤተሰብ ምጣኔ በሚል ርእስ ከቀረበው ምንባብ የወጡ ናቸው፡፡በመሆኑም ምንባቡን ደግማችሁ በማንበብ ከስራቸው ለተሰመረባቸው ቃላት አገባባዊ ፍቺ ስጡ፡፡**

1. ስለቤተሰብ ምጣኔ ስናነሳ የልጆችን ቁጥር…
2. ለዛሬ ገለፃዬን በዚሁ አበቃሁ።
3. ተፈጥሯዊ ዘዴዎች የሚባሉት ከግንኙነት መታቀብ …
4. በሕክምና ባለሙያ ድጋፍ መጠቀም ትችላላችሁ።
5. ዘመናዊ የእርግዝና መከላከያ ዘዴዎች…

ለ. በ "ሀ" ስር በቀረቡ አረፍተነገሮች ከስራቸው የተሰመረባቸውን ቃላት አገባባዊ ፍቺያቸውን ከ "ለ" ስር በመምረጥ አዛምዱ፡፡

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. ዝንጀሮው ከገደል ወድቆ አፈር በላ፡፡ | ሀ. አሸነፈ |
| 2. ሂካ ቁርሱን ሻይ በዳቦ በላ፡፡ | ለ. አሳዘነ |
| 3. ቦና እቁብ በላ፡፡ | ሐ. ተመገበ |
| 4. ገመቹ ሞባይሉን ተበላ፡፡ | መ. ሞተ |
| 5. የጅማ ከ.ነ.ማ. የእግር ኳስ ቡድን ዋንጫ በላ፡፡ | ሠ. ተሰረቀ |
| 6. የልጁ አሟሟት አንጀቴን በላው፡፡ | ረ. ደረሰ |
| | ሰ. ፈወሰ |

ክፍለጊዜ ዘጠኝ

## ትምህርት ስድስት፡ ሰዋስው

በዚህ የትምህርት ይዘት የሰዋስው እውቀታችሁን ለመጠቀም የሚያግዙ መልመጃዎች የቀረቡ ሲሆን ለጥያቄዎቹ በተገቢው መንገድ በጽሁፍ መልሱ፡፡

### መልመጃ አራት

ሀ. ዓረፍተነገርን በተመለከተ በምእራፍ አንድ የቀረበላችሁን ማስታወሻ መሰረት በማድረግ በሰንጠረዡ ውስጥ የቀረቡ ቃላትን በማገናኘት ሙሉ መልእክት የሚያስተላልፉ አስር ዓረፍተነገሮችን መስርቱ፡፡

| ባለቤት | ተሳቢ | ማሰሪያ አንቀጽ |
|---|---|---|
| ነጋዴው | ሰብሉን | ተንከባከበች |
| ዋንኦፊ | ህግ | ጣለች |
| ፖሊሷ | ታካሚዎችን | ናቸው |
| ከማል እና ተስፋዬ | ዶክተር | አስከበረች |
| ዶሮ | እህሉን | ሰበሰቡ |
| ሀኪሟ | ጓደኛሞች | ነች |
| ገበሬዎች | እንቁላል | ሸጠው |

**ለ. ከዚህ በታች የቀረቡት ዓረፍተነገሮች ተዘበራርቀው ስለተቀመጡ ሙሉ መልእክት አያስተላልፉም፡፡ ስለዚህ አረፍተነገሩን እንደገና አስተካክላችሁ ጻፉ፡፡**

1. ስለጠማት በላይነሽ ጠጣች ውሃ፡፡
2. ሰይፉ ደስ መምህሩ አለው ስለጠራው፡፡
3. መሰረት መጫወት ትወዳለች መረብ ኳስ፡፡
4. ወደቤቱ ከትምህርትቤት አቡበከር ሲወጣ በሩጫ ገባ፡፡

# ምዕራፍ ሶስት

# የበጎ ፈቃድ አገልግሎት

## የሚጠበቁ ውጤቶች

**ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ፡**

- ስለ አንድ ርዕሰ ጉዳይ አዳምጣችሁ ስሜታችሁን ትገልጻላችሁ፡፡
- የበጎ ፈቃደኝነት መተግበሪያ አካባቢዎችን ትለያላችሁ፡፡
- የምንባቡን ፍሬ ሀሳብ ታስታውሳላችሁ፡፡
- ምንባቡን አንብባችሁ ከምንባቡ ተዘውታሪ ቃላት ለይታችሁ ታወጣላችሁ፡፡
- አራት አንቀጽ ያሉት የማግባቢያ ድርሰት ትጽፋላችሁ፡፡
- የቃላትን ነጠላና ብዙ ቁጥር ለይታችሁ ታመለክታላችሁ፡፡

**ክፍለጊዜ አንድ**

## ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

**በዚህ የትምህርት ክፍል የተለያዩ የማዳመጥ መልመጃዎች ቀርበዋል፡፡ መምህራችሁ የሚያነቡላችሁን ጽሁፍ መሰረት አድርጋችሁ ጥያቄዎቹን በተገቢው መንገድ ስሩ፡፡**

### ኦብሴ ሉቦ

### ቅድመማዳመጥ ጥያቄዎች

**ሀ. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ፡፡**

1. ሰዎችን በተለያዩ ነገሮች መርዳት ምን ተብሎ ይጠራል?
2. ሰዎችን በምን በምን ተግባራት ረድታችሁ ታውቃላችሁ?

## የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎች

ከዚህ በታች የቀረቡ ጥያቄዎችን የሚነበብላችሁን ጽሁፍ እያዳመጣችሁ መልሶቹን በማስታወሻ ደብተራችሁ ላይ ጻፉ፡፡

1. አብሴ የተወለደችው የት ነው?
2. አብሴ የመጀመሪያ ዲግሪዋን ያገኘችው በምን ሙያ ነበር?.
3. የአንቀጾቹን ፍሬ ሀሳቦች መዝግቡ፡፡

## የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች

### ተግባር አንድ

በማዳመጥ ሂደት ስር የያዛችሁትን የጽሁፉን ፍሬ ሀሳቦች ተራ በተራ በመነሳት ለክፍል ተማሪዎች አንብቡላቸው፡፡

### መልመጃ አንድ

ሀ. ያዳመጣችሁትን ጽሁፍ መሰረት በማድረግ የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ፡፡

1. እነ አብሴ ወደሀገር ቤት ተመልሰው ምን ምን የበጎ ስራ አገልግሎት ሰጡ?
2. የኦክስጂን የመተንፈሻ መሳሪያ ለየትኞቹ ህሙማን አገልግሎት ይሰጣል?
3. አብሴን ያስደሰታት ምን ነበር?
4. አብሴን የበጎ ፈቃድ አገልግሎት እንድትሰጥ ያነሳሳት ምክንያት ምንድን ነው?

5. አብሴ ጓደኞቿን በበጎፈቃድ አገልግሎት እንዲሳተፉ እንዴት አሳመነች?
6. ከአብሴ ተግባር ምን መማር እንደሚቻል ተናገሩ፡፡
7. በመጨረሻ ላይ አብሴ ያስተላለፈችውን መልእክት በራሳችሁ አባባል ግለጹ፡፡

**ክፍለጊዜ ሁለት**

## ትምህርት ሁለት፡ መናገር

**ከዚህ በታች የቀረበው ምስል በቡድናችሁ ለምታደርጉት ንግግር መነሻ ይሆናችኋል፡፡ በዚህ መሰረት ከምስሉ በመቀጠል የቀረቡላችሁን ተግባራት በትኩረት አከናውኑ፡፡**



### ተግባር ሁለት

1. ከምስሉ ምን ተረዳችሁ?
2. በምስሉ እንደሚታየው ወጣት በምን በምን የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ተሳትፋችሁ ታውቃላችሁ?
3. በምስሉ ላይ እንደሚታየው ወጣት እናንተም እንዲህ አይነት ተግባር ለመፈጸም ያላችሁን እቅድ ለክፍል ተማሪዎች ተናገሩ፡፡
4. "ሰዎችን መርዳት በሰዎቹ ላይ የተረጂነት ስሜት ስለሚፈጥር ባይተገበር መልካም ነው።" በሚለው ሀሳብ ላይ ያላችሁን አቋም ግለጹ፡፡

# ትምህርት ሶስት፡ ማንበብ

**ከዚህ በታች የቀረቡት ምንባብ እና መልመጃዎች አንብባችሁ እንድትረዱ የሚያግዙ ናቸው፡፡ስለዚህ ምንባቡን በትኩረት በማንበብ ለቀረቡት ጥያቄዎች ተገቢውን መልስ ስጡ፡፡**

## ቅድመ ማንበብ ጥያቄዎች

**ሀ. ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቄዎች በቃል መልስ ስጡ፡፡**

1. በአከባቢያችሁ እና በሀገር አቀፍ ደረጃ በበጎ ተግባር የሚታወቁ ሰዎችን ጥቀሱ፡፡
2. በተራ ቁጥር አንድ የጠቀሳችኋቸው ሰዎች አበይት ተግባራት ምን ምን ናቸው?
3. ለሚከተሉት ቃላት እና ሀረጋት ፍቺ ስጡ፡፡
   - 3.1. ለትርፍ ያልተቋቋመ ልማት ተኮር ማህበር
   - 3.2. ለትርፍ የተቋቋመ

## ሙዳይ

ሙዳይ የበጎ አድራጎት ማህበር እ.ኤ.አ በ2000 የተቋቋመ ከማንኛውም የፖለቲካ እና ሀይማኖታዊ ነገሮች ነፃ የሆነና ለትርፍ ያልተቋቋመ ልማት ተኮር ማህበር ነው፡፡ ሆኖም ግን በህጋዊ መንገድ በይፋ የተመዘገበው እ.ኤ.አ ጥቅምት 4/2012 ላይ ነው፡፡ ተቋሙ ስራውን የጀመረው በአዲስ አበባ ከተማ የካ ክፍለከተማ ወረዳ 11 ውስጥ 200 የሚደርሱ አባላትን በመያዝ ነበር፡፡

ሙዳይ በጎ አድራጎት ማህበር በመጀመሪያ ይታወቅ የነበረው “ፍሬሽ ኤንድ ግሪን አካዳሚ” በሚባለው ለትርፍ በተቋቋመ ትምህርት ቤት አማካይነት

ነው፡፡ ሆኖም ግን ከቆይታ በኋላ የ"ፍሬሽ ኤንድ ግሪን" አካዳሚ ባለቤት የሆኑት ወይዘሮ ሙዳይ ምትኩ የትምህርት ቤት ክፍያ መክፈል የማይችሉ እንዲሁም ምሳ ማግኘት የማይችሉ በርካታ ተማሪዎች እንዳሉ በማስተዋላቸው ለጥቂት ተማሪዎች ነፃ የትምህርት እድል ለመስጠት ችለዋል፡፡ ሆኖም ግን ይህ የነጻ ትምህርት እድል የሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች ቁጥር እጅግ እያደገ በመምጣቱ የትምህርት ቤቱ ባለቤት የነበራቸውን የንግድ እንቅስቃሴ ወደ በጎ አድራጎት ማህበር ለመለወጥ በመወሰናቸው እ.ኤ.አ በ2012 ጀምሮ "ፍሬሽ ኤንድ ግሪን" አካዳሚ ከሙዳይ በጎ አድራጎት ማህበር እንዲለይ ውሳኔን አስተላለፉ፡፡

## የንባብ ጊዜ ጥያቄዎች

1. ከምንባቡ እስካሁን የተረዳችሁትን ፍሬ ሀሳብ ግለጹ፡፡
2. ቀጣዮቹ አንቀጾች ስለምን የሚያወሱ ይመስላችኋል?

የሙዳይ በጎ አድራጎት ዋነኛ ትኩረቱ የተለየ እገዛ የሚያስፈልጋቸው የአቅመ ደካማ ቤተሰብ ልጆች ላይ ነው፡፡ ተቋሙም ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው አካሎች ምግብ፣ ህክምና፣ የትምህርት ቤት ክፍያ፣ የምገባ ፕሮግራም፣ የትምህርት ቤት ቁሳቁስ ድጋፍ፣ ኮምፒውተርና ገቢ የሚያስገኙ ስልጠናዎች እየሰጠ ይገኛል፡፡

ከዚህ ድርጅት አብዛኛዎቹ ተጠቃሚዎች በተለያየ ምክንያት ልጆቻቸውን ያለ አባት የሚያሳድጉ አቅመ ደካማ እናቶች ናቸው፡፡ ከእነዚህ እናቶች አብዛኛዎቹ ከዚህ በፊት የተለያየ ጥቃት የደረሰባቸው፣ ኤችአይቪ ቫይረስ በደማቸው ውስጥ ያለ፣ መጠለያ የሌላቸውና ከዚህ በፊት በሴተኛ አዳሪነት ይተዳደሩ የነበሩ ናቸው፡፡ በጎ አድራጎቱ እነዚህን ሰዎች ካሉበት ችግር እንዲላቀቁ በርካታ ድጋፎችን ያደርጋል፡፡ ከነዚህም መካከል የተወሰኑት

የእጅ ስራ ስልጠናዎችን እንዲያገኙ በማድረግና የስራ ቦታ በማመቻቸት ስራዎችን መስራት እንዲችሉ አድርጓል፡፡

ሙዳይ በአሁኑ ሰአት 650 ለሚሆኑ ህፃናት እና 450 ለሚሆኑ እናቶች አገልግሎት እየሰጠ የሚገኝ ማህበር ነው፡፡ ይህ ተቋም ትኩረት ለሚያደርግላቸው አካላት የተለየ ፕሮጀክት ቀርፆ በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛል፡፡ ለዚህ ፕሮጀክት በዋነኛነት የገቢ ምንጭ ሆኖ የሚያገለግለው "ፍሬሽ ኤንድ ግሪን" ሀላፊነቱ የግል ማህበር ሲሆን በተጨማሪም የተለያዩ በጎ አድራጊ ግለሰቦች የግል ድርጅቶች የገቢ ምንጭ በመሆን ያገለግላሉ፡፡ በሙዳይ ማህበር ስር የሚገኙ ህፃናት ተቋሙ የመጠለያ፣ የምግብ፣ የአልባሳት፣ ትምህርት፣ ህክምና፣ ገቢ የሚያስገኙ የሙያ ስልጠናዎች እና የህይወት ክሂል ስልጠናዎች በመስጠት ወደ ስራ እንዲሰማሩ ያደርጋል፡፡

*(ከድርጅቱማህደር የተገኘና ለመማሪያ መጽሀፍ እንዲመች ተሻሽሎ የቀረበ)*

**ክፍለጊዜ አራት**

## የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች

**መልመጃ ሁለት**

**ሀ. ምሳሌውን መሰረት በማድረግ ከየአንቀጾቹ አምስት አምስት ተዘውታሪ ቃላት በመለየት ጻፉ፡፡**

| ተዘውታሪ ቃሉ ያለበት አንቀጽ | ተዘውታሪ ቃል |
|---|---|
| አንቀጽ አንድ | ልማት |
| አንቀጽ ሁለት | እናቶች |
| አንቀጽ ሶስት | ወላጅ |
| አንቀጽ አራት | ህክምና |

ለ. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት በስራቸው ከቀረቡት አማራጮች መካከል ትክክለኛውን መልስ በመምረጥ መልሱ፡፡

1. ለትርፍ ያልተቋቋመ ልማት ተኮር ማህበር ሲል ምን ማለት ነው?

ሀ. ነጋዴ

ሐ. በጎአድራጊ

ለ. አትራፊ

መ. ጥቅም ፈላጊ

2. ሙዳይ በጎ አድራጎት ማህበር በመጀመሪያ ይታወቅ የነበረው _______ ነው፡፡

ሀ. በትምህርት ስራ

ለ. ወላጆቻቸውን በተለያዩ ምክንያቶች ያጡ ህጻናትን በማሳደግ

ሐ. አረጋውያን በመርዳት

መ. አካል ጉዳተኞችን በማገዝ

3. ከሚከተሉት አንዱ የሙዳይ በጎ አድራጎት ማህበር ተጠቃሚ አካል ያልሆነው የቱ ነው?

ሀ. የኤችአይቪ ቫይረስ ተጠቂዎች

ለ. መጠለያ የሌላቸው ሰዎች

ሐ. በሴተኛ አዳሪነት የሚተዳደሩ

መ. ስራ አጥ ወጣቶች

4. የበጎ አድራጎት ማህበሩ ከመሰረታዊ ፍላጎቶች በተጨማሪ ለህፃናት ከሚሰጠው አገልግሎት ውስጥ የሚካተተው የቱ ነው?

ሀ. የትምህርት

ለ. የህክምና

ሐ. የህይወት ክሂል ስልጠናዎች

መ. ሁሉም መልስ ነው

5. የበጎአድራጎት ማህበሩ የገቢ ምንጭ ምንድን ነው?

ሀ. ከውጭ ሀገር የሚላክ እርዳታ

ለ. በሀገር ውስጥ ከሚሰበሰብ እርዳታ

ሐ. ከፍሬሽ ኤንድ ግሪን አካዳሚ ገቢ

መ. ለ እና ሐ መልስ ናቸው፡፡

### ተግባር ሶስት

በሚከተለው ሰንጠረዥ ውስጥ ሰዎች በበጎ ተግባር ሲሳተፉ የሚሰሩትና የተግባሩ ትሩፋት ምን እንደሆነ በምሳሌው መሰረት በጽሁፍ ግለጹ፡፡

| ሰዎች በበጎ ተግባር ሲሳተፉ የሚሰሩት | የተግባሩ ትሩፋቶች ምን ሊሆን ይችላል? |
|---|---|
| የአቅመ ደካሞችን ቤት መጠገን | ከብርድና ዝናብ እፎይታን ማግኘት |
| የጎርፍ መሄጃ ቦይ ማጽዳት | ጎርፍ በየመንገዱ ላይ ቆሻሻ አይበትንም |
| | |
| | |
| | |
| | |

ክፍለጊዜ አምስት

## ትምህርት አራት፡ መጻፍ

**የመጻፍ ክሂላችሁን ውጤታማ በሆነ መልኩ እንድትጠቀሙ የሚረዱ ማስታዎሻዎችና ተግባራት ቀርበዋል፡፡ ተግባራቱን በተገቢው መንገድ ስሩ፡፡**

**ማስታወሻ**

አስረጅ ድርሰት፣ ማግባቢያ ድርሰት /persuasive paragraph/ተብሎም ሊገለጽ ይችላል፡፡ አስረጅ ድርሰት ከሚጻፍባቸው ስልቶች መካከል አወዳዳሪና አነጻጻሪ የአንቀጽ ማስፋፊያ ስልቶች ይጠቀሳሉ፡፡

**አወዳዳሪና አነጻጻሪ አንቀጽ፡**

አወዳዳሪና አነጻጻሪ አንቀጽ የሚያብራራው በሁለት ነገሮች መካከል ያለን ተመሳስሎና ልዩነትን ነው።ማወዳደር በነገሮች መካከል ያሉትን ተመሳሳይ ባህሪያት ማብራራት ሲሆን ማነፃፀር ደግሞ ልዩነቶችን ማብራራት ነው።

## ተግባር አራት

በምእራፍ ሁለት መጻፍ በሚለው የትምህርት ይዘት ስር የተማራችሁትን ድርሰት ለመጻፍ የሚከናወኑ ተግባራትን አስታውሱ፡፡ በዚህ መሰረት የሚከተለውን ምሳሌ መሰረት በማድረግ አንድ ርዕስ መርጣችሁ በማወዳደር የአንቀጽ አጻጻፍ ስልት ሁለት አንቀጽ ያለው ድርሰት ጻፉ፡፡

**ምሳሌ፡ በማወዳደር የተጻፈ አንቀጽ**

መድኃኒት ቀማሚና ደራሲ የሚለያዩበት ነጥብ አለ፡፡ቀማሚ በአይን የሚታዩትንና በእጅ የሚዳሰሱትን ነገሮች እያሰባሰበና በእጁ እየገለበጠ ስለሚቀምማቸው ነው፡፡ደራሲ ግን በአእምሮው እየሰበሰበና እየቀረጸ ይጽፋል እንጂ እንደቀማሚ በእጁ አይዳስሳቸውም፡፡ በአይኑም አያያቸውም፡፡ ከተጠቀሱት ምክንያቶች በስተቀር እየሰበሰቡ ቀምሞና አዘጋጅቶ ለህዝብ በመስጠት ግን ሁለቱም አንድ ናቸው፡፡

**ክፍለጊዜ ሰባት**

## ተግባር አምስት

ከዚህ በታች ለማነጻጸር አንቀጽ የቀረበውን ምሳሌ መሰረት በማድረግ ከሚቀርቡላችሁ መነሻ ሀሳብ አንድ በመምረጥ ባለሁለት አንቀጽ ድርሰት ጽፋችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡

1. የድሮ ተማሪዎች እና የአሁንጊዜ ተማሪዎች
2. በገጠር አከባቢ የሚኖሩ እና በከተማ የሚኖሩ ተማሪዎች
3. በመማሪያ መጽሀፍት ብቻ ታግዞ መማር እና በአጋዥ መጽሃፍት ታግዞ መማር

**ምሳሌ፡ በማነጻጸር የተጻፈ አንቀጽ**

**በአብዛኛው የዛሬዎቹ ሴቶች ከግማሽ ምዕተ ዓመት በፊት ከነበሩት ጥንታዊ ሴቶች በቀለለና በተሻለ ሁኔታ ምግብ ማዘጋጀት ይችላሉ።** *የጥንት ሴቶች የማገዶ እንጨት ለመልቀም ወደዱር ይሄዳሉ፣ ያገኙትንም እንጨት የሚፈልጡትና የሚቆርጡት ራሳቸው ናቸው። የዛሬዎቹ ግን ምግብ የሚያዘጋጁት ያለ ብዙ ውጣውረድ የጋዝ ምድጃቸውን በክብሪት አቀጣጥለው ወይም ኤሌክትሪክ በመጠቀም ነው። የጥንቶቹ ሴቶች የምግብ አዘገጃጀት ሙያን የሚማሩት በትዕግስት በመመልከትና አስቸጋሪ በሆኑ ሁኔታዎች ውስጥ በማለፍ ነው፡፡ የዛሬዎቹ ግን በቀላሉ ስለሙያው ሊያሳውቃቸው የሚችሉና ስለጥሩ ምግብ አዘገጃጀት መመሪያዎችን ሊያስገነዝቧቸው የሚችሉ መጻሕፍትን በማንበብ ነው። የጥንት ሴቶች ከጓሯቸው ጎመን፣ ድንች፣ ቃሪያ፣ ወዘተ አምጥተው ሰርተው ሲያቀርቡ የዛሬዎቹ ግን የሚፈልጉትን የአትክልት አይነት በቀላሉ ወደ ገበያ ማዕከል ጎራ ብለው ያመጣሉ፡፡*

**ክፍለጊዜ ስምንት**

# ትምህርት አምስት፡ ቃላት

**ከዚህ በታች የቀረበው ማስታወሻ እና መልመጃዎች አዳዲስ ቃላትንና ጥምር ቃላትን እንድትለዩ የሚረዱ ናቸው፡፡ ለጥያቄዎቹ ተገቢ መልስ በጽሁፍ ስጡ፡፡**

## መልመጃ ሶስት

**ከላይ ለማነጻጸር ከቀረበው ምሳሌ ውስጥ አምስት አዳዲስ ቃላትን መርጣችሁ በማውጣትና ፍቺ በመስጠት እርስበርስ ተለዋውጣችሁ አርሙ፡፡**

ምሳሌ፡ **የገበያ አዳራሽ -** ሰዎች የተለያዩ ነገሮችን የሚገዙበት የገበያ ማእከል

**ማስታወሻ**

**ጥምር ቃል፡** ሁለት ቃላት ተጣምረው የሚፈጥሩት ሌላ አዲስ ትርጉም ያለው አንድ ቃል ነው፡፡ አንድ ቃል ለመሆኑም መለያ መስፈርቱን የሚከተለውን ምሳሌ ማየት ይቻላል፡፡

የጥምር ቃሉ ትርጉም ቃሉን ካስገኙት ተጣማሪ ቃላት የተለየ ነው፡፡ ምሳሌ፡ **ጤናጣቢያ -** የህክምና አገልግሎት የሚሰጥ ተቋም ነው፡፡ ይህ ቃል ከሁለት ቃላት የተመሰረተ ነው፡፡ ከጤና እና ጣቢያ፤ ጤና የሰውን ልጅ የጤንነትን ሁኔታ ሲያመለክት ጣቢያ ደግሞ የአንድ ነገር መገኛ ቦታ ያመለክታል፡፡ስለዚህ ሁለቱ ቃላት ሳይጣመሩ የነበራቸው ትርጉምና ከተጣመሩ በኋላ ያላቸው ትርጉም የተለየ ነው፡፡

## መልመጃ አራት

**ሀ. ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥምር ቃላት ቃላቱ ሳይጣመሩ የያዙትን ፍቺ እና ከተጣመሩ በኋላ ያላቸውን ፍቺ በጽሁፍ አመልክቱ፡፡**

| | | |
|---|---|---|
| ምሳሌ፡ በጎ ፈቃድ | በጎ | ጥሩ ነገር |
| | ፈቃድ | ይሁንታ |

በጎፈቃድ፡ በፍላጎት አንድን ነገር ለመስራት መወሰን

1. ትምህርትቤት
2. ልበሙሉ
3. ሰውሰራሽ
4. ደንብልብስ

**ክፍለጊዜ ዘጠኝ**

## ትምህርት ስድስት፡ ሰዋስው

**ከዚህ በታች የቀረቡት ማስታወሻ እና መልመጃዎች የሰዋስው ችሎታችሁን በተገቢው መንገድ እንድትጠቀሙ የሚረዱ ናቸው፡፡ ስለሆነም ለጥያቄዎቹ በጽሁፍ ተገቢውን መልስ ስጡ፡፡**

**ማስታወሻ**

**የቃላት ነጠላና የብዙ ቁጥር ምንነት**

ነጠላ ቁጥር አንድ ነገር ሲያመለክት፣ ብዙ ቁጥር ግን ከአንድ በላይ የሆኑ ነገሮችን ያመለክታል፡፡

ምሳሌ፡- ሀ. ፍየል --ፍየሎች

ለ. ቃል--ቃላት

ከላይ ለመመልከት እንደቻልነው ፍየል የሚለው አንድ ፍየል መሆኑን ሲያመለክት ፍየሎች የሚለው ቃል ግን ከአንድ በላይ መሆናቸውን ያመለክታል፡፡ ይህም የሆነበት ምክንያት /-ኦች/ አብዥ ቅጥያ ምእላድ ስለተጨመረበት ነው፡፡ የሁለተኛው ምሳሌ፡ ቃል ነጠላ ቁጥርን ሲያመለክት ቃላት ግን ብዙ ቁጥር ያመለክታል፡፡ በቃሉ ላይም /-ኣት/ የሚል አብዢ ቅጥያ ምላድ ተጨምሮበታል፡፡ /-ኦች/ የአማርኛ አብዢ ቅጥያ ሲሆን /-ኣት/ የግእዙ አብዢ ቅጥያ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡

## መልመጃ አምስት

**ሀ. ከዚህ በታች በነጠላ ቁጥር የቀረቡትን ወደ ብዙ ቁጥር በመለወጥ አብዢ ቅጥያ ምእላዶችን ለይታችሁ አመልክቱ፡፡**

ምሳሌ፡ ልጅ - ነጠላቁጥር

ልጆች - ብዙቁጥር ቅጥያ ምእላዱ /-ኦች/

1. ቤት
2. ሰው
3. ቃል
4. እንስሳ
5. ደብተር

**ለ. ከዚህ በታች ከቀረቡት ቃላት የያዙትን አብዢ ቅጥያዎችን በመለየት ወደ ነጠላ ቁጥር ቀይሩ፡፡**

ምሳሌ፡- ፍየሎች - ብዙ ቁጥር ቅጥያ ምዕላዱ /ኦች/

ፍየል - ነጠላ ቁጥር

እንስሳት - ብዙ ቁጥር ቅጥያ ምዕላዱ /-ኣት/

እንስሳ - ነጠላ ቁጥር

1. ሴቶች
2. ወንዶች
3. ትእዛዞች
4. ገዳማት
5. እርሳሶች

# ምእራፍ አራት

# የታዋቂ ግለሰቦች ህይወት ታሪክ

## የሚጠበቁ ውጤቶች

**ከዚህ ምእራፍ ትምህርት በኋላ፡**

- የቀረበውን ምንባብ በማድመጥ ፍሬ ሀሳቡን ትናገራላችሁ፡፡
- በቡድን በመሆን በቀረበ መመሪያ ላይ ትወያያላችሁ፡፡
- አንብባችሁ ፈሊጣዊ አነጋገሮችን ትለያላችሁ፡፡
- የመሸጋገሪያ ቃላትን ትለያላችሁ፡፡
- ተዘውታሪ ቃላትን ለተለያዩ አገልግሎቶች ትጠቀማላችሁ፡፡
- ሀረጋትን ትለያላችሁ፡፡

**ክፍለጊዜ አንድ**

## ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

**የማዳመጥ ክሂላችሁን እንድትጠቀሙ የሚረዱ ጽሁፍ እና የመልመጃ ጥያቄዎች ቀርበዋል፡፡ በትኩረት በማዳመጥ ጥያቄዎቹን በተገቢው መንገድ ስሩ፡፡**

## አርቲስት አሊ ቢራ

### ቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች

**ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቄዎች በቃል መልስ ስጡ፡፡**

1. የምታውቋቸውን ስመጥር ድምጻዊያንን ስም ዘርዝሩ?
2. የህይወት ታሪክ በውስጡ የሚያካትተውን ጉዳዮች ዘርዝሩ፡፡
3. ከዚህ በታች የቀረበው ፎቶ የማን እንደሆነ ለመምህራችሁ ተናገሩ፡፡



አርቲስት ዓሊ ቢራ

## የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎች

1. አርቲስት ዓሊ ቢራ የተወለደው የት ነው?
2. አርቲስቱ የሀይማኖት ትምህርቱን የተከታተለው እስከ ስንት ዓመት እድሜው ድረስ ነው?
3. ጽሁፉን እያዳመጣችሁ አዳዲስ ቃላትን በማስታወሻ ደብተራችሁ መዝግቡ፡፡

## የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች

### መልመጃ አንድ

**ሀ. የሚከተለው አንቀጽ ካዳመጣችሁት ጽሁፍ የተወሰደ ነው፡፡ ከአንቀጹ የወጡ ቃላትን በተገቢው ቦታቸው በማስገባት አንቀጹ የተሟላ ሃሳብ እንዲሰጥ አድርጉ፡፡**

| | |
|---|---|
| የሙዚቃ ባንድ | ጥሪውን |
| «ከአርፊን ቀሎ» | «ቢራን በሪኤ» |

አርቲስት ዓሊ ቢራ በሚያቀነቅነው ዘፈን የአድማጭን ስሜት በመያዙ እና በማስደሰቱ ከህዝብ ከፍተኛ አድናቆትን አተረፈ። በ1962 ዓ.ም. በድሬዳዋ ከተማ ከሚገኘው «ከአርፈንቀሎ» __________ ለአርቲስቱ የአብረን እንሥራ ጥሪ ቀረበለት። ዓሊም __________ በደስታ ተቀብሎ በ1963 የባንዱ አባል በመሆን ከባንዱ ጋር ስራውን ማቅረብ ጀመረ። __________ የሙዚቃ ባንድ ጋር በመሆን __________ የተሰኘውን ሙዚቃ ለአድማጭ አቀረበ።

## ለ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ከተሰጡት አማራጮች ተገቢውን መልስ መርጣችሁ ጻፉ፡፡

1. ትምህርቱን እየተማረ <u>ጎን ለጎን</u> የሚወዳቸውን ሙዚቃዎች በተለያዩ ቋንቋዎች እያዳመጠ አደገ፡፡ ከስሩ የተሰመረው ቃል የሚያመለክተው

   ሀ. አንድ ነገር ላይ ማተኮሩን ሐ. ሁለት ነገሮችን እየተገበረ መሆኑን

   ለ.ትምህርቱን መማሩ መ. የሚወዳቸው ሙዚቃ መኖራቸውን

2. አርቲስት አሊ ቢራ በሚያቀነቅነው ዘፈን የአድማጭን ስሜት <u>በመያዙ</u> አድናቆትን አተረፈ፡፡ የተሰመረበት ቃል አገባባዊ ትርጉም

   ሀ. በእጁ መጨበጡ ሐ. ማቀፉ

   ለ. ትኩረት መሳቡ መ. ስሜቱን መጉዳቱ

3. ዓሊ በሙዚቃው ዘርፍ <u>የላቀ</u> አስተዋጽኦ አድርጓል፡፡ ለተሰመረበት ቃል ፍቺ ሊሆን የሚችለው የቱ ነው?

   ሀ. ያነሰ ለ. ጥቂት ሐ. ዝቅተኛ መ. ከፍተኛ

4. “ለአዲሱ ትውልድ ጥሩ ተምሳሌት ሆነ፡፡” ሲባል ማንን ለማመልከት ተፈልጎ ነው?

   ሀ. በዘመኑ ያለን ወጣት ሐ. ህዝቡን

   ለ. በእድሜ የገፉ ሰዎችን መ. በህይወት የሌሉ ሰዎችን

5. የአርቲስቱ ስም ዓሊ መሀመድ ከሚለው ይልቅ ዓሊ ቢራ በሚል በሰዎች ዘንድ እንዲጠራ ያደረገው

ሀ. ወላጆቹ ስሙ በዚህ እንዲጠራ ስለፈለጉ
ሐ. በመምህሩ ምክንያት
ለ. "ቢራንበሪኤ" በሚለው ዘፈኑ ምክንያት
መ.በጓደኞቹ ምክንያት

**ክፍለጊዜ ሁለት**

## ትምህርት ሁለት፡ መናገር

**ከዚህ በታች የቀረቡት ተግባራት የመናገር ክሂላችሁን እንድትጠቀሙ የሚያግዙ ስለሆኑ ተግባራቱን በተገቢው መንገድ ስሩ፡፡**

**ማስታወሻ**

**የህይወት ታሪክ**

የህይወት ታሪክ የግለሰቦችን የቤተሰብ ሁኔታ፣ የትውልድ ስፍራና ዘመን፣ የአስተዳደግ ሁኔታ፣ የትምህርት ሁኔታ እና ለማህበረሰባቸው፣ ለአገራቸው ብሎም ለአለም ያበረከቷቸውን አስተዋጽኦዎች በማካተት በሌላ ሰው የሚጻፍ ነው፡፡ ይህም ግለሰቦች በህይወት እያሉና ከዚህ አለም በሞት ከተለዩ በኋላ ሊጻፍ ይችላል፡፡ በሌላ በኩል የሚጻፈው በራሱ በባለታሪኩ ከሆነ ግለታሪክ ይባላል፡፡

**ተግባር አንድ**

**ሀ. የሚከተሉትን ተግባራት ካከናወናችሁ በኋላ ሀሳባችሁን በንግግር ለክፍል ጓደኞቻችሁ ግለጹ፡፡**

1. ከዚህ በፊት የግለሰብ የህይወት ታሪክ ሲነበብ ሰምታችሁ የምታውቁ ከሆነ ምን ምን እንዳካተተ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ፡፡
2. የራሳችሁን ግለታሪክ ለክፍል ተማሪዎች ተራ በተራ እየተነሳችሁ ተናገሩ፡፡

ክፍለጊዜ ሶስት

**ተግባር ሁለት**

1. በህይወት ወይም ከህልፈተ ህይወት በኋላ የተጻፉ የህይወት ታሪኮችን ከተለያዩ ምንጮች በማሰባሰብ ወደክፍል አምጥታችሁ ለተማሪዎች አንብቡ፡፡

ክፍለጊዜ አራት

# ትምህርት ሶስት፡ ማንበብ

**ከዚህ በታች የቀረቡት ምንባብና መልመጃዎች የአንብቦ መረዳት ክሂላችሁን እንድትጠቀሙ የሚረዱ በመሆናቸው ጥያቄዎቹን በትኩረት በመስራት መልስ ስጡ፡፡**


## ቅድመ ማንበብ ጥያቄዎች

**ሀ. ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቄዎች በቃል መልስ ስጡ፡፡**

1. የምታውቋቸውን ስመጥር ሰዓሊያን ስም ዘርዝሩ፡፡
2. በአከባቢያችሁ ከሚገኙ ቁሳቁሶች ቅርጻ ቅርጾችን አዘጋጅታችሁ ታውቃላችሁ? ከሆነ ምን ምን?
3. ለቀረቡት ቁልፍ ቃላት በቡድን ተወያይታችሁ ትርጉማቸውን ለመምህራችሁ ተናገሩ፡፡

| | |
|---|---|
| አርቲስት | ቅርጻቅርጽ |
| የስእል ጥበብ | ኤግዚብሽን |

# አርቲስት ሻምበል ለማ ጉያ



አርቲስት ሻምበል ለማ ጉያ በ1921 ዓ.ም በምስራቅ ሸዋ ዞን በአዳአ ሊበን ወረዳ ዳሎ በምትባል ቦታ ተወለደ። ቤተሰቦቹ አርሶ አደሮች ስለ ነበሩ ሻምበል ለማ በግብርና ሥራ ቤተሰቦቹን እያገዘ አደገ። ከግብርና ጐን ለጐንም የእርሻ መሣሪያዎች ሞፈር፣ ቀንበርና የመሳሰሉት ሲሰሩ በትኩረት ይመለከት ነበር። እንዲሁም የአካባቢው ማህበረሰብ የተለያዩ የቤት ውስጥ መገልገያ ቁሶችን ከሸክላና ከጭቃ ሲሰሩ እያየ አደገ።

አርቲስት ሻምበል ለማ ጉያ በሕፃንነቱ የማህበረሰቡን ሙያ እያየ ስለአደገ የተለያዩ ቅርጻ ቅርጾችንና ሥዕሎችን ከእንጨትና ከሸክላ መሥራት ጀመረ። እሱ የሚሰራቸውን ሥራዎች እያዩ የአካባቢው ነዋሪዎች ስለተደነቁ አባቱ ትምህርት ቤት እነዲያስገቡት መከሯቸው። አርቲስት ለማ በአካባቢው ያገኘውን ልምድ እያሰፋ በመሄድ ዕድሜው 17 ዓመት በደረሰ ጊዜ ትምህርት ቤት የመግባት ዕድል አገኘ። ትምህርት ቤት ውስጥም ሥዕል በመሳልና በትምህርቱ ላይ ባለው ትጋት በተማሪዎችና በመምህራን እየተደነቀ መጣ። እስከ ሰባተኛ ክፍል በቢሾፍቱ ከተማ በቢሾፍቱ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በዚያን ጊዜ «ልብነድንግል» በሚባል ትምህርት ቤት ተማረ። በዘመኑ እሱ የተማረው የክፍል ደረጃ እንደከፍተኛ ደረጃ ስለሚታይ

በመምህርነት ሙያ እንዲሰለጥን ወደ ማሰልጠኛ ተላከ። ይሁን እንጂ ለሥልጠናው ፍላጎት ስላልነበረው ወደ ቢሾፍቱ በመመለስ የተለያዩ ቅርጻቅርጾችንና ሥዕሎችን ሰው በሚማርክ መልኩ መቅረፅና መሣሉን ቀጠለ።

አርቲስት ለማ በዚያ ጊዜ ከሰራቸው ቅርጻቅርጾች መካከል አንዱ ከእንጨትና ከአቡጀዲ ጨርቅ ተሰርቶ ወደ አየር ኃይል የተላከ የአውሮፕላን ቅርፅ ነው። ይህን ቅርፅ የአየር ኃይል ሠራተኞች በጣም ከመውደዳቸውና ከመገረማቸው የተነሣ ለአየር ኃይሉ የበላይ አስተዳዳሪ አሳዩ። አስተዳደሩም በዚህ የአውሮፕላን ቅርፅ በመደነቁ ቅርጹን የሰራውን ሰው እንዲያቀርቡለት አዘዘ። አርቲስት ለማም በአስተዳደሩ መፈለጉን ሲሰማ ወደ ኢትዮጵያ አየር ኃይል አቀና። አርቲስቱ እዚያ እንደደረሰ የአየር ኃይል አስተዳደሩም ጥበቡን በማድነቅ ወደፊት ምን መሆን እንደሚፈልግ ጠየቀው። እሱም «በኢትዮጵያ አየር ኃይል ውስጥ ገብቼ መሥራት እፈልጋለሁ።» በማለት ፍላጎቱን ገለፀ። አስተዳደሩም ጥያቄውን ተቀብሎ ፈቀደለት። አርቲስቱም አየር ኃይል ከገባ በኋላ የጦር መሣሪያ ሥልጠናንና የአውሮፕላን አካላትን መፍታትና መጠገን ለአምስት ዓመታት ሰልጥኖ ተመረቀ። በተመረቀበት ሙያም ሰዎችን እያሰለጠነ ነበር።

አርቲስት ሻምበል ለማ ጉያ መደበኛ ሥራውን እየሰራ የሥዕል መሣል ጥበብን ከኢጣሊያ አርቲስቶች ጋር በመሆን በይበልጥ አዳበረ። ከዚያም በኋላ የተለያዩ ሥዕሎችን በመሣል በ1950 ዓ.ም በአስመራ ለኤግዚቢሽን አቀረበ። ከዚህም በመነሣት ታዋቂ እየሆነ መጣ። ይሁን እንጂ በዚያን ጊዜ በማህበረሰቡ ላይ ይደርስ የነበረው ግፍና ጭቆና በጣም እያሣሰበው ስለመጣ በጥበብ ሥራው ተቃውሞውን መግለፅ ጀመረ። ለምሣሌ ወተት ደፍታ፣ እሷጋ ያለውንም አይጥ ትታ ከገመድ ላይ ያለውን ሥጋ ለማውረድ

የምትሞክረውን ድመት በመሣሉ በዚያን ጊዜ የነበሩት ባለሥልጣናት ሥራውን ተቃውመው የመንግስት ሥራ እንዲያቆም አደረጉት።

## የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎች

1. እያነበባችሁት ካለው ምንባብ የየአንቀጾቹን ፍሬ ሀሳብ በማስታወሻ ደብተራችሁ መዝግቡ፡፡
2. ከምንባቡ አዳዲስ ቃላት ለይታችሁ መዝግቡ፡፡
3. የሚቀጥለው ምንባብ መልእክት ምን ሊሆን እንደሚችል ግምታችሁን ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ፡፡

አርቲስት ለማ ወደ ኋላ ሳይመለስ የሥዕል መሣል ተግባሩን በቁርጠኝነት ቀጠለ። በዚህ ሙያውም ታዋቂነት ከማግኘቱ የተነሣ ከዓለም አገሮች እንደ አሜሪካ፣ ስዊድን፣ ዩናይትድ ኪንግደም፣ ኬኒያና ሴኔጋል ውስጥ ሥራውን ለኤግዚቢሽን ማቅረብ ችሏል። ከዚህም ብዙ ገቢ አግኝቷል። በአገኘው ገቢ ቢሾፍቱ ውስጥ «የአፍሪካ አርትጋለሪ» አቋቁሟል። በዚህ ጋለሪ ውስጥም ከእንጨት፣ ከቆዳ፣ ከቅል፣ ከእንስሳት ፀጉርና ከመሣሰሉት የተሰሩ ለዓይን ማራኪ የሆኑ ሥዕሎችና ቅርጻቅርጾች በብዛት ይገኛሉ። ወደ አርቲስት ሻምበል ለማ ጉያ ጋለሪ የሚሄዱ የአገር ውስጥና የውጭ አገር ዜግነት ያላቸው ሰዎች ሥዕሉን በብዛት ስለሚገዙ ከዚህ በሚያገኘው ገቢ ኢኮኖሚውን እያሳደገ መጣ።

አርቲስት ለማ ሙያውን ለልጆቹና ወንድሞቹ ስለአስተማረ እነርሱም ከእሱ የተማሩትን ሙያ የገቢ ምንጫቸው አድርገው በአገር ውስጥና በውጭ አገር የተመቻቸ ኑሮ እየኖሩ ይገኛሉ። ሙያውን ለተተኪ ትውልድ ለማስተላለፍ ባለው ምኞትና ተነሣሽነት ጋለሪው በሚገኝበት ቦታ ሕንፃ በማሠራት በውስጡ የመዋዕለ ሕፃናት ትምህርት ቤት ከፍቶ ከመደበኛ ትምህርት ጐን

ለጐን ሕፃናት የሥዕል ትምህርት ችሎታቸውን እንዲያደብሩ ሙያውን እያጐናፀፋቸው ነው። አርቲስት ለማ ጉያ ከ2010 ጀምሮ ባደረበት ህመም ምክንያት ሀገር ውስጥና ከሀገር ውጭ ባሉ ዶክተሮች ሲረዳ ቆይቶ በጥቅምት 16/2010 በ92 ዓመቱ በአዲስ አበባ አረፈ፡፡

በአጠቃላይ አርቲስት ሻምበል ለማ ጉያ በሥዕልና ቅርጻቅርጽ ሙያው በዓለም ትልቅ ታዋቂነት ያገኘና የኪነ-ጥበብ እድገትን በማስቀጠል ረገድ ትልቅ ሚና የተጫወተ የኪነ ጥበብ ሰው ነበር።

*(የኢፌድሪ ትምህርት ሚኒስቴርና የኦሮሚያ ትምርት ቢሮ፡፡2007፡፡ ለአማርኛ ቋንቋ ማስተማሪያ ከተዘጋጀዉ መጽሐፍ መጠነኛ መሻሻል ተደርጎበት የተወሰደ)*

**ክፍለጊዜ አምስት**

## የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች

**መልመጃ ሁለት**

**ሀ. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባዳመጣችሁት ጽሁፍ መሰረት በቃል መልሱ፡፡**

1. አርቲስቱ በልጅነቱ እያየ ያደገው ምን ነበር?
2. የአከባቢው ማህበረሰብ የአርቲስቱን አባት ልጃቸውን ትምህርት ቤት እንዲያስገቡ የመከሯቸው ምን በማየት ነው?
3. የመምህርነትን ሙያ እንዲሰለጥን ሲላክ ትቶ የተመለሰው ወደየትኛው ከተማ ነበር?
4. አርቲስቱ "የአፍሪካ አርት ጋለሪ " በሚል ባቋቋመው ውስጥ የሚገኙት ምን ምን ናቸው?
5. አርቲስቱ ስራውን በኤግዚቢሽን ያሳይ የነበረበትን አገራት ተናገሩ፡፡

**ለ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ባዳመጣችሁት ጽሁፍ መሰረት ትክክል ከሆነ 'እውነት' ካልሆነ ግን 'ሀሰት' በማለት በጽሁፍ መልስ ስጡ፡፡**

1. አርቲስቱ ከእንጨትና ከአቡጀዲ የሰራው የመኪና ቅርጽ ነበር፡፡
2. አርቲስቱ የስእል ጥበቡን በይበልጥ ያዳበረው ከእንግሊዝ አርቲስቶች ጋር በመሆን ነው፡፡
3. ስለአርቲስቱ የአስተዳደግ ሁኔታ ያነበባችሁት በጽሁፉ መጨረሻ ክፍል ነው፡፡
4. በሁለተኛው አንቀጽ ውስጥ **"ይሁን እንጂ"** የሚለው አያያዥ ቃል አርቲስቱ የስእል ጥበብን ትቶ ወደመምህርነት መመለሱን ያመለክታል፡፡
5. አርቲስቱ ከመደበኛው ስራ ጎን ለጎን ህጻናት የስእል ችሎታቸውን እንዲያዳብሩ እገዛ ያደርግ ነበር፡፡

**ክፍለጊዜ ስድስት**

**ሐ. ከስራቸው ለተሰመረባቸው ቃላት በአረፍተነገሩ ውስጥ የሚኖራቸውን አገባባዊ ፍች በጽሁፍ አመልክቱ፡፡**

1. ቤተሰቦቹ <u>አርሶ አደሮች</u> ነበሩ፡፡
2. የእርሻ መሳሪያዎችን ሲሰሩ <u>በትኩረት</u> ይመለከት ነበር፡፡
3. በትምህርቱ ላይ ባለው <u>ትጋት</u> በተማሪዎችና በመምህራን እየተደነቀ መጣ፡፡
4. ለማም በአስተዳደሩ መፈለጉን ሲሰማ ወደ ኢትዮጵያ አየር ሀይል <u>አቀና</u>፡፡

**መ. በ'ሀ' ስር ለቀረቡት ጥያቄዎች ከ 'ለ' ስር ፍቺያቸውን በመምረጥ አዛምዱ፡፡**

| "ሀ" | "ለ" |
|---|---|
| 1. ተግባር | ሀ. ቁስል |
| 2. ውጭ አገር | ለ. ብቃት |
| 3. ህመም | ሐ. ባህር ማዶ |
| 4. ሚና | መ. የልጆች መዋያ |
| 5. ለማስተላለፍ | ሠ. በአብዛኛው |
| 6. በብዛት | ረ. ለማዛመት |
| 7. ወደኋላ | ሰ. ድርሻ |
| 8. መዋዕለ ህጻናት | ሸ. ወደቀድሞው |
| 9. ችሎታ | ቀ. በመገረሙ |
| 10. በመደነቁ | በ. ድርጊት |

## ተግባር ሶስት

**ከዚህ በታች በቀረቡት ጥያቄዎች ላይ በቡድን ተወያይታችሁ የደረሳችሁበትን ሀሳብ በቃል ለክፍል ተማሪዎች አቅርቡ፡፡**

1. አርቲስቱ በአከባቢው የተለያዩ ቅርጻቅርጾች ሲሰሩ እያየ ማደጉ ለሙያው መጎልበት ምንአስተዋጽኦ ያደረገ ይመስላችኋል?
2. ታዋቂ ሰው መሆን የሚኖረውን ጥቅምና ጉዳት አስረዱ፡፡
3. አርቲስቶችና የህክምና ባለሙያዎች ለህብረተሰቡ የሚሰጡትን አገልግሎት አስረዱ፡፡

ክፍለጊዜ ሰባት

## ትምህርት አራት፡ መጻፍ

**ከዚህ በታች የቀረቡት ተግባራት የመጻፍ ክሂላችሁን እንድትጠቀሙ የሚያግዙ ቀርበዋል፡፡ ተግባራቱን በሚሰጠው ትእዛዝ መሰረት ስሩ፡፡**

### ተግባር አራት

**ከቀረበላችሁ አንቀጽ ውስጥ የመሸጋገሪያ ቃላት አውጥታችሁ ጻፉ፡፡**

ምሳሌ፡ ይኸውም

ስለ ስነጽሁፍ መነጋገር ሲጀመር ገና ከመነሻው ተዘውትሮ የሚጠየቅ አንድ ጥያቄ አለ፡፡ **ይኸውም** ማንኛውም የተጻፈ ነገር ስነጽሁፍ ነው ወይስ አይደለም? የሚል ነው፡፡ ለጥያቄው የሚሰጠው መልስ በሁለት አቅጣጫዎች ነውም አይደለምም ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ የመጀመሪያው አቅጣጫ ማንኛውም የተጻፈ ነገር ማለትም በወረቀት፣ በእንጨት፣ በድንጋይ፣ በጨርቅ እንዲሁም በመሰል ነገሮች በጽሁፍ ተቀርጾ የተገኘ ሁሉ ስነጽሁፍ ነው ይላሉ፡፡ ሁለተኛው አቅጣጫ ተጽፎ የተገኘ ሁሉ ስነጽሁፍ አይደለም የሚለው ሲሆን ከላይ የተጠቀሱትንና እነሱን የመሰሉትን ከስነጽሁፍ አይቆጥራቸውም፡፡

ስለስነጽሁፍ የተሰጡትን ሁለት የብያኔ አቅጣጫዎች ባጭሩ ተመልክተናል፡፡ ከነዚህ አቅጣጫዎች የእኛን ትኩረት የሚስበው ሁለተኛው ማለትም ስነጽሁፍን ለተወሰኑ የፈጠራ ስራዎች ብቻ የሚሰጥ በመሆኑ እሱን ዘርዘር አድርጎ መመልከት ይገባል፡፡ እዚህ ላይ ስነጽሁፍ ስንል “ከሁሉ አስቀድሞ በከያኒው የተፈጠረ ከያኒው የሚያበጀው የኪነጥበብ ስራ” መሆኑ መታወቅ አለበት፡፡ ይህ የፈጠራ ስራ የሰውን የተለያዩ ገጠመኞችና የኑሮ መልኮች ሊያሳይ የሚችል የሰዎች ሀሳብ መግለጫ ነው፡፡

*(ዘሪሁን አስፋው(1992) የስነጽሁፍ መሰረታውያን መጽሀፍ የተወሰደ)፡፡*

ክፍለጊዜ ስምንት

**ተግባር አምስት**

1. ወደቤተ መጻህፍት ጎራ ብላችሁ የተለያዩ ጽሁፎችን አንብቡና ስታነቡ ካጋጠማችሁ ጽሁፍ አንድ አንቀጽ መርጣችሁ በውስጡ ያሉትን መሸጋገሪያ ቃላት ለይታችሁ በማውጣት ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡
2. ከዚህ በታች በቀረቡት ቅደም ተከተሎች መሰረት መረጃ በማሰባሰብ የህይወት ታሪክ ጻፉ፡፡
   - በመጀመሪያ በህይወት ታሪክ ሊካተቱ የሚችሉ ጭብጦችን መሰረት በማድረግ ከአምስት የማያንሱ ጥያቄዎች አዘጋጁ፡፡
   - በመቀጠል ጥያቄዎቹን በአቅራቢያችሁ ለምታገኙት ጓደኞችሁ አቅርባችሁ መረጃ ሰብስቡ፡፡
   - በመጨረሻም መረጃዎቹን በአንቀጽ አደራጅታችሁ ለክፍል ተማሪዎች አንብቡ፡፡

ክፍለጊዜ ዘጠኝ

## ትምህርት አምስት፡ ቃላት

**ከዚህ በታች የቀረበው ማስታወሻና ጥያቄዎች የቃላት ችሎታችሁን እንድትጠቀሙ የሚረዱ ስለሆኑ መልመጃዎቹንና ተግባራቱን በተሰጣችሁ ትእዛዞች መሰረት መልስ ስጡ፡፡**

**ተግባር ስድስት**

1. ተዘውታሪ ቃላት የምንላቸው ምን አይነት ቃላት ናቸው?
2. በየቀኑ ከምትጠቀሚቸው ቃላት አስሩን በመጻፍ የጻፉችሁትን ከጓደኞችሁ ጋር በመለዋወጥ ተገማገሙ፡፡

**ማስታወሻ**

**ተዘውታሪ ቃላት**

**ተዘውታሪ ቃላት የሚባሉት በእለት ተእለት የቋንቋ አጠቃቀማችን ለተለያዩ አላማዎች የምንጠቀምባቸው ቃላት ናቸው፡፡ ለምሳሌ፡- አስተማሪ፣ ትምህርት ቤት፣ መጽሃፍ፣ ለሰላምታ የምንጠቀማቸው ቃላት ወዘተ. ይጠቀሳሉ፡፡**

**ክፍለጊዜ አስር**

**መልመጃ አራት**

ሀ. ከዚህ በታች ከቀረበው አንቀጽ አስር ተዘውታሪ ቃላት ለይታችሁ አውጡ፡፡

ለ. ከአስሩ ተዘውታሪ ቃላት ለአምስቱ ቀጥተኛ ፍች ስጡ፡፡

## ብልጧ ወፍ

አንዲት ወፍ በበረሃ ሰማይ ላይ ስትበር ብዙ ጊዜ ከመቆየቷ የተነሳ ውሃ ጠማት፡፡ ውሃ ለመጠጣት ስትፈልግ አንድ የውሃ እንስራ አየች፡፡ ወደ ውሃው እንስራ ተጠግታ ስትመለከት ውሃው ጎድሎ ስለነበር ለመጠጣት እንደምትቸገር ተገነዘበች፡፡ ከዚያም ውሃ የያዘውን እንስራ በድንጋይ ለመስበር ብትሞክር አልተሳካላትም፡፡ ጥቂት ካሰበች በኋላ ትናንሽ ጠጠሮችን እየለቀመች ወደ ውሃው እንስራ ውስጥ መጨመር ጀመረች፡፡ ቀስ በቀስ ውሃው ወደ እንስራው አፍ እየተጠጋ መጣ፡፡ ከዚያም ጠጥታ ጥሟን አረካች፡፡

ክፍለጊዜ አስራ አንድ

## ትምህርት ስድስት፡ ሰዋስው

**በዚህ የትምህርት ይዘት ስር ቃላትንና ሀረጋትን እንድትለዩ የሚያግዙ መልመጃዎችና ተግባራት ተካተዋል፡፡በመሆኑም ለቀረቡላችሁ ተግባራትና መልመጃዎች በትእዛዛቸው መሰረት ተገቢውን መልስ ስጡ፡፡**

### ተግባር ሰባት

1. የቃልንና የሀረግን ልዩነት አስረዱ፡፡
2. ሀረግ ከዓረፍተ ነገር የሚለይበትን በምሳሌ በማስደገፍ አሳዩ፡፡

**ማስታወሻ**

**ሀረግ**

ድምጾች ስርዓት ባለው መልኩ ተቀናጅተው ቃልን እንደሚፈጥሩ ሁሉ፣ ቃላትም ስርዓታዊ ቅንጅት በማድረግ ሀረግን ይመሰርታሉ፡፡ በመሆኑም ሀረግ ከቃል ከፍ ያለ ከዓረፍተነገር አነስ ያለ የቋንቋ መዋቅር ነው፡፡

በአማርኛ ቋንቋ አምስት አይነት የሀረግ ዐይነቶች አሉ፡፡ እነሱም፡

1. ስማዊ ሀረግ
2. ግሳዊ ሀረግ
3. ቅጽላዊ ሀረግ
4. ተውሳከግሳዊ ሀረግ
5. መስተዋድዳዊ ሀረግ ናቸው፡፡

ምሳሌ፡-

| ቃል | ሀረግ |
|---|---|
| ሀ. ቤት | ትልቅ ቤት |
| ለ. ሰበረ | ብርጭቆ ሰበረ |
| ሐ. አክባሪ | ሰው አክባሪ |
| መ. ገና | አሁን ገና |
| ሠ. እንደ | እንደ እህቱ |

**መልመጃ አምስት**

**ክፍለጊዜ አስራ ሁለት**

**ሀ. በ "ሀ" ስር ለተዘረዘሩ የሀረግ አይነቶች በ "ለ" ስር ከቀረቡት ምሳሌዎቻቸው ጋር አዛምዱ፡፡**

| "ሀ" | "ለ" |
|---|---|
| 1. ስማዊ ሀረግ | ሀ. በጣም ደግ |
| 2. ግሳዊ ሀረግ ናቸው፡፡ | ለ. ከወንድሙ ጋር |
| 3. ቅጽላዊ ሀረግ | ሐ. አሁን ቶሎ |
| 4. ተውሳከግሳዊ ሀረግ | መ. የቆዳ ጃኬት |
| 5. መስተዋድዳዊ ሀረግ | ሠ. መኪና ገዛ |

**ለ. ከዚህ በታች ቃላትና ሀረጋት ተዘርዝረዋል፡፡ በተዘጋጀው ሰንጠረዥ ውስጥ በየወገናቸው ለይታችሁ አስቀምጡ፡፡**

1. ደብተር
2. ከሸክላ የተሰራ ቤት
3. ሁለት በግ
4. አእዋፍ
5. ልበሙሉ
6. ሰዎች
7. መቼ ተከፈተ
8. የጠይም ቆንጆ
9. እንደ ወንድሙ ክፉኛ
10. ከእህቱ ጋር

| ቃል | ሀረግ |
|---|---|
| አእዋፍ | ከእህቱ ጋር |
| | |
| | |
| | |
| | |
| | |

**መልመጃ ስድስት**

**ሀ. ምሳሌውን መሰረት በማድረግ ከዚህ በታች ከቀረቡት ሀረጋትና ዐረፍተነገሮች በመምረጥ በትክክለኛው ቦታ አስገቡ፡፡**

1. ረጅም እንጨት
2. ሂካ በሬውን ሸጠው
3. ቀይ ሱሪ
4. አለማየሁ ከቤቱ ወጣ
5. አፊያ ፎጭ ነች፡፡
6. ጥሩ ልጅ
7. የልጅ አዋቂ

| ሀረግ | ዓረፍተ ነገር |
|---|---|
| ቀይ ሱሪ | ሂካ በሬውን ሸጠው |
| | |
| | |
| | |

# ምዕራፍ አምስት

# ውሃና ጠቀሜታው

## የሚጠበቁ ውጤቶች

**ከዚህ ምእራፍ ትምህርት በኋላ፡-**

- የቀረበላችሁን ምንባብ አዳምጣችሁ መልእክቱን ትናገራላችሁ፡፡
- ስለውሃ ጥቅም ትገልጻላችሁ፡፡
- ምንባብን በማድመጥ የምክንያትና ውጤትን ሀሳብ ትለያላችሁ፡፡
- ተራኪ ድርሰት ትጽፋላችሁ፡፡
- የቃላትን እማሬያዊ ፍች ትሰጣላችሁ፡፡
- ገቢርና ተገብሮ ዓረፍተነገሮችን ትለያላችሁ፡፡

ክፍለጊዜ አንድ

## ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

**በዚህ የትምህርት ይዘት የማዳመጥ ክሂላችሁን እንድትጠቀሙ የሚረዱ ጽሁፍ እና የመልመጃ ጥያቄዎች ቀርበውላችኋል፡፡ በመሆኑም ጽሁፉን በትኩረት በማዳመጥ ጥያቄዎቹን በተገቢው መንገድ ትሰራላችሁ፡፡**

### የውሃ ብክለት



## ቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች

ሀ. ከዚህ በታች የቀረቡትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ፡፡

1. ለሰው ልጅ ህይወት መሰረታዊ የሆኑ ነገሮችን ዘርዝሩ፡፡
2. ከላይ በቀረበው ምስል ሰዎቹ ምን እየሰሩ እንደሆነ ተናገሩ፡፡
3. በቀጣይ የምታዳምጡት ጉዳይ ስለምን እንደሆነ ገምቱ፡፡

## የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎች

1. በውሃ የተሸፈነው የመሬት ክፍል ምን ያህል ነው?
2. ቀጥሎ ያለው የጽሁፉ ታሪክ ስለምን ሊያወሳ እንደሚችል ገምቱ፡፡

ክፍለጊዜ ሁለት

## የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች

### መልመጃ አንድ

ሀ. ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቄዎች ያዳመጣችሁትን ጽሁፍ መሰረት በማድረግ በቃል መልስ ስጡ፡፡

1. “ውሃ ህይወት ነው” የተባለው በምን ምክንያት ነው?
2. ዋነኞቹ የውሃ ምንጮች እነማን ናቸው፡፡
3. ውሃ እንዲበከል የሚያደርጉ ምክንያቶችን ግለጹ፡፡
4. የውሃ ብክለት ታዳሽ ነው ሲባል ምን ማለት ነው?
5. ከውሃ መነሻ እና ከውሃ መነሻ ውጪ የሚከሰት የውሃ ብክለት ልዩነታቸውን አብራሩ፡፡
6. ሰዎች ንጹህ ውሃ መጠቀም እንዲችሉ ከመንግስትና ከህብረተሰቡ ምን ይጠበቃል ትላላችሁ?

ክፍለጊዜ ሶስት

## ትምህርት ሁለት፡ መናገር

ከዚህ በታች የቀረቡት ተግባራት የንግግር ክሂላችሁን እንድትጠቀሙበት ለማገዝ የቀረቡ ሲሆን ለተግባራቱ ተገቢውን መልስ ስጡ፡፡

### ተግባር አንድ

ከዚህ በታች በቀረቡት ሀሳቦች ላይ በጥልቀት በቡድናችሁ በመወያየት የደረሳችሁበትን ማጠቃለያ ለክፍል ተማሪዎች አቅርቡ፡፡

1. የእርሻ ማዳበሪያ እና የከባቢ አየር ኬሚካሎች የወራጅና የከርሰምድር ውሃን እንዴት ይበክላሉ?
2. ውሃን ማደስ አስቸጋሪ የሚያደርገው ምንድን ነው?
3. የእለት ተእለት የሰው ልጅ ስራዎች በአከባቢያችሁ በሚገኙ ወንዞችና የተለያዩ የውሃ ምንጮች ላይ የሚያደርሰውን አዎንታዊና አሉታዊ ተጽእኖዎች ግለጹ፡፡
4. እቤታችሁ ውሃ ያለአግባብ ስትጠቀሙ ወላጆቻችሁ ምን አይነት ስሜት እንደሚኖራቸው ለጓደኞቻችሁ አብራሩ፡፡

ክፍለጊዜ አራት

### ተግባር ሶስት

ከዚህ በታች የቀረቡት ርእሶች ስር ስለውሃ ጥቅም በቡድን በመወያየት በምሳሌው መሰረት ጻፉ፡፡

| ለንጽህና | ለመዝናኛ | ለትራንስፖርት | ለሀይል ማመንጫ |
|---|---|---|---|
| 1.ልብስ ለማጠብ | መዋኘት | በመርከብ መጓዝ | ለእህል ወፍጮ |
| 2. ………… | ………… | ………… | ………… |
| 3. ………… | ………… | ………… | ………… |
| 4. ………… | ………… | ………… | ………… |
| 5. ………… | ………… | ………… | ………… |

ክፍለጊዜ አምስት

# ትምህርት ሶስት፡ ማንበብ

**ከዚህ በታች የቀረበው ምንባብ እና መልመጃዎች የማንበብ ክሂላችሁን እንድትጠቀሙ የሚረዱ ናቸው፡፡ ስለዚህ በትኩረት በማንበብ ለቀረቡት ጥያቄዎች ተገቢውን መልስ ስጡ፡፡**

## ቅድመ ምንባብ ጥያቄዎች

**ሀ. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃል መልስ ስጡ፡፡**

1. ለቤት አገልግሎት የምትጠቀሙትን ውሃ የምታገኙት ከየት ነው?
2. የውሃ መበከል የሚያስከትላቸውን ችግሮች ለቡድናችሁ አባላት ግለጹ፡፡
3. ውሃ ወለድ፣ ውሃ ማከም፣ ውሃ ማጣራት ስለሚሉት ሀረጋት ፍቺ ምን እንደሆነ በቡድን ተነጋገሩበት፡፡

## አልማዝና የውሃ አጠቃቀሟ

የወይዘሮ አልማዝ ቤተሰብ በውሃ ወለድ በሽታዎች በተደጋጋሚ ይጠቃሉ፡፡ በዚህ ምክንያት ወይዘሮ አልማዝ ምግቦችንና የመጠጥ ውሃን በንፅህና ለመያዝ ብትሞክርም የቤተሰቦቿ ጤንነት ሊሻሻል ባለመቻሉ ችግሩ የተከሰተው በውሃ ብክለት እንደሆነ ጠረጠረች፡፡ ጥርጣሬዋ እየጨመረ ሲመጣ ለቤት አገልግሎት የምትጠቀመውን የወንዝ ውሃ በብርጭቆ እየቀዳች ማስተዋል ጀመረች። በብርጭቆው ውስጥ ከሥር እየዘቀጠ የሚቀረው ቆሻሻ ጥርጣሬዋን አባባሰው። ከዚህም የተነሳ ለሀኪም መንገር እንዳለባት ወሰነች። ከዚያም ወደጤና ተቋም ሄዳ ለመጠጥ የምትጠቀመው የወንዝ ውሃ እንደሆነ ለሀኪሙ ተናገረች፡፡ ሀኪሙም ውሃ በሕይወት ለመኖር አስፈላጊ ቢሆንም ንፅህናው ካልተጠበቀ ለከፍተኛ ሕመም እንደሚያጋልጥ አስረዳት።

በመቀጠልም «የተገኘው ውሃ ሁሉ ለመጠጥ ሊሆን አይችልም። ስለዚህ ከተለያዩ ምንጮች የሚገኝ ውሃ ተጣርቶና ታክሞ ለመጠጥ መዋል ይኖርበታል። የቧንቧ ውሃም ቢሆን በአጋጣሚ ቧንቧው ተሰብሮ ወይም ተበላሽቶ ሊበከል ስለሚችል አፍልቶ መጠቀም ያስፈልጋል» በማለት መከራት።

## የንባብ ጊዜ ጥያቄዎች

1. በአንደኛው አንቀጽ ውስጥ ያገኛችሁትን ፍሬ ሀሳብ በማስታወሻ ደብተራችሁ መዝግቡ፡፡
2. የወይዘሮ አልማዝ ቤተሰቦች በተደጋጋሚ ጊዜ የሚጠቁት በምንድን ነው?

ወይዘሮ አልማዝ ሐኪሙ የመከሯትን በመቀበል በመጀመሪያ የሚጠጣና የማይጠጣ ውሃ መኖሩን ተገነዘበች። በዚህም መሰረት በሻሽ ውሃን የማጣራት ዘዴን ጥቅም ላይ አዋለች፡፡ ዘዴውም በሚከተሉት ሂደቶች ውስጥ ያልፋል፡፡ በመጀመሪያ ከወንዝ የቀዳችውን ውሃ በሻሽ ታጠላለች፤ በመቀጠል ውሃውን እየተንተከተከ እንፋሎት እስኪወጣው ድረስ ታፈላዋለች። ከዚያም ሲቀዘቅዝ በእንሥራ ትገለብጥና መልሶ እንዳይበከል ትከድነዋለች። በመጨረሻም ለመጠጣት ሲፈለግ በንፁህ ጣሳ ወይም ብርጭቆ በመቅዳት ቤተሰቦቿ ለመጠጥ እንዲጠቀሙበት ታደርጋለች። ይህን ተግባር ለተከታታይ ሳምንታት ተጠቀመች።

ወይዘሮ አልማዝ ለሁሉም የቤተሰቡ አባላት ውሃን አፍልቶ ከማጠጣት በተጨማሪ ሌላ ዘዴ መጠቀም አሰበች። ስለጉዳዩ የአካባቢ ሰዎችን ስታማክር የውሃ ማከሚያ መድኃኒቶችን መጠቀም አማራጭ እንደሆነ ነገሯት። የውሃ ማከሚያ መድኃኒት የሚጠጣ ውሃ ለማጣራት የሚያገለግል

መሆኑን ተገንዝባ መጠቀም ጀመረች። ድካሟንም ቀነሰላት። በመጨረሻም ወይዘሮ አልማዝ የሀኪሙንና የአካባቢውን ኗሪዎች ምክር ተቀብላ ንፁህ ውሃ መጠቀም ቻለች። ከወንዝ የምትቀዳውንም ውሃ በሻሽ አጣርታ በማፍላት ወይም የውሃ ማከሚያ መድኃኒት በመጨመር መጠቀም የዘወትር ልምዷ አደረገች፡፡ የልጆቿም ጤንነት ቀስበቀስ መሻሻል አሣየ።

*(የኢ.ፌ.ድ.ሪ ትምህርት ሚኒስቴርና የኦሮሚያ ትምርት ቢሮ፡፡2007፡፡ ለአማርኛ ቋንቋ ማስተማሪያ የተዘጋጀ መጽሀፍ ተሻሽሎ የቀረበ)*

## አንብቦ መረዳት ጥያቄዎች

**ከዚህ በታች የቀረቡት ጥያቄዎች የአንብቦ መረዳት ክሂልህ/ሽን ለማዳበር የሚረዱ ናቸው፡፡ለጥያቄዎቹ ተገቢውን መልስ ስጥ/ጭ፡፡**

**መልመጃ ሁለት**

**ሀ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች በጽሁፍ መልስ ስጡ፡፡**

1. የውሃ ወለድ በሽታዎች ምን ምን ሊሆኑ ይችላሉ?
2. የውሃ ንጽህና ለመጠበቅ ይረዳል የምትሉትን ዘዴ ዘርዝሩ፡፡
3. ውሃ ወለድ ማለት ምን ማለት ነው?
4. በአከባቢያችሁ ውሃን ለማከም ህብረተሰቡ የሚጠቀምበት ዘዴ ዘርዝሩ፡፡

**ለ. ወይዘሮ አልማዝ የተጠቀመችውን በሻሽ ውሃ የማጣራት ሂደት ቅደም ተከተል አስተካክላችሁ በቃል ተናገሩ፡፡**

1. ለመጠጣት ሲፈለግ በንፁህ ጣሳ ወይም ብርጭቆ በመቅዳት ቤተሰቦቿ ለመጠጥ እንዲጠቀሙበት ታደርጋለች።
2. ከወንዝ የቀዳችውን ውሃ በሻሽ ታጠላለች፤
3. ሲቀዘቅዝ በእንሥራ ትገለብጥና መልሶ እንዳይበከል ትከድነዋለች።

4. ይህን ተግባር ለተከታታይ ሳምንታት ተጠቀመች።
5. ውሃውን እየተንተከተከ እንፋሎት እስኪወጣው ድረስ ታፈላዋለች።

ክፍለጊዜ ስድስት

## ትምህርት አራት፡መጻፍ

ከዚህ በታች የቀረበው ማስታወሻና ተግባር የጽሁፍ ክሂላችሁን እንድት ጠቀሙበት የሚረዳ ሲሆን ማስታወሻውን በትኩረት በማንበብ ተግባሩን በትእዛዙ መሰረት ስሩ፡፡

**ማስታወሻ**

**ተራኪ ድርሰት**

ስላለፈ ድርጊት የሚተርክ ወይንም የሚያትት ጽሁፍ ተራኪ ድርሰት ይባላል፡፡ ለዚህ ምሳሌ ሊሆን የሚችል አንቀፅ ከዚህ በታች ቀርቧል፡፡

ምሳሌ፡

በምስራቅ ወለጋ ዞን በአርጆ ወረዳ በ1932 ዓ.ም የተወለደው ሃይሌ ፊዳ የማያልቅ ትዕግስት ያለው ሰው አድማጭ ነው፡፡ ሊያስቆጣ ወይም ስሜትን ሊነካ የሚችል የግል ጉዳይን እንኳ በበጎ የሚያይ ሰው ነበር፡፡ ሃይለቃልና ቁጣ የራቁት ሰው ነው፡፡ ከዚህም ሌላ ሃይሌ ሁልጊዜ ጠያቂ ሠው ነው፤ በትምህርቱ ከልጅነት ጀምሮ ጎበዝ ነበር፡፡ 8ኛ ክፍል ብሄራዊ ፈተና ወስዶ፣ በአገር አቀፍ ደረጃ አንደኛ ወጥቶ በማዕረግ ወደ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ተሸጋገረ። ስብዕናውም ሙሉ የነበረ ሰው ነው፡፡ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን ጄነራል ዊንጌት ትምህርትቤት ተምሯል፡፡ አብረውት የተማሩና የቅርብ ጓደኞቹ እንደሚናገሩት ከሆነ፤ ሁሉም ሠው ሊወዳጀው የሚጓጓለት፣ ጨዋና አስተዋይ ነበር፡፡ በዚህ ላይ በኢትዮጵያ ጉዳይ ገና በለጋነቱ ማሰብ የጀመረ ሰው ነው፡፡ የአለም የፖለቲካ ሃሣቦችን መመርመር የጀመረው ገና የሁለተኛ ደረጃ ተማሪ እያለ ነው፡፡ 12ኛ ክፍልን የጨረሰው በከፍተኛ ነጥብና ማዕረግ ነበር፡፡ ዩኒቨርሲቲም ገብቶ፣ በልዩ ማዕረግ አጠናቀቀ፡፡

*(አዲስ አድማስ ጋዜጣ፡፡2010፡፡ አዲስ አበባ፡፡ ለክፍል ደረጃው እንዲመች ተሻሽሎ የቀረበ)*

**ተግባር አራት**

1. ከላይ የቀረበውን የተራኪ ድርሰት ምሳሌ መሰረት በማድረግ ከታዋቂ አትሌቶቻችን የአንዳቸውን ታሪክ ከተለያዩ መረጃ ምንጮች በማሰባሰብ ባለሁለት አንቀጽ ተራኪ ድርሰት ጽፋችሁ እርስበርስ በመለዋወጥ አርሙ፡፡
2. ቤተመጽሃፍት በመሄድ በተራኪ ድርሰት አጻጻፍ የተጻፉ ድርሰቶችን በመለየት ወደክፍል በማምጣት ለክፍል ጓደኞቻችሁ አንብቡላቸው፡፡

**ክፍለጊዜ ሰባት**

## ትምህርት አምስት፡ ቃላት

**ከዚህ በታች የቀረቡት ማስታወሻ፣ ተግባርና የመልመጃ ጥያቄዎች በተለያዩ ቃላት እንድትጠቀሙ የሚያግዙ ናቸው፡፡ ስለዚህ ማስታወሻውን በትኩረት በማንበብ ለጥያቄዎቹ በጽሁፍ ተገቢውን መልስ ስጡ፡፡**

**ተግባር አምስት**

ለቃላት ብዙ ጊዜ የሚሰጠው ትርጉም ቀጥተኛ ነው፡፡ አልፎ አልፎ ሰዎች የቃላትን ተደራቢ ፍቺ ሲጠቀሙ ይስተዋላል፡፡ ለምሳሌ አንበሳ የሚለውን ቃል ሀይለኛ፣ ጀግና፣ ጎበዝ ሰው ለማለት ይጠቀሙበታል፡፡ እንዲህ አይነቱ ተግባር አጋጥሟችሁ ከሆነ በምሳሌ በማስደገፍ ለመምህራችሁ በጽሁፍ አቅርቡ፡፡

### ማስታወሻ

**እማሬያዊ ፍቺ**

ቃላት እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍች ሊኖራቸው ይችላል፡፡ የቃላት እማሬያዊ ፍች የሚባለው የቃላቱ የመዝገበ ቃላት ወይም ቀጥተኛ ፍቺን የሚያመለክት ነው፡፡

ለምሳሌ፡ ቤት ለሚለው እማሬያዊ ፍቺው ለሰውልጅ መኖሪያ የሚያገለግል ከእንጨት፣ ከሸክላ ድንጋይ፣ ከብሎኬት…ወዘተ ሊሰራ የሚችል በማለት ፍችውን መስጠት ይቻላል፡፡

**መልመጃ ሶስት**

**ሀ. ለሚከተሉት ቃላት መዝገበቃላትን በመጠቀም በጽሁፍ እማሬያዊ ፍቺ ስጡ፡፡**

ምሳሌ፡ ምስጥ ጉንዳን የምትመስል፣ ከመሬት ውስጥ አፈር ወደ ውጪ የምትቆልል ቀላ ያለች ነፍሳት ናት፡፡

1. ምስጥ
2. ቋንጣ
3. ኤሊ
4. ጅብ
5. ድንጋይ
6. ንብ
7. ተርብ
8. በግ
9. እባብ
10. እርግብ

ክፍለጊዜ ስምንት

## ትምህርት ስድስት፡ ሰዋስው

**ቀጥለው የቀረቡት ማስታወሻ፣ ተግባርና የመልመጃ ጥያቄዎች የሰዋስው እውቀታችሁን ለመጠቀም የሚያግዙ ስለሆኑ ለተግባራቱ እና ለመልመጃ ጥያቄዎች ተገቢውን መልስ በጽሁፍ ስጡ፡፡**

## ማስታወሻ

### ገቢር ዓረፍተ ነገር

ገቢር ዓረፍተ ነገር የአረፍተ ነገሩ ባለቤት ድርጊት ፈጻሚ የሚሆንበት የዓረፍተ ነገር አይነት ነው፡፡

ምሳሌ፡ ሀ. ልጁ ዶሮውን አረደው፡፡

ለ. ደሚቱ ብርጭቆ ሰበረች፡፡

## ተግባር ስድስት

**በሳጥኑ ውስጥ የቀረቡትን ግሶች በመጠቀም አምስት ገቢር ዓረፍተ ነገሮች ጽፋችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡**

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ጠረገ | ጻፈ | አነበበ | ወሰደ | አከመ |

ምሳሌ፡ ጫልቱ ቤቱን ጠረገች፡፡

## መልመጃ አራት

**ሀ. ከዚህ በታች በቀረቡት ዓረፍተነገሮች ውስጥ ተዘበራርቀው የተቀመጡትን ቃላት አስተካክላችሁ ገቢር አረፍተ ነገር መስርቱ፡፡**

1. ጭድ ሲፈን ሰጠች ለበሬው፡፡
2. በፍጥነት መኪናውን ደስታ ነዳ፡፡
3. ቡና ወቀጠ ቶለሳ፡፡
4. ሰውነት ሊጋ ኳሱን፡፡

**ክፍለጊዜ ዘጠኝ**

**ማስታወሻ**

**ተገብሮ ዓረፍተ ነገር**

ተገብሮ ዓረፍት ነገር የአረፍት ነገሩ ባለቤት ድርጊት ሲፈጸምበት የሚያመለክት የዓረፍት ነገር አይነት ነው፡፡

ምሳሌ፡- ሀ. በሬው ተሸጠ፡፡

ለ. መስታወቱ ተሰበረ፡፡

## ተግባር ሰባት

**በሳጥኑ ውስጥ የቀረቡትን ግሶች በመጠቀም አምስት ተገብሮ ዓረፍት ነገር ጽፋችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡**

ተጠረገ ተጻፈ ተነበበ ተወሰደ ታከመ

ምሳሌ፡ ቤቱ ተጠረገ፡፡

## መልመጃ አምስት

**አምስት ገቢር እና አምስት ተገብሮ ዓረፍተ ነገሮች መስርቱ፡፡**

ምሳሌ፡ ተገብሮ ዓረፍተነገር፡ ውሃው ተደፋ፡፡

ገቢር ዓረፍተነገር፡ ቤካ መጽሀፍ ገዛ፡፡

# ምእራፍ ስድስት

# የሰዎች ዝውውር

## የሚጠበቁ ውጤቶች

**ከዚህ ምእራፍ ትምህርት በኋላ ፡-**

- ምንባቦችን በማዳመጥ ዋና ዋና ነጥቦችን ትለያላችሁ፡፡
- የሰዎች ዝውውር ጽንሰሀሳብ ምንነት ትገልጻላችሁ፡፡
- በራሳችሁ በመተማመን ከጓደኞቻችሁ ጋር ትነጋገራላችሁ፡፡
- የገላጭ ድርሰትን መዋቅር ትመረምራላችሁ፡፡
- የቃላትን ፍካሬያዊ ፍች መለየትና ፍችያቸውን ትበይናላችሁ፡፡
- ዓረፍተ ነገሮችን ከአገልግሎታቸው አንጻር ትለያላችሁ፡፡

**ክፍለጊዜ አንድ**

## ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

**በቀጣይ አዳምጣችሁ እንድትረዱ የሚያግዛችሁ ጽሁፍ እና የመልመጃ ጥያቄዎች ቀርበውላችኋል፡፡ በመሆኑም ጽሁፉን በትኩረት በማዳመጥ ጥያቄዎቹን በተገቢው መንገድ ትሰራላችሁ፡፡**



# ሰሚራ

**ከዚህ በታች የቀረቡት ጥያቄዎች የአዳምጦ መረዳት ክሂላችሁን እንድትጠቀሙ የሚያግዙ ስለሆኑ ለጥያቄዎቹ በቃል ተገቢውን መልስ ስጡ፡፡**

## ቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች

**ለሚከተሉት ጥያቄዎች ለክፍል ተማሪዎች በቃል መልስ ስጡ፡፡**

1. ምስሉንና ርእሱን ተመልክታችሁ በቀጣይ ስለምን እንደምታዳምጡ ተናገሩ፡፡
2. ከአከባቢያችሁ የተሻለ ኑሮ ፍለጋ ወደ ውጭ ሀገር ስለተሰደዱ ሰዎች የምታውቁትን ለጓደኞቻችሁ ተናገሩ፡፡
3. ከላይ ስለቀረበው ምስል የተረዳችሁትን ያህል ለመምህራችሁ ተናገሩ፡፡

## የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎች

1. ከሚቀርብላችሁ ጽሁፍ አዳዲስ ቃላትን በማስታወሻ ደብተራችሁ መዝግቡ
2. በመጀመሪያው አንቀጽ ውስጥ የተላለፈው መልእክት ምን እንደሆነ ግለጹ፡፡
3. በቀጣይ በሚቀርብላችሁ ጽሁፍ ውስጥ ሰሚራን ምን ያጋጥማታል ብላችሁ ታስባላችሁ?

## የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች

**መልመጃ አንድ**

**ለሚከተሉት ጥያቄዎች ያዳመጣችሁትን ጽሁፍ መሰረት በማድረግ በቃል መልሱ፡፡**

1. ሰሚራ ወደማታውቀው ሀገር እንድትሄድ ያነሳሳት ምንድን ነው?
2. ጣሰው ሰሚራን ከትምህርቷ አቋርጣ እንድትሄድ ማድረጉ ተገቢ ነው ትላላችሁ? ለምን?
3. የሰሚራ የውጭ ሀገር ጉዞ ህልሟ ምን እንደሚመስል ተናገሩ፡፡
4. ስለሰሚራ ያዳመጣችሁትን ሀሳብ ጠቅለል አድርጋችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ፡፡
5. ጣሰው መቀጣቱ ተገቢ ነው ትላላችሁ? ለምን?

ክፍለጊዜ ሁለት

## ትምህርት ሁለት፡ መናገር

**ከዚህ በታች የቀረቡት ተግባራት የንግግር ክሂላችሁን እንድትጠቀሙበት ለማገዝ የቀረቡ ሲሆን ለተግባራቱ ተገቢውን መልስ ስጡ፡፡**

### ተግባር አንድ

1. ወጣቶች በህገወጥ ደላሎች በመታለል ትምህርታቸውን አቋርጠው ከመሰደድ እንዲቆጠቡ መፍትሄ ይሆናል ብላችሁ የምታስቡትን በቡድን ተወያዩ፡፡ ሀሳባችሁንም በተወካያችሁ አማካይነት ለመምህራችሁ ተናገሩ፡፡
2. ወላጆች ወይም አሳዳጊዎች ልጆቻቸው በህገወጥ መንገድ እንዳይሰደዱ ማድረግ ያለባቸውን መፍትሄዎች ጥንድ ጥንድ በመሆን ተወያዩና ለክፍል ተማሪዎች አቅርቡ፡፡

ክፍለጊዜ ሶስት

# ትምህርት ሶስት፡ ምንባብ

**ከዚህ በታች የቀረቡት ምንባብ እና የመልመጃ ጥያቄዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታችሁን እንድትጠቀሙ የሚረዱ ሲሆን የተዘጋጀውን ምንባብ በትኩረት በማንበብ ተገቢውን መልስ ስጡ፡፡**

## ቅድመምንባብ ጥያቄዎች

**ሀ. ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቄዎች  በቃል መልስ ስጡ፡፡**

1. ህገወጥ የሰዎች ዝውውር አስከፊነትን ግለጹ፡፡
2. ህገወጥ የሰዎች ዝውውር ወንጀል ስለመሆኑ ያላችሁን መረጃ ተናገሩ፡፡
3. በህገወጥ የሰዎች ዝውውር በጣም ተጎጂ የሆኑት የማህበረሰብ ክፍሎች እነማን ናቸው?

## ሕገወጥ የሰዎች ዝውውር

ሕገወጥ የሰዎች ዝውውር አስከፊ ገጽታ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት እ.ኤ.ኤ. በ2000 ያወጣውና "የፓሌርሞ" ስምምነት በመባል የሚታወቀው ስምምነት ሕገወጥ የሰዎች ዝውውር ለብዝበዛ ዓላማ ሰዎችን በተለይም ሴቶችና ሕፃናትን በኃይል፣ በዛቻ፣ በተንኮል፣ በማታለል፣ በመጥለፍ ወይም በተበዳይ ላይ ኃላፊነት ላለው ሰው ገንዘብ ወይም ሌላ ጥቅም በመስጠት መመልመል፣ ማጓጓዝ፣ ማስተላለፍ፣ መደበቅ ወይም መቀበል ማለት እንደሆነ ይገልፃል፡፡ ሕፃናትን መመልመል፣ ማጓጓዝ፣ ማስተላለፍ፣ መደበቅ ወይም መቀበል በራሱ በሰዎች መነገድ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ በሴቶችና በልጆች መነገድን የሚከለክለው የኢትዮጵያ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 597 እና 635 ላይም ይኸው ትርጉም

ተቀምጧል:: ከዚህ ትርጓሜ መረዳት እንደምንችለው፣ በሰዎች መነገድ በዋናነት ሦስት ነገሮችን ያጠቃልላል:: እነዚህም: በኃይል ወይም በማታለል መመልመል፣ በሀገር ውስጥ ወይም ወደ ሌላ ሀገር በህጋዊ ወይም በህገወጥ መንገድ ማዘዋወር፣ እና አዘዋዋሪዎች ተበዳዮችን የገንዘብ ጥቅም ማግኛ ማድረጋቸው ብዝበዛ ናቸው::

ሰዎች በህገወጥ ዝውውር ምክንያት ለተለያዩ ጉዳቶች ይጋለጣሉ:: ለምሳሌ ኢ-መደበኛ በሆኑ ንግድ መስመሮች የሚደረግ አደገኛ ጉዞ፣ በአዘዋዋሪዎች የሚደርስ ጥቃትና ብዝበዛ፣ በመዳረሻ አገራት የሚያጋጥም አስከፊ የሥራ ሁኔታዎች ይጠቀሳሉ:: እነዚህም ተደማምረው በተጠቂዎች ላይ ዘለቄታዊ የአካል፣ የአእምሮ እና ማህበራዊ ቀውስ ያሳድራሉ:: ከዚህም በላይ የህገወጥ ዝውውር ተጠቂዎች በግል ህይወታቸው፣በማህበራዊ ህይወታቸው እና በኢኮኖሚያቸው ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ይፈጥራል::

## የምንባብ ጊዜ ጥያቄዎች

1. ምንባቡን እያነበባችሁ ቁልፍ ቃላትን መዝግቡ::
2. ከመጀመሪያው አንቀጽ ስለህገወጥ የሰዎች ዝውውር ምን ተገነዘባችሁ?
3. ቀጥሎ የሚመጣው ምንባብ ስለምን የሚያወሳ ይመስላችኋል?

ከግል ሕይወት አኳያ የሕገወጥ ዝውውር ሰለባ የሆኑ ሰዎች የወጣትነት ጊዜያቸውን ከቤተሰቦቻቸውና ከማህበረሰቡ ርቀው በአስከፊ ሁኔታ እንዲያሳልፉ ያደርጋል:: በመሆኑም የተሟላ ስብእና ለመገንባት የሚችሉበት ጊዜ ይባክናል:: ይህም ከሚደርስባቸው ብዝበዛና ጥቃት ጋር ተደማምሮ ለተለያዩ የስነልቦና ችግሮች ያጋልጣቸዋል:: ከዚያም አልፎ የወንጀል ድርጊት ተሳታፊ እና ተጠቂ የመሆን እድላቸውን ያሰፋዋል::

ከማኅበራዊ ሕይወት አንፃር ደግሞ ሕገወጥ የሰዎች ዝውውር ተጠቂዎችን ከመደበኛው ማህበራዊ ምህዳራቸው በመነጠል ማኅበራዊ ሕይወታቸውን የማዛባት እንዲሁም ከማኅበራዊ ድጋፍ በማራቅ ይበልጥ ተጋላጭ እንዲሆኑ የማድረግ ውጤት አለው፡፡ በተለይም ተጠቂዎች የሚኖሩበት ሁኔታ ከለመዱት በእጅጉ የተለየ ሲሆንና መሰረታዊ እምነታቸውን ጥያቄ ውስጥ የሚያስገባ ድርጊት እንዲፈፅሙ ወይም ባልተለመደ ማህበራዊ ሂደት ውስጥ እንዲሳተፉ ሲገደዱ (ለምሳሌ የቀጣሪዎቻቸውን እምነት እንዲከተሉ ሲገደዱ) ችግሩ የባሰ ይሆናል፡፡ እንዲህ ዓይነቱ ማህበራዊ መገለልና ጫና በተጠቂዎች ላይ ዘላቂ ችግር በማድረስ ወደ ማኅበረሰባቸው ሲመለሱ በቀላሉ መቀላቀል እንዳይችሉና ገለልተኛ ሆነው እንዲቀጥሉ ያደርጋቸዋል፡፡

ከኢኮኖሚ አንጻር ደግሞ ሕገወጥ ደላሎች የሚጠይቁትና በማታለልም ሆነ በግድ የሚወስዱት ገንዘብ ከፍተኛ በመሆኑ የተጠቂዎች ቤተሰቦች ለከፍተኛ እዳ ይዳረጋሉ፡፡ ከዚያም አልፎ ብዙውን ጊዜ ደመወዛቸውን በጊዜውና ሳይቀናነስ የማግኘት እድል ስለማይኖራቸው በተመለሱ ጊዜ ለደረሰባቸው ስቃይ ማካካሻ ሊሆን የሚችል ገንዘብ አይኖራቸውም፡፡ የተለያዩ ጥናቶች እንዳሳዩት የአእምሮ መታወክ፣ አካላዊ ጉዳት እና ሞት በተጠቂዎች ላይ በተደጋጋሚ ይደርሳሉ፡፡ ተጠቂዎች እጃቸውና እግራቸው ተሰብሮ ወይም ባልታወቀ ምክንያት ሞተው ሬሳቸው የሚመጣበት አጋጣሚ በተደጋጋሚ ተከስቷል፡፡ ሕገወጥ የሰዎች ዝውውር ከግል ተበዳዮች አልፎ በሚኖሩበት ማኅበረሰብም ላይ ከፍተኛ ኤኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳት ያደርሳል፡፡ ችግሩ በአፋጣኝ ካልተፈታም ሙስና እና ንቅዘት እንዲስፋፋ ብሎም መንግስት የሕዝብን አመኔታ እንዲያጣ ሊያደርግ ይችላል፡፡

*(ጌታቸው ምትኩ "በሰዎች መነገድ/ ሕገወጥ የሰዎች ዝውውር ምንድነው?" ለንባብ እንዲመች ተደርጎ የተዘጋጀ፡፡)*

ክፍለጊዜ አራት

## የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች

### መልመጃ ሁለት

**ሀ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ምንባቡን መሰረት በማድረግ በጽሁፍ መልስ ስጡ፡፡**

1. “የፓሌርሞ”ን ስምምነት ጭብጥ ግለጹ?
2. የኢትዮጵያ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 597 እና 635 ስለምን ያብራራል?
3. ሰዎች በህገወጥ ዝውውር ምክንያት እንዴት ላሉ ጉዳቶች ይጋለጣሉ?
4. የህገወጥ ዝውውር ተጠቂዎች በግል ህይወታቸው፣ በማህበራዊ ህይወታቸው እና በኢኮኖሚያቸው ላይ ምን አይነት አሉታዊ ተጽእኖ ይደርስባቸዋል?
5. በአንቀጽ ሁለት “እነዚህም ተደማምረው…” በሚል የቀረበው ሀረግ ምን ያመለክታል?

**ለ. ለሚከተሉት ቃላት ምንባቡን መሰረት በማድረግ ፍች ስጡ፡፡**

1. ህገወጥ
2. ሙስና
3. ንቅዘት
4. መመልመል
5. ወንጀል
6. ምህዳር
7. ተበዳይ
8. መዳረሻ
9. መገለል
10. ማዛባት

ክፍለጊዜ አምስት

## ትምህርት አራት፡ መጻፍ

**የሚከተሉት ማስተወሻና ተግባር በተለያዩ ጉዳዮች ዙሪያ እንድትጽፉ የሚረዷችሁ ናቸው፡፡ በመሆኑም ማስታወሻውን መሰረት በማድረግ ከስሩ የቀረበውን ተግባር አከናውኑ፡፡**

### ማስታወሻ

**ገላጭ ድርሰት**

**አንድ ነገር እንዴት እንደሚሰራ ወይንም እንደሚፈጸም የሚያመለክት ወይንም የሚመራ ድርሰት ገላጭ ድርሰት በመባል ይታወቃል፡፡**

**ምሳሌ፡ ነፋስ በአይን የማይታይ፣ በእጅ የማይዳሰስ ሲነፍስ ስሜቱ ለፍጥረት ሁሉ የሚስማማ ነው፡፡ ይህ በራሪ አየር ተለቶ ከሚታወቀው አየር ከኩሬና ከሀይቅ፣ ከባህርና ፈሳሽ፣ በጸሀይ ሀይል ተነስቶ በአየር ውስጥ ከሚዛወረው እንፋሎት፣ ከአትክልት ርግፍጋፊ፣ ከአቧራ በአየር ውስጥ ከሚገኙት ከጥቃቅን ነገሮችና ተባዮች ይመሰረታል፡፡**

### ተግባር ሁለት

ከላይ የቀረበላችሁን ገላጭ ድርሰት ማስታወሻና ምሳሌ መሰረት በማድረግ ከዚህ በታች ከቀረቡት ርእሶች መካከል አንዱን በመምረጥ በገላጭ ድርሰት ሁለት አንቀጽ ጻፉ፡፡

1. ከሳውዲ አረቢያ ተመላሽ ስደተኞችን ማቋቋም
2. በስደት ጊዜ በሴቶች ላይ የሚደርሰውን ጾታዊ ጥቃት መቀነስ
3. ህገወጥ ደላሎችን አጋልጦ ለህግ በማቅረብ ላይ የሚታዩ ችግሮች

**ክፍለጊዜ ስድስት**

## ትምህርት አምስት፡ ቃላት

**በዚህ ትምህርት ስር ለቃላት እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍች በተመለከተ ማስታወሻና መልመጃዎች ቀርበውላችኋል፡፡ ለቀረቡት መልመጃዎች ና ተግባር ተገቢውን መልስ ትሰጣላችሁ፡፡**

**ማስታወሻ**

**የቃላት ፍካሬያዊ ፍቺ**

**ቃላት ከመዝገበ ቃላት ወይም ከቀጥተኛ ትርጉም ባሻገር የሚሰጡት ፍቺ የቃላት ፍካሬያዊ ፍች ይባላል፡፡**

ምሳሌ፡- ሀ. ወንበር

1. የተቀመጥኩበት **ወንበር** አዲስ ነው፡፡

   ለመቀመጫነት የሚያገለግል (እማሬያዊ ፍች)

2. ወይዘሮ ማዘንጊያ የፖለቲካ **ወንበር** ያዙ፡፡

   ወንበር- ስልጣን አገኙ

**መልመጃ ሶስት**

**ሀ. የሚከተሉትን ቃላት በቀረበው ምሳሌ መሰረት ፍካሬያዊ ፍቺ እንዲሰጡ በማድረግ አረፍተነገር መስርቱ፡፡**

ምሳሌ፡ እሱ <u>ምስጥ</u> ነው፡፡

(ፍካሬያዊ ፍቺ፡ መሰሪ ማለት ነው፡፡)

1. ምስጥ
2. ቋንጣ
3. ኤሊ
4. ጅብ
5. ድንጋይ
6. ንብ
7. ተርብ
8. በግ
9. እባብ
10. እርግብ

ክፍለጊዜ ሰባት

**መልመጃ አራት**

**ሀ. ከዚህ በታች ለቀረቡት ቃላት እማሬያዊ ፍችና ፍካሬያዊ ፍች ስጡ፡፡**

1. ምስጥ
2. ቋንጣ
3. ኤሊ
4. ጅብ
5. ድንጋይ
6. ንብ
7. ተርብ
8. በግ
9. እባብ
10. እርግብ

**ተግባር አራት**

ሀ. ከላይ በቀረበው ትምህርት መሰረት ለእማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍቺ ምሳሌ ሊሆኑ የሚችሉ አስር ቃላትን ጽፋችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡

ለ. በ "ሀ" ስር የጻፋችኋቸውን ቃላት ፍካሬያዊ ፍቺ እንዲሰጡ አድርጋችሁ አረፍተነገር መስርቱ፡፡

ክፍለጊዜ ስምንት

# ትምህርት ስድስት፡ ሰዋስው

**ስለአረፍተነገር አገልግሎት የሚያወሳውን ማስታወሻ አንብባችሁ ከስሩ የቀረቡትን ጥያቄዎች በጽሁፍ መልስ ስጡ፡፡**

## ማስታወሻ

### የአረፍተነገር አገልግሎት

ዓረፍተነገሮች ከአገልግሎታቸው አንጻር በአራት ዓይነት ይከፈላሉ።

እነሱም፡- ሀ. ሀተታዊ ዓረፍተ ነገር

ለ.ጥያቄያዊ ዓረፍተ ነገር

ሐ. አጋኗዊ ዓረፍተ ነገር

መ. ትእዛዛዊ ዓረፍተ ነገር

1. **ሀተታዊ ዓረፍተነገር፡** እውናዊ መረጃ ወይም ሃሳብ የሚገለጽባቸው ዓረፍተነገሮች ናቸው። ሀተታዊ ዓረፍተነገር በአዎንታዊና አሉታዊ መልኩ ሊቀርብ ይችላል፡፡

ምሳሌ፡ ሀ. ሀተታዊ ዓረፍተ ነገር

1.ዛሬ በጣም ደክሞኛል።

2. ታደሰ ወደቤቱ ሄደ፡፡

ለ. አሉታዊ ዓረፍተ ነገር

1. ሳምራዊት ወደትምህርት ቤት አልሄደችም።

2. አህመድ ከአዳማ አልመጣም፡፡

2 **ጥያቄያዊ ዓረፍተነገር፡** ሁልጊዜ ጥያቄ ይጠይቃል። በአረፍተነገሩ መጨረሻም ጥያቄ ምልክት ይኖረዋል። ጥያቄያዊ ዓረፍተነገር ምን ጊዜም መልስ ይሻል፡፡ መልሱ አጭር ወይም ረጅም ሊሆን ይችላል፡፡

ምሳሌ፡- ሀ. ለምን ቁርስህን አልበላህም?

ለ. የቡድን ሥራችሁን አጠናቀቃችሁ?

**መልመጃ አምስት**

ሀ. በሚከተለው ሰንጠረዥ ውስጥ ሶስት አዎንታዊ እና አሉታዊ ዓረፍተ ነገሮች መስርቱ፡፡

| አዎንታዊ ዓረፍተ ነገር | አሉታዊ ዓረፍተ ነገር | ጥያቄያዊ ዓረፍተነገር |
|---|---|---|
| ቢ.ፍቱ የሮባ እህት ነች፡፡ | ቢ.ፍቱ የሮባ እህት አይደለችም | የሮባ እህት ማን ትባላለች? |
| | | |
| | | |
| | | |

**ክፍለጊዜ ዘጠኝ**

## ማስታወሻ

**የዓረፍተ ነገር አገልግሎት**

3. **ትዕዛዛዊ ዓረፍተነገር፡** ትዕዛዝን ለማስተላለፍ የሚያገለግሉ ዓረፍተነገሮች ናቸው። ፍላጎታዊ መልዕክት ይተላለፍባቸዋል፡፡

   ምላሌ፡- እባክህ፣ መስኮቱን ዝጋው!

4. **አጋኗዊ ዓረፍተነገር**

   አጋኗዊ ዓረፍተ ነገር ከውስጥ ፈንቅለው የሚወጡ ድንገተኛና ስሜታዊ ጉዳዮችን መግለጫ ነው። ድንጋጤን፣ አድናቆትን፣ ግርምትን ወይም ቁርጠኛነትን ለመግለፅ የሚዋቀር ዓረፍተነገር ሁሉ አጋኗዊ ዓረፍተነገር ይባላል።

   ምሳሌ፡- እንደሌንሳ የሚያምር አይቼ አላውቅም!

**መልመጃ ስድስት**

**ሀ. በምሳሌዎቹ መሰረት ትእዛዛዊና አጋኗዊ ዓረፍተነገሮችን መስርቱ፡፡**

| ትእዛዛዊ ዓረፍተነገር | አጋኗዊ ዓረፍተነገር |
|---|---|
| 1. መጽሀፉን አምጣ! | እንዴት! ያለመጽሀፍ ነው! |
| 5. | |
| 6. | |
| 7. | |
| 8. | |
| 9. | |

# ምዕራፍ ሰባት

# ማህበራዊ ግንኙነት

## የሚጠበቁ ውጤቶች

**ከዚህ ምእራፍ ትምህርት በኋላ :-**

- የምንባቡን ፍሬ ሀሳብ በማዳመጥ ትናገራላችሁ፡፡
- ስለማህበራዊ ጉዳይ ትገልጻላችሁ፡፡
- ተዘውታሪና ፈሊጣዊ አነጋገሮችን ለተግባቦት ትጠቀማላችሁ፡፡
- በተለያዩ ማህበራዊ ጉዳዮች ላይ ተመስርታችሁ ጽሁፎችን ታዘጋጃላችሁ፡፡
- ተመሳሳይ ፍች ያላቸውን ቃላት ታዛምዳላችሁ፡፡
- አገልግሎታዊ አረፍተነገሮችን ትመሰርታላችሁ፡፡

**ክፍለ ጊዜ አንድ**

## ዕድር

## ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

**በዚህ ትምህርት ክፍል የማዳመጥ ክሂላችሁን እንድታሻሽሉ የሚረዳችሁ ቀርበውላችኋል፡፡ ስለሆነም መልመጃዎቹን በትእዛዙ መሰረት መልሱ፡፡**

### ቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች

**ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቄዎች በቃል መልስ ስጡ፡፡**

1. በአከባቢያችሁ ያሉ የእድር ስሞችን ጥቀሱ፡፡
2. የጠቀሳችኋቸው እድሮች ምን ምን ተግባራትን ይፈጽማሉ?

## የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎች

1. መምህራችሁ ጽሁፉን ሲያነቡላችሁ አዳዲስ ቃላትን በመለየት በማስታወሻ ደብተራችሁ መዝግቡ፡፡
2. የሚቀጥለው ጽሁፍ ስለምን የሚያወሳ ይመስላችኋል?

**ክፍለ ጊዜ ሁለት**

## የአዳምጠ መረዳት ጥያቄዎች

**መልመጃ አንድ**

**ሀ. ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቄዎች ያዳመጣችሁትን ጽሁፍ መሰረት በማድረግ በቃል መልስ ስጡ፡፡**

1. ስለእድር ጠቀሜታ ባዳመጣችሁት ጽሁፍ መሰረት የምታውቁትን ለመምህራችሁ ተናገሩ፡፡
2. ሰዎች እድር የሚገቡት ለምን እንደሆነ ግለጹ?
3. እድር በመግባትና ባለመግባት መካከል ያለውን ልዩነት አስረዱ፡፡
4. እድር አለመግባት የሚያደርሰውን ማህበራዊና ስነልቦናዊ ጫና ግለጹ፡፡
5. "የእድር መስራቾች ከመተዋወቅ አልፎ የጋራ ፍላጎት ያላቸው ናቸው፡፡" የሚለው ሀሳብ የሚያስተላልፈው መልእክት ምንድን ነው?
6. የእድር ደንቦች በውስጣቸው ምን ምን ሊይዙ እንደሚችሉ ተናገሩ፡፡

**ለ. ከስራቸው ለተሰመረባቸው ቃላትና ሀረጋት አገባባዊ ፍች ከቀረቡት አማራጮች ተገቢውን መልስ ምረጡ፡፡**

1. ሰዎች እድር ወይም ሸንጎ በሚል ሁለቱንም መጠሪያ <u>በተለዋዋጭነት</u> ይጠቀሙበታል፡፡

   ሀ. በተቃራኒ ለ. በመተካት ሐ. ሁል ጊዜ መ. ዘወትር

2. አንዱ ሌላውን የሚያካፍልበት እና ለቀጣዩ ትውልድ <u>አውርሰው</u> የሚያልፉበት ማህበራዊ ተቋም ነው፡፡

   ሀ. ተክለው ለ. ሰተዋቸው ሐ. እንዲገለገሉበት አድርገው

   መ. ሁሉም

3. እድር መግባትና አለመግባት ማህበራዊ <u>ጫና</u> አለው፡፡

   ሀ. ግዴታ ሐ. ጉዳት ሐ. አስገዳጅ መ. ሀ ና ሐ መልስ ናቸው፡፡

4. እድር <u>እንደአለኝታ</u> ተደርጎ ይታያል፡፡

   ሀ. ተቃራኒ ለ. ችኩል ሐ. መከታ መ. የማይጠቅም

5. በእድር ውስጥ <u>አድልዎ</u> ቦታ የልውም፡፡

   ሀ. ማበላለጥ ሀ. መደሰት ሐ. መዝናናት መ.ሁሉም

6. እድር አለመግባት ከማህበረሰቡ ራስን እንደማግለል <u>ይቆጠራል</u>፡፡

   ሀ. አንድ፣ሁለት… ይባላል፡፡

   ለ. ከሰው ጋር ይጣላል፡፡

   ሐ. ብዙ ሆኖ መኖር ያመለክታል፡፡

   መ. ይታያል

7. እድር በእድርተኛው ዘንድ እንደቤተሰብ <u>እዳ</u> ተሸካሚ ሆኖ ይታያል፡፡

   ሀ. ገንዘብ ያበደረ ለ. ቤተሰብ ላይ የተጣለ አደራ

   ሐ. የቤተሰብ ሀብት መ. የቤተሰብ አባል

8. <u>ቀደም ሲል</u> እድሮች በቃል በሚተላለፉ ተግባራትና ደንቦች ይተዳደራል፡፡

   ሀ.ከዚህ በፊት ለ. ኋላ ሐ. አሁን መ. ነገ

9. መስራቾቹ ከመተዋወቅ <u>አልፎ</u> የጋራ ፍላጎት ያላቸው ናቸው፡፡

   ሀ. ሄዶ ለ. ዞሮ ሐ. በተጨማሪ መ. አቋርጦ

10. እድር የሚተዋወቁ ሰዎች በፈቃደኝነት የሚመሰርቱት ባህላዊ-ማህበራዊ <u>ተቋም</u> ነው፡፡

ሀ. መስሪያ ቤት ለ.ትምህርት ቤት ሐ. ንብረት መ. መረዳጃ ድርጅት

**ክፍለጊዜ ሶስት**

## ትምህርት ሁለት፡ መናገር

**ከዚህ በታች የቀረቡት ተግባራት የንግግር ክሂላችሁን ችሎታ እንድትጠቀሙ ለማድረግ ያግዛሉ፡፡ ለተግባራቱ ተገቢውን መልስ ስጡ፡፡**

**ማስታወሻ**

ክርክር ሁለት ወይም ከዚያ በላይ በመሆን በግል ወይም በቡድን በመደራጀት በሚደግፉት ርእሰጉዳይ ላይ ተጨባጭ መረጃዎችን በመጠቀም ተከራካሪያቸውን ለማሳመን የሚደረግ ሙግት ነው፡፡ ከተከራካሪዎች የሚጠበቅ ነገር እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

- ስለሚከራከሩበት ርእሰጉዳይ በቂ መረጃ ማሰባሰብ
- በክርክሩ ሂደት ዳኞችን፣ ተከራካሪዎችንና አድማጮችን ሰላምታ በመጠየቅ ስለሚከራከሩበት ርእስ ማስተዋወቅ
- መረጃውን በተጨባጭ በተፈቀደው ጊዜ ውስጥ ማቅረብ
- የተከራካሪን ሀሳብ በመረጃ አስደግፎ ውድቅ ማድረግ
- ዳኞችን፣ ተከራካሪን ማክበር
- በመጨረሻም ሀሳብን አጠቃሎ በማቅረብ ዳኞችን አመስግኖ ማጠናቀቅ ያስፈልጋል፡፡

### ተግባር አንድ

ሀ. ከዚህ በመቀጠል በቡድናችሁ ለሚደርሳችሁ የመከራከሪያ ሀሳብ መረጃ በማጠናቀር ተዘጋጅታችሁ ተከራከሩ፡፡

**ቡድን አንድ፡** እድር ባይኖረንም ከማህበረሰቡ ጋር መኖር ይቻላል፡፡

**ቡድን ሁለት፡** ያለእድር ከማህበረሰቡ ጋር መኖር ይከብዳል፡፡

ለ. ከቀረበው ክርክር ምን እንደተገነዘባችሁ ተራ በተራ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ግለጹ፡፡

ክፍለጊዜ አራት

**ተግባር ሁለት**

1. በምትኖሩበት አከባቢ ሰዎች የሚረዳዱበትን ማህበራዊ አጋጣሚ በተመለከተ መረጃ በማሰባሰብ በክፍል ውስጥ በንግግር አቅርቡ፡፡
2. ጓደኞቻችሁ ካቀረቡት ንግግር የትኛው በደንብ ትኩረታችሁን እንደሳበ በምክንያት በማስደገፍ ለመምህራችሁ ተናገሩ፡፡

ክፍለጊዜ አምስት

# ትምህርት ሶስት፡ ማንበብ

## የቅድመ ንባብ ጥያቄዎች

**ከዚህ በታች ለቀረቡት ሀሳቦች በቡድን በመወያየት በቃል መልሱ፡፡**

1. ስለእቁብ ከዚህ በፊት የምታውቁትን ሀሳባችሁን ለመምህራችሁ ተናገሩ፡፡
2. እቁብ በማህበራዊ ግንኙነት ላይ ያለው አስተዋጽኦ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ፡፡

### እቁብ

የሰብአዊነት አስተሳሰብ «ለሰው መድሃኒቱ ሰው ነው፤» በሚለው ህዝባዊ ፍልስፍና ይገለፃል። ህዝቦች ለሃዘንም ለደስታም ተደጋግፈው ይቆማሉ። ድግግፉን መልክና ስርዓት ለማስያዝ፣ **ዘላቂና** ሁሉንም በእኩልነት የሚያስተናግድ ይሆን ዘንድም ደንብ አበጅተው፣ ልክ ወስነው ያቋቋሟቸው የመደጋገፊያ ጊዜያዊም ሆኑ ዘላቂ መደበኛም ሆኑ ኢ-መደበኛ ተቋማት አሉ።

የግለሰቦች እርስ በእርስ እንዲሁም በግለሰብና ማህበር መካከል ያለው ጥብቅ ቁርኝትና ትስስር ደልዳላ ሚዛን ጠብቆና ጸንቶ እንዲቆይ ምሰሶ ሆኖ ካቆሙት ማህበረሰባዊ ሥርዓቶች መካከል እንደ እቁብ፣ እድር፣ በበዓላት ቀን መጠራራት፣ **ደቦ** ወይም ወንፌል ያሉ ተጠቃሾች ናቸው። እድር፣ እቁብ፣ ማኅበር፣ የመንደር መረዳጃ ማኅበራት በኅብረተሰብ መካከል ላለው ማኅበረሰባዊ እሴቶቻችን መገለጫዎች ናቸው። በቤተሰብ ደረጃ ያሉትን የማኅበረሰባዊ **እሴት** መገለጫዎችን ደግሞ የቤተሰብ ጉባዔና የዘመድ አዝማድ ግብዣ ይጠቀሳሉ። በጓደኛሞች ደረጃም የጓደኛሞች ጉባዔ በጓደኛሞች መካከል ላለው ማኅበረሰባዊ እሴት መገለጫ ናቸው።

## የንባብ ጊዜ ጥያቄዎች

1. ከላይ ከቀረቡት አንቀጾች ውስጥ ያገኛችሁን ፍሬ ሀሳብ ተናገሩ፡፡
2. በቀጣይ ከምንባቡ ምን ምን ሀሳቦችን ማግኘት እንደምትችሉ ገምቱ፡፡

እቁብ በኢኮኖሚ ፋይዳው በማሰብ በአንድ አካባቢ የሚኖሩና የሚተዋወቁ ሰዎች በራሳቸው ነጻ ፍላጐት ከሚመሰርቷቸው ማህበሮች አንዱ ነው። እቁብ አባላቱ በጋራ በስምምነት ደንብ አዘጋጅተው እንደኑሮ ደረጃቸውና የገቢ ምንጫቸው በየሳምንት፣ በየሁለት ሳምንቱ ወይም በየወሩ ገንዘብ የሚከፍሉበትና የሚያጠራቅሙበት ተቋም ነው፡፡ እቁብ ሰዎች የጋራ ገንዘባቸውንም በእጣ በሚወሰን ቅደም ተከተል በተወሰነ **የጊዜ ገደብ** እንዲደርሳቸው የሚያደርግ ነው፡፡ ኢኮኖሚ ጠቀሜታውም የጐላ ነው። እቁብ **የቆየ** መሰረት ያለው ባህላዊ የገንዘብ ማሰባሰቢያ ዘዴ ሲሆን፤ በብዙ ነገሮችም ከባንክ ወይም ከሌሎች የቁጠባ ማህበራት ይለያል። ዘመናዊና የተደራጀ አሰራርን የማይከተል፣ **ወለድ** የማይታሰብበት፣ የሚመራበት ሕግ ወይም ተቆጣጣሪ አካል ወይም በህግ የታወቀ መብትና ግዴታዎችን

መቀበል የሚያስችል ሕጋዊ ሰውነት የሌለው ማህበር መሆኑ በዋናነት ይጠቀሳል።

እቁቦች ልዩ ልዩ ደንቦች ሊኖራቸው ቢችልም ተመሳሳይ ይዘት ያለው አወቃቀርና አሰራር ይከተላሉ። እያንዳንዱ እቁብ ሰብሳቢ፣ ፀሐፊና አባላት አለው። በደንቡ ውስጥ የእጣ አወጣጥ ፣ የቅጣት አፈፃፀምና የአዲስ አባላት ቅበላ፣ እንዲሁም ዕጣን ለሌላ አባል አሳልፎ የመስጠትና የዋስትና አግባብ ስርዓት በዝርዝር ሰፍሮ ይገኛል። የአባላትን የመክፈል አቅምና ፈቃደኝነት ብቻ መሰረት የሚያደርግ ማህበራዊ ተቋምም ነው። ምንም እንኳን ተቋሙ በኢኮኖሚያዊ አቅማቸው ተቀራራቢ ደረጃ ያላቸው ሰዎች የሚደራጁበት ቢሆንም እንደ ዕድር ልዩ ልዩ እምነት፣ ሙያ፣ ቋንቋና ብሄረሰባዊ ማንነት ያላቸውን ሰዎች የሚያስተሳስር መሆኑ ማህበረሰባዊ መሰረቱን ሰፊ ያደርገዋል።

ምንም የገቢ ምንጭ ሳይኖራቸው ተበድረው እቁብ የሚጥሉትን ግን ከትዝብት ማህደራችን ውስጥ መለየቱ ተገቢ አይመስለኝም። እነዚህ ሰዎች እጣ ፈንታቸው በአበዳሪዎቻቸው ላይ የወደቀ ነው። ብድሩን መመለስ ካልቻሉ ደግሞ ብሩን ሲቀበሉ ዋስ የሆናቸው ሰው ተጠያቂ ይሆናል። በሌላ አገላለጽ በተለይ የእቁብ ገንዘብ የበሉ ሰዎች ቀሪ ክፍያ ስለመክፈላቸው የአንድነትና የነጠላ ዋስትና በፅሁፍ፣ ምስክሮች ባሉበት የገንዘቡ መጠን ተገልፆ ዋሶችን ማስፈረሙ በተለያየ ምክንያት እቁብ የበሉ ሰዎች ሲጠፉ ዋሱን ለመጠየቅ ያስችላል። እቁብ ያለምንም ተፈጥሯዊና ማህበረሰባዊ መድልዎ ሁሉንም ሰው እኩል የሚያሳትፍና ጠቀሜታው ከፍ ያለ በመሆኑ ሊበረታታና ዘላቂነት ሊኖረው ይገባል። ከተቻለም ዘመናዊነትን ጠብቆ መዋቀር ቢችል ከዚህም በላይ የጎላ ጠቀሜታ ይኖረዋል።

*(አዲሱ ገረመው፡፡ 2012፡፡አዲስ ዘመን፣ አዲስአበባ፡፡)*

## የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች

### መልመጃ ሁለት

**ሀ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ምንባቡን መሰረት በማድረግ ትክክል ከሆነ እውነት ካልሆነ ግን ሀሰት በማለት በጽሁፍ መልሱ፡፡**

1. እቁብ መግባት የሚችሉት ሀብታሞች ብቻ ናቸው፡፡
2. እቁብ በአንድ አካባቢ የሚኖሩ ሰዎች በስምምነት የሚፈጥሩት ማህበራዊ መረዳጃ ነው፡፡
3. እቁብ የሚከፈልበት ጊዜ በከፋዮች ስምምነት ይወሰናል፡፡
4. በእድርና በእቁብ መካከል ልዩነት የለም፡፡
5. በሁለተኛው አንቀጽ "…ምሶሶ ሆኖ ካቆሙት…" ተብለው የተገለጹት የእድሩ ባለቤቶች ናቸው፡፡
6. እቁብ የበላ ሰው ብሩን ለመውሰድ ዋስ ይጠራል፡፡
7. በመጨረሻው አንቀጽ "እነዚህ ሰዎች" የተባሉት እቁብ ሰብሳቢዎች ናቸው፡፡

**ለ. ከስራቸው ለተሰመረባቸው ቃላት ምንባቡን መሰረት በማድረግ የያዙትን አገባባዊ ፍች ከተሰጡት አማራጮች ምረጡ፡፡**

1. የሰብአዊነት አስተሳሰብ "ለሰው መድሃኒቱ ሰው ነው" በሚለው <u>ፍልስፍና</u> ይገለጻል፡፡

    ሀ. ምክር                    ሐ. ኩራት

    ለ. አስተሳሰብ                 መ. ድጋፍ

2. በግለሰብና ማህበር መካከል ያለው ጥብቅ ቁርኝትና ትስስር ደልዳላ ሚዛን ጠብቆና <u>ጸንቶ</u> እንዲቆይ ምሶሶ ሆኖ ካቆሙት እቁብ አንዱ ነው፡፡

ሀ. መሰረት ይዞ　　　　　　　　ሐ. ሞልቶ

ለ. ላልቶ　　　　　　　　　　መ. ፈጥኖ

3. በእቁብ አደረጃጀት ሂደት አባላቱ በጋራ በስምምነት የሚፈጥሩት ደንብ አለ፡፡

ሀ. ፍላጎት　　　　　　　　　ሐ. ህግ

ለ. ውድድር　　　　　　　　　መ. ቅጣት

4. እቁቦች ልዩ ልዩ ደንቦች ሊኖራቸው ቢችልም ተመሳሳይ ይዘት ያለው አወቃቀርና አሰራር ይከተላሉ፡፡

ሀ. አብሮ ይጓዛሉ　　　　　　ሐ. ይወስዳሉ

ለ. ይተገብራሉ　　　　　　　መ. ያመጣሉ

5. እነዚህ ሰዎች እጣፈንታቸው በአበዳሪዎቻቸው ላይ የወደቀ ነው፡፡

ሀ. የለመለመ　　　　　　　　ሐ. የከሰረ

ለ.የዘለለ　　　　　　　　　 መ. በባለቤትነት የተወሰደ

**ክፍለጊዜ ሰባት**

**ማስታወሻ**

**ፈሊጣዊ አነጋገር**

በንግግርም ሆነ በጽሁፍ ፈሊጣዊ አነጋገሮችን እየቀላቀሉ መጠቀሙ ጥልቅና ምጥቀት ያላቸው ሀሳቦችን ለማስተላለፍ ከማስቻሉም በላይ የቋንቋ ችሎታንም ለማስገንዘብ አይነተኛ ማስረጃ ይሆናል፡፡

ምሳሌ:አንድ ሰው የተስማሙበትን መልሶ የሚያፈርስ ሰው ቢያጋጥመው በአጭር አገላለጽ

አንተ! ሁለት ምላስ አለህ፡፡ በማለት ሊገልጽ ይችላል፡፡ ይህም ከሀዲ መሆኑን ይገልጽበታል፡፡

ውስጥ የያዙትን ትርጉም በጽሁፍ መልስ ስጡ፡፡

ምሳሌ፡1. እሱ በስብሰባው ላይ የተነገረውን ሀሳብ ሰምቶ ልቡ ተሰበረ ፡፡

(በጣም አዘነ)

1. አለማየሁ ሀሳቡ <u>ሁለት ልብ</u> ሆነበት፡፡
2. እቴነሽ <u>ልበደንዳና</u> ነች፡፡
3. ጫልቱን <u>ሳር ቅጠሉ</u> ይወዳታል፡፡
4. ገመቹ <u>ቆርጦ ቀጥል</u> ነው፡፡

**ክፍለጊዜ ስምንት**

## ተግባር ሶስት

በቡድን በመሆን ሰዎች ለተለያዩ ጉዳዮች የሚጠቀሙባቸውን አስር ፈሊጣዊ አባባሎችን ከተለያዩ ምንጮች መረጃ በማሰባሰብ አገልግሎታቸውን በዓረፍተነገር ውስጥ በማስገባት ለክፍል ጓደኞቻችሁ በጽሁፍ አቅርቡ፡፡

ምሳሌ፡ ሰውየው ብሩን ቶሎ ስላልተመለሰለት <u>ደሙ ፈላ</u>፡፡ **ተናደደ**

## መልመጃ ሶስት

**ለሚከተሉት ፈሊጣዊ አባባሎች በጽሁፍ ፍቺያቸውን ስጡ፡፡**

**ምሳሌ፡ ሁሉ አማረሽ - ሁሉንም የምትመኝ**

1. መላቢስ
2. አይንአውጣ
3. ጆሮጠቢ
4. ሆደባሻ
5. እጁ አጠረ
6. እግረደረቅ
7. ጥላቢስ
8. የአዞ እምባ
9. ጥርሰ ፍንጭት


## ትምህርት አራት ፡ መጻፍ

ከዚህ በታች የቀረቡት ጥያቄዎች የመጻፍ ክሂላችሁን በአግባቡ ለመጠቀም የሚያግዙ ናቸው፡፡ ስለሆነም ለቀረቡ ተግባራት ተገቢውን መልስ ስጡ፡፡

### ተግባር አራት

ሀ. ለሚከተሉት ተግባራት በቡድን በመሆን ተገቢውን መልስ በጽሁፍ ስጡ፡፡

1. የቀረበላችሁን ምሳሌ መሰረት በማድረግ በአከባቢያችሁ የማህበረሰቡን አብሮ የመኖር ባህል የሚያጠናክሩ ማህበራዊ እሴቶች ጻፉ፡፡




2. በምንባቡ መግቢያ “ለሰው መድሃኒቱ ሰው ነው” የሚለው ምሳሌያዊ አነጋገር የያዘውን መልእክት አስፋፍታችሁ ጻፉ፡፡
3. ሌሎች ማህበራዊ ኑሮን የሚያበረታቱ ምሳሌያዊ አነጋገሮችን ቤተሰብ በመጠየቅ መዝግባችሁ የሚያስተላልፉትን መልእክት በጽሁፍ አቅርቡ፡፡

ምሳሌ፡ ከአንድ ብርቱ ሁለት መድሀኒቱ - አንድሰው ብቻውን ከሚሰራ ሁለት ሆነው ቢሰሩ ስራው ቶሎ ሊሰራ ይችላል፡፡

## ትምህርት አምስት፡ ቃላት

በቀጣይ የቀረቡ የመልመጃ ጥያቄዎች በዚህ ትምህርት ክፍል የቃላት እውቀታችሁን እንድታሳድጉ የሚረዱ መልመጃዎች ቀርበዋል፡፡ ስለዚህ ጥያቄዎቹን በተገቢው መንገድ ስሩ፡፡

### መልመጃ አራት

ከዚህ በታች በሀ ስር የተዘረዘሩት ቃላት ከላይ በቀረበላችሁ ምንባብ ውስጥ ደምቀው የቀረቡ ሲሆን አገባባቸውን መሰረት በማድረግ ፍቺያቸውን ከለ ስር በመምረጥ አዛምዱ፡፡

| "ሀ" | "ለ" |
|---|---|
| 1. ዘላቂ | ሀ. ማብቂያ ጊዜ |
| 2. ደቦ | ለ. ሊደገፍ |
| 3. እሴት | ሐ. መደራጀት |
| 4. ገደብ | መ. ማበላለጥ |
| 5. የቆየ | ሠ. አዲስ መመዝገቢያ |
| 6. ወለድ | ረ. ሀብት |
| 7. ቅበላ | ሰ. ረጅም ጊዜ ያስቆጠረ |
| 8. መድልዎ | ሸ. መክፈያ ጊዜ ካለፈ የሚጨመር |
| 9. ሊበረታታ | ቀ. ወጥ |
| 10. መዋቀር | በ. ትብብር |

### ተግባር አምስት

በሚከተሉት ቃላት መካከል ያለውን እንድነትና ልዩነት በቡድን ሆናችሁ ከተወያያችሁ በኋላ የደረሳችሁበትን ሀሳብ ለመምህራችሁ በጽሁፍ አቅርቡ፡፡

1. እድር እና እቁብ
2. ደቦ እና የበጎ ፈቃድ አገልግሎት

**ክፍለጊዜ አስራ አንድ**

**መልመጃ አምስት**

ከዚህ በታች ሰዎች ተገናኝተው ስለኑሮዋቸው የሚነጋገሩበትን አጋጣሚዎች የሚገልጹ ቃላትና ሀረጋት ተዘርዝረዋል በምሳሌው መሰረት በተጠቀሱት መገናኛ ቦታዎች የሚያነሱትን ሀሳብ በጽሁፍ ግለጹ፡፡

ምሳሌ፡ የቀበሌ ስብሰባ - በቀበሌያቸው ስለሚደረጉ ልማቶች ይነጋገራሉ፡፡

1. የእድር መሰብሰቢያ ቦታ
2. ሰርግ ቤት
3. የእምነት ቦታዎች
4. ትምህርት ቤት
5. የስፖርት ማዘውተሪያ ቦታዎች
6. ሀዘን

**ክፍለጊዜ አስራ ሁለት**

# ትምህርት ስድስት፡ ሰዋስው

**በዚህ የትምህርት ይዘት የቀረቡት የመልመጃ ጥያቄዎች የሰዋስው እውቀታችሁን ለመጠቀም የሚረዱ ስለሆነ ጥያቄዎችን በትኩረት በማንበብ ተገቢውን መልስ በጽሁፍ ስጡ፡፡**

**መልመጃ ስድስት**

ሀ. ከዚህ በታች በሰንጠረዡ ውስጥ የቀረቡትን ዓረፍተነገሮች ምሳሌ በማድረግ ለዓረፍተነገር አገልግሎት አይነቶች ምሳሌ ሊሆኑ የሚችሉ በመመስረት በትክክለኛው ቦታቸው አስገቡ፡፡

| አዎንታዊ ዓረፍተነገር | አሉታዊ ዓረፍተነገር | ጥያቄያዊ ዓረፍተነገር | ትእዛዛዊ ዓረፍተነገር |
|---|---|---|---|
| | | | |
| | | ሴና መቼ መጣች? | |
| | | | |
| መኪና መንዳት ይችላል፡፡ | | | ወደቤትህ ግባ! |
| | ከመስሪያ ቤት አልተመለሰም፡፡ | | |

ለ. ከዚህ ቀደም አረፍተ ነገሮች ከአገልግሎታቸው አንጻር በአራት እንደሚመደቡ የተማራችሁትን በማስታወስ በአራቱ የአረፍተነገር አገልግሎት አይነቶች ለእያንዳንዳቸው ምሳሌ የሚሆኑ ሶስት ሶስት አረፍተ ነገሮችን መስርቱ፡፡

# ምእራፍ ስምንት

## ሱሰኝነት

### የሚጠበቁ ውጤቶች

ከዚህ ምእራፍ ትምህርት በኋላ፡-

- ሱሰኝነት ያለውን ተጽእኖ ትገልጻላችሁ፡፡
- ያዳመጣችሁትን ጽሁፍ ፍሬ ሀሳብ ትገልጻላችሁ፡፡
- ሀሳብን እንደገና በማዋቀር ታቀርባላችሁ፡፡
- የምንባብን ሀሳብ እንደገና በማቀናጀት በቃል ታቀርባላችሁ፡፡
- በጽሁፍ ውስጥ ስርዓተ ነጥቦችን ትጠቀማላችሁ፡፡
- ለተዘውታሪ ቃላት አገባባዊ ፍች ትሰጣላችሁ፡፡
- ድርብ ዓረፍተ ነገሮችን ትመሰርታላችሁ፡፡

ክፍለ ጊዜ አንድ

## ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

**ከዚህ በታች የሚቀርብላችሁ ጽሁፍ እና የመልመጃ ጥያቄዎች የማዳመጥ ክሂላችሁን እንድትጠቀሙ የሚያግዙ በመሆናቸው ለጥያቄዎቹ ተገቢውን መልስ ስጡ፡፡**

## የሱሰኝነት ተጽእኖ

### ቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች

**ሀ. ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቄዎች በቡድን በመነጋገር በቃል መልስ ስጡ፡፡**

1. የሱስን ምንነት ለመምህራችሁ ተናገሩ፡፡
2. ሱስ የሚያስይዙ ነገሮች ምን ምን ናቸው?

## የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎች

1. መምህራችሁ ጽሁፉን ሲያነቡላችሁ አዳዲስ ቃላት ናቸው የምትሉትን በማስታወሻ ደብተራችሁ መዝግቡ፡፡
2. ጽሁፉን እያዳመጣችሁ በምክንያትና ውጤት የተሳሰሩ ዓረፍተነገሮችን መዝግቡ፡፡

**ክፍለጊዜ ሁለት**

## የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች

### መልመጃ አንድ

**ሀ. ለቀረቡት ጥያቄዎች ባዳመጣችሁት መሰረት በጽሁፍ ትክክለኛውን መልስ ስጡ፡፡**

1. ሱስ ከሚያስይዙ ነገሮች መካከል ሶስቱን ዘርዝሩ፡፡
2. ሱሰኝነት ለምን ለምን ችግሮች እንደሚያጋልጥ አብራሩ፡፡
3. ሱስ አንዴ ከተለመደ በኋላ መላቀቅ ስለመቻልና አለመቻል ያላችሁን ሀሳብ ግለጹ፡፡
4. ሲጋራ የሚያጨሱ ሰዎች ከማያጨሱ ሰዎች ጋር ሲነጻጸሩ በምን በሽታ ሊጠቁ እንደሚችሉ ዘርዝራችሁ ጻፉ፡፡
5. በአንደኛው አንቀጽ የመጀመሪያው መስመር “በየጊዜው ውል የሚል አምሮት…” ሲባል ምን ለማለት ተፈልጎ ነው?
6. በሲጋራ ውስጥ ያለው ንጥረነገር ምን የማድረግ ሀይል እንዳለው ግለጹ፡፡
7. ጫት ምን የማድረግ ሀይል አለው?
8. ሰዎች በስካር መንፈስ ምን ሊያደርጉ እንደሚችሉ እና ስካሩ ሲያልፍላቸው ምን እንደሚሰማቸው አስረዱ፡፡

9. ሱሰኝነት በማህበራዊ ህይወት ሊያመጣ የሚችለውን አሉታዊ ተጽእኖ ግለጹ፡፡

**ለ. ለሱስ የሚያጋልጡ ነገሮች በማህበራዊ፣ በኢኮኖሚ እና በጤና ላይ የሚያስከትሉ አሉታዊ ተጽእኖዎችን ምሳሌውን መሰረት በማድረግ በቢጋር ሰንጠረዥ ውስጥ አመልክቱ፡፡**

| ሱስ የሚያስይዙ ነገሮች | በማህበራዊ ኑሮ | በኢኮኖሚ | በጤና |
|---|---|---|---|
| ሲጋራ ማጬስ | ሰዎች ሽታውን በመሸሽ ከሰው መራቅ | | |
| ጫት መቃም | | ገንዘብ ማጣት | |
| አልኮል መጠጣት | | | ለሳንባ በሽታ መጋለጥ |

**መልመጃ ሁለት**

**ሀ. በሚከተሉት ዓረፍተነገሮች ውስጥ ለተሰመረባቸው ቃላት አገባባዊ ፍች ከቀረቡት አማራጮች በመምረጥ መልሱ፡፡**

1. ሱስ አንዴ ከተለመደ በየጊዜው አምጡ አምጡ የሚያሰኝ ልማድ ነው፡፡
   ሀ. አድርጉ ሐ. ብሉ
   ለ. አትውሰዱ መ. ጨፍሩ
2. ከሱስ አስያዥ ነገሮች አንዱ ሲጋራ ነው፡፡
   ሀ. ወሳጅ ሐ. አጋላጭ
   ለ. ውስጥ መ. አገናኝ
3. እንደሲጋራ ማጨስ ሁሉ ጫት መቃም ሱስ ያስይዛል፡፡
   ሀ. መጣላት ሐ. መጠጣት
   ለ. መብላት መ. መቆርጠም

4. በስካር መንፈስ ጥፋት የሚሰሩ ሰዎች ስካሩ ካለፈላቸው በኋላ በሰሩት ስራ ይጸጸታሉ፡፡

ሀ. ይደሰታሉ ሐ. ይሮጣሉ

ለ. ይዘላሉ መ. ባላደረኩት ኖሮ ይላሉ

5. ለከፍተኛ ሱስ ከተጋለጡ በኋላ አብዛኞቹ ከሱስ ለመውጣት ያዳግታቸዋል፡፡

ሀ. ይቀላቸዋል ሐ. ያቅታቸዋል

ለ. ይቀናቸዋል መ. ያስጠላቸዋል

6. በጫት ሱስ መጠመድ የስራ ባህልን ስለሚጎዳ ለግለሰብም ሆነ ለሀገር እድገት ጸር ይሆናል፡፡

ሀ. መያዝ/እንቅፋት ሐ. ደስታ/መፈወስ

ለ. ምቹት/ተድላ መ. እድገት/መርካት

7. የጫት ሱስ፣ ወጣቶች አፍላ እድሜያቸውን በትምህርትና በስራ እንዳያሳልፉ እንቅፋት ይሆናል፡፡

ሀ. የእርጅና ሐ. የጉልምስና

ለ. የልጅነት መ. ሀናሐ መልስ ናቸው፡፡

8. ሱሰኝነት ለተደጋጋሚ ብስጭት ስለሚፈጥር የጤና ችግር ያስከትላል፡፡

ሀ. ደስታ ሐ. ኩራት

ለ. ንዴት መ. ጥፋት

9. በሱስ ምክንያት ወጣቶች ለቦዘኔነትና ለድብርት ይጋለጣሉ፡፡

ሀ. ለስራ ፈጣሪነት ሐ. ለመጠንቀቅ

ለ. ለመቀለድ መ. ለስራፈትነት

ክፍለጊዜ ሶስት

## ትምህርት ሁለት፡ መናገር

የሚከተሉት ተግባራት የንግግር ክሂላችሁን ውጤታማ በሆነ መልኩ እንድትጠቀሙ የሚረዱ በመሆናቸው ለተግባራቱ ተገቢውን መልስ ስጡ፡፡

### ተግባር አንድ

1. የሱሰኝነት ተጽእኖ በሚል ከዚህ በፊት የቀረበላችሁን ጽሁፍ ፍሬ ሀሳብ ለክፍል ጓደኞቻችሁ በቃል አቅርቡ፡፡

2. አልኮልነት ያላቸው መጠጦች መጠጣት በጤና ላይ የሚያስከትለውን ጉዳት የህክምና ባለሙያ ጠይቃችሁ ያገኛችሁትን መረጃ በቃል ለክፍል ተማሪዎች ግለጹ፡፡

ክፍለጊዜ አራት

## ትምህርት ሶስት፡ ምንባብ

በዚህ የትምህርት ይዘት የቀረቡት ምንባብና የመልመጃ ጥያቄዎች የማንበብ ክሂላችሁን እንድትጠቀሙ የሚረዱ ስለሆኑ ለጥያቄዎቹ ተገቢውን መልስ ስጡ፡፡

### ቅድመንባብ ጥያቄዎች

ሀ. ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቄዎች በቃል መልስ ስጡ፡፡

1. በሱስ የተጠቁ ወጣቶች ምን ምን ሲፈጽሙ ተመልክታችሁ ታውቃላችሁ?
2. ወላጆች ልጆቻቸው በሱስ እንዳይጠቁ ምን ሊያደርጉ እንደሚችሉ ተናገሩ፡፡

## ሱስና ወጣቶች

ሱስ ማንኛውም ነገር በሰዎች ላይ የአካላዊና የስነልቦናዊ ጥገኝነት ስሜትን የሚፈጥር ነው፡፡ ሱስ የሚያካትታቸው፣ ሰዎች ለመነቃቃት፣ ድብርትን ለማስወገድ፣ ጀብዱ ለመሥራት፣ ህመምን ለማስታገስና ከፍተኛ የደስታ ስሜትን ለመጎናጸፍ ብለው የሚያጨሷቸው፣ የሚቅሟቸው፣ በአፍንጫ የሚስቧቸውንና በደም ስር የሚወስዷቸውን ነገሮች ናቸው፡፡

ሰዎች በተለያዩ ምክንያቶች በሱስ ይጠመዳሉ፡፡ ከምክንያቶቹም መካከል ቤተሰብ፣ ጓደኛ እና አካባቢ ይጠቀሳሉ፡፡ ከቤተሰብ አንጻር ለምሳሌ አባት ቤት ውስጥ ሲጋራ ሲያጨስ እያየ ያደገ ልጅ በሲጋራ ሱስ የመያዝ እድሉ ከፍተኛ ይሆናል፡፡ በሱስ የተጠመደ ጓደኛ ያለውም እንዲሁ ቀስበቀስ ሱሰኛ ሊሆን ይችላል፡፡ በአከባቢው ሱስ የሚያስይዙ ነገሮችን የሚያዘወትሩ ሰዎች መካከል ያደገ ልጅ በአከባቢ የሚያስተውለውን ነገር ለመጠቀም ሲሞክር ሱሰኛ ሆኖ ሊቀር ይችላል፡፡ በዚህ የተነሳ ወጣቶችም እንደ ቀልድ አንድ ብለው የጀመሩት ሲውል ሲያድር የህይወታቸው አካል ይሆንና ኑሯቸውን በማመሰቃቀል እስከ ህልፈተ ህይወት ሊያደርሳቸው ይችላል፡፡

ሱስ አምራች ኃይል በሚባሉት ወጣቶች ላይ የተለያዩ ተጽእኖዎችን ያመጣል፡፡ ከነዚህ መካከል ዋና ዋናዎቹ በትምህርት፣ በአካላዊ ጤና፣ በአእምሮ ጤና፣ በማህበራዊ ኑሮ እና በኢኮኖሚ ላይ የሚያመጣው ተጽዕኖ ናቸው፡፡

## የንባብ ጊዜ ጥያቄዎች

1. ለሱስ የሚያጋልጡ ምክንያቶች ምንድን ናቸው?
2. እስካሁን ያነበባችሁትን መሰረት በማድረግ በቀጣይ ምንባቡ ስለምን የሚያወሳ ይመስላችኋል?

ሱስ በትምህርት ላይ በርካታ ችግሮችን ያመጣል፡፡ በተለይ በወጣት ተማሪዎች ላይ ከትምህርት መቅረት፣ የክፍልና የቤት ስራ አለመስራት፣ በተጓዳኝ የትምህርት እንቅስቃሴ በንቃት አለመሳተፍ ያስከትላል፡፡ እንዲሁም ለውጤት ማሽቆልቆል እና ለትምህርት ማቋረጥ ምክንያት ይሆናል፡፡ ይህም የሚሆንበት ምክንያት አደንዛዥ ዕፅና ሱሰኝነት በአዕምሯቸውና በጠባያቸው ላይ በሚያሳድረው ተጽእኖ ትምህርታቸውን በትኩረት መከታተል እንዳይችሉ ስለሚያደርጋቸው ነው፡፡

ሱስ በአካላዊ ጤናም ላይ ጉዳት ያስከትላል፡፡ አብዛኛውን ጊዜ በከተማዎች አካባቢ የሚታዩ የመኪና አደጋዎች ውስጥ ትልቁን ድርሻ የሚይዙት በወጣት አሽከርካሪዎች ምክንያት የሚከሰቱ ሲሆኑ ለአደጋውም መንስኤ ጠጥቶ ማሽከርከር ነው። በዚህም ምክንያት ሱስ በንብረታቸው ላይ ከሚያደርሰው ጉዳት ባሻገር ለአካል ጉዳተኝነትና ለሞት ያጋልጣቸዋል፡፡አልፎ ተርፎም በሌሎች ሰዎችና ንብረት ላይ ከፍተኛ ጉዳት ያደርሳሉ፡፡

ሱስ በአእምሮ ጤና ላይ የሚያስከትለው ጉዳቶች የሚከተሉት ናቸው፡፡ እነዚህም የዕድገት ውስንነት፣ ተስፍ መቁረጥ፣ መገለል፣ ስነልቦናዊና ማኅበራዊ ችግሮች ናቸው፡፡ በሱስ የተጠመዱ ወጣቶች ከሱስ ነፃ ከሆኑ ወጣቶች ጋር ሲነጻጸሩ ለተለያዩ የአዕምሮ በሽታዎች የመጋለጥ ዕድላቸው ከፍተኛ ነው፡፡ ለምሳሌ ድብርት፣ አስቸጋሪ ጠባይ፣ የስብዕና መቃወስ፣ እራስን ለማጥፋት ማሰብና መሞከር እንዲሁም ማጥፋት ተጠቃሽ ናቸው፡፡ በተጨማሪም ሱስና አደንዛዥ ዕፅ የወጣቶችን የማስታወስ ስርዓትና ከዚህ ቀደም በቀላሉ የሚያከናውኗቸውን ስነልቦናዊና አካላዊ ክህሎቶችን ያዛባል፡፡

በተጨማሪም ሱስ ማህበራዊ ኑሮን ያመሰቃቅላል፡፡ ለምሳሌ በሱስ ውስጥ ያሉ ወጣቶች ከጓደኞቻቸው ወይም አቻዎቻቸው ይገለላሉ፡፡ እንዲሁም

በሱስ የተያዘ ጠባያቸውን በመመልከት ማኅበረሰቡ የተለያዩ አካባቢያዊ እንቅስቃሴዎች ውስጥ ሌሎችንም ያበላሻሉ ብሎ በማሰብ እንዳይሳተፉ ይከለክሏቸዋል። ይህም ለለውጥና እራሳቸውን ለመቀየር ያላቸውን መነሳሳት ያኮላሸዋል፡፡

ሱሰኝነት ከግላዊ ተግዳሮቶች ባሻገር በቤተሰብ ህይወት ውስጥ ትልቅ ችግር ይፈጥራል፡፡ በተለይ በወንድምና እህቶች ላይ የሚፈጥረው ጫና ቀላል አይደለም፡፡ ወንድማቸው/እህታቸው ወይም አንድ የቤተሰብ አካል በሱስ መጠመዱ በጓደኞቻቸውና በማኅበረሰባቸው ውስጥ ከመልካም ቤተሰብ እንዳልመጡ አድርጎ ስለሚመለከታቸው ከሌላው ጋር ማኅበራዊ መስተጋብር ለመፍጠር ይሸማቀቃሉ። እራሳቸውንም ያገላሉ፡፡

በተጨማሪም የቤተሰብን ኢኮኖሚአዊ አቅም ይፈታተናል፡፡ በሱስ ለተጠመዱ ወጣቶች የሚወጣው ወጪ ቀላል አይደለም፡፡ በሱስ በመጠመዳቸው ምክንያት እራሳቸውን ማስተዳደር ስለማይችሉ በሌሎች ላይ ጥገኛ ይሆናሉ፡፡ ከፍ ሲልም የሚያገኙትን ገንዘብ ሁሉ ሱሳቸውን ለማስታገስ ይጠቀሙበታል። ያን ማድረግ ካልቻሉ ደግሞ ወደ ወንጀል ሊሰማሩ ይችላሉ፡፡ ይህም በመሆኑ ከእዚህ ህይወት ውስጥ እንዲወጡ የሚደረገው እገዛና የህክምና ዕርዳታ ቀላል የማይባል ወጪ ያስወጣል፡፡

በአጠቃላይ ዕድሜቸው ከ18 ዓመት በታች የሆኑ ወጣቶች ወንጀል ቢሠሩ እንኳን ወንጀለኞች ሳይሆን ወጣት ጥፋተኞች ነው የሚባሉት፡፡ ማንኛውም ሰው ሊክደው የማይችል የወጣት ጥፋተኝነትና ሱስ ግንኙነት አላቸው፡፡ በሱስ ምክንያት ወጣቶች የተለያዩ ጥፋቶችን ሲያጠፉ በፍርድ ቤት ጉዳያቸው ተመርምሮ ጥፋተኛ ሆነው ከተገኙ ወደ ወጣቶች ተሐድሶ ማዕከል እንዲገቡ ይደረጋል፡፡

*(አዲስ ዘመን፡፡ 2011፡፡ ለመማሪያ መጽሀፍ እንዲመች ተሻሽሎ የቀረበ)*

ክፍለጊዜ አምስት

## የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች

### መልመጃ ሶስት

**ለሚከተሉት ጥያቄዎች ምንባቡን መሰረት በማድረግ በጽሁፍ መልስ ስጡ፡፡**

1. ሰዎች የሱሰኝነት ጠባይ እንዳላቸው የሚያመለክቱ ምልክቶች ምን ምን ናቸው?
2. ሰዎች ሱስን እንዴት ሊጀምሩ ይችላሉ?
3. ሱሰኝነት በትምህርት ላይ የሚያስከትለው ችግር ምንድን ነው?
4. ሱስ የሚያስይዙ ነገሮች በምን በምን ዘዴ ሊወሰዱ ይችላሉ?
5. በአራተኛው አንቀጽ "ይህም…" የሚለው ቃል ምን ለማመልከት የገባ ነው?

### መልመጃ አራት

**ሀ. የሚከተሉት ቃላት ከምንባቡ የተወሰዱ ናቸው፡፡ ቃላቱ ምንባቡ ውስጥ ባላቸው አውድ ፍች ስጡ፡፡**

| | | |
|---|---|---|
| 1. ተግዳሮቶች | 7. ማሽቆልቆል | 13. ጥገኝነት |
| 2. መስተጋብር | 8. ማከላሸት | 14. ጀብዱ |
| 3. አደንዛዥ እጽ | 9. ማሽማቀቅ | 15. ማጎናጸፍ |
| 4. አእምሮ ጤና | 10. ማዕከል | 16. መመሰቃቀል |
| 5. መገለል | 11. ተሃድሶ | 17. ተጓዳኝ |
| 6. አካላዊ ጤና | 12. ድብርት | 18. መቃወስ |

**ለ. ቀጥሎ ከቀረቡት ጉዳዮች አኳያ በምንባቡ ከተጠቀሱት የሱስ ተጽእኖዎች ባሻገር እናንተ ያስተዋላችኋቸውን ሌሎች ተጽእኖዎችን በመለየት ተወያዩባቸው፡፡**

1. ትምህርት
2. ጤና
3. ጓደኝነት
4. ቤተሰብ

**ክፍለጊዜ ስድስት**

## ትምህርት አራት፡ መጻፍ

**የሚከተሉት ማስታወሻዎችና የመልመጃ ጥያቄዎች የመጻፍ ክሂላችሁን ለመጠቀም የሚያስችሉ በመሆናቸው ለጥያቄዎቹ ተገቢውን መልስ ስጡ፡፡**

### ማስታወሻ

**ስርዓተነጥብ**

ሰዎች በንግግር ሲግባቡ ድምጻቸውን ከፍ እና ዝቅ በማድረግ መልእክት ያስተላልፋሉ፡፡ በጽሁፍ ሲግባቡ ግን ተገቢውን ስርዓተነጥብ በተገቢው ቦታ ካልተጠቀሙ በስተቀር ማስተላለፍ የፈለጉት መልእክት ግቡን አይመታም፡፡ በጽሁፍ ውስጥ ከምንጠቀምባቸው ስርዓተነጥቦች የሚከተሉት ይጠቀሳሉ፡፡

**አንድ ነጥብ ወይም ይዘት (.)** አንድ ነጥብ ለሚከተሉት አገልግሎቶች ይውላል፡፡

አህጽሮተ ቃልን የሚመሰርቱ ሆሄያትን ለመለየት ያገለግላል፡፡

ምሳሌ፡ ኢ.መ.ማ. የኢትዮጵያ መምህራን ማህበር

አንድን ቃል በተወሰኑ ሆሄያት አሳጥሮ ለማቅረብ

ምሰሌ፡ ወሮ. ወይዘሮ

ብርና ሳንቲምን ለይቶ ለማመልከት

ምሳሌ፡ 5.45 (አምስት ብር ከአርባ አምስት ሳንቲም)

**ሁለት ነጥብ ወይም ነቁጥ (፡)**

ሰዓትንና ደቂቃን ለመለየት ያገለግላል፡፡

ምሳሌ፡ 3፡40 (ሶስት ሰዓት ከአርባ ደቂቃ)

**መልመጃ አምስት**

**ሀ. በምሳሌው መሰረት የቀረቡትን ቃላትና ሀረጋት አንድ ነጥብ በመጠቀም አሳጥራችሁ ጻፉ፡፡**

ምሳሌ፡ ወይዘሮ ወ.ሮ

1. ዓመተምህረት
2. ዶክተር
3. ሁለት ብር ከሀምሳ ሳንቲም

**ለ. የቀረበውን ምሳሌ መሰረት በማድረግ ሁለት ነጥብ በመጠቀም ሰዓትና ደቂቃን በአሃዝ አስተካክላችሁ ጻፉ፡፡**

ምሳሌ፡ ስምንት ሰዓት ከሰላሳ ደቂቃ = 8:30

1. ስድስት ሰዓት ከሰላሳ ደቂቃ
2. አስራ ሁለት ሰዓት ከሃያ ደቂቃ

**ክፍለጊዜ ሰባት**

## ስርዓተነጥብ

3. **ሁለት ነጥብ ከሰረዝ** (፡-) ይህ ምልክት የዓረፍተነገር ሀሳብ ከማብቃቱ በፊት በዝርዝር የሚቀርቡ ነጥቦች መኖራቸውን ለማመልከት ያገለግላል፡፡
   ምሳሌ፡ የኤድስ መተላለፊያ መንገዶች በርካታ ናቸው፡፡ እነዚህም፡- ልቅ የሆነ የግብረስጋ ግንኙነት፣ ባልተቀቀለ መርፌ መጠቀም የመሳሰሉት ናቸው፡፡
4. **ነጠላ ሰረዝ** (፣) በዓረፍተ ነገር ውስጥ በተከታታይ ተደርድረው የሚቀርቡትን ተመሳሳይ ሙያ ያላቸውን የቃላት ድርድር ለመለየት ያገለግላል፡፡
   ምሳሌ፡ ከበደ መርካቶ ሄዶ ኮት፣ ሱሪ፣ ሸሚዝ፣ የውስጥ ልብሶችና ጫማ ገዝቶ መጣ፡፡
5. **አራት ነጥብ** (፡፡) የተሟላ ሀሳብ የሚያስተላልፍ ዓረፍተነገር ማቆሚያ ነው፡፡
   ምሳሌ፡ አበበ ጎበዝ ተማሪ ነው፡፡

**መልመጃ ስድስት**

**ሀ. የሚከተሉትን ዓረፍተነገሮች ተገቢውን ስርዓተነጥብ በመጠቀም አሟልታችሁ ጻፉ፡፡**

1. ልጁ መጽሀፉን ያነባል
2. ጓደኞቹ ቶላ ከበደ ሕይወት እና ከሪም ናቸው
3. አለባቸው በግ ፍየል በሬ ላም እና ፈረስ ያግዳል
4. ለቤት መስሪያ የተለያዩ ግብዓቶች ያስፈልጋሉ እነሱም እንጨት ድንጋይ ሲሚንቶ አሸዋ ሚስማር ቆርቆሮ እና የመሳሰሉት ናቸው
5. አንድ ተማሪ ትምህርት ቤት ሲሄድ የሚከተሉት የመማሪያ ቁሳቁሶች ያስፈልጉታል እነዚህም ቁሳቁሶችም ደብተር እርሳስ እስክሪፕቶ እና መጽሃፍ ናቸው

**ክፍለጊዜ ስምንት**

**መልመጃ ሰባት**

## ትምህርት አምስት፡ ቃላት

**በዚህ የትምህርት ይዘት ስር የቀረቡት ጥያቄዎች የቃላት ችሎታችሁን እንድታሳድጉ የሚረዱ ናቸው፡፡ ለጥያቄዎቹ ተገቢውን መልስ በጽሁፍ ስጡ፡፡**

**ሀ. ከስራቸው ለተሰመረባቸው ቃላት አገባባዊ ፍች ስጡ፡፡**

1. ከፍተኛ ስሜትን ለመጎናጸፍ ብለው <u>የሚያጨሷቸው</u> … (አንቀጽ 1 ሶስተኛ መስመር)
2. እንደ <u>ቀልድ</u> አንድ ብለው የጀመሩት ሲውል ሲያድሩ የህይወታቸው አካል ይሆንና ………(አንቀጽ 1 ዘጠነኛ መስመር)

3. በተማሪ ወጣቶች ላይ <u>የውጤት</u> ማሽቆልቆል … (አንቀጽ 3 አንደኛ መስመር)
4. በዚህ ምክንያት <u>በንብረት ላይ</u> ጉዳት ከማድረስ ባሻገር ለአካል ጉዳተኝነትና …..(አንቀጽ 4 ሰባተኛ መስመር)
5. የእድገት ውስንነት፣ <u>ተስፋ</u> መቁረጥ፣ መገለል፣ ስነልቦናዊና ማህበራዊ ችግሮች…(አንቀጽ 4 አንደኛ መስመር)

ክፍለጊዜ ዘጠኝ

## ትምህርት ስድስት፡ ሰዋስው

**ከዚህ በታች የቀረቡት ማስታወሻና ጥያቄዎች የሰዋስው ችሎታችሁን እንድትጠቀሙ የሚረዱ ናቸው፡፡ በመሆኑም ለጥያቄዎቹ ተገቢውን መልስ በጽሁፍ ስጡ፡፡**

### ማስታወሻ

**ድርብ ዓረፍተነገር**

ምሳሌ፡

1. የእያንዳንዱ ቤተሰብ ቁጥር ጨምሯል።
2. የሕዝብ ቁጥር በፍጥነት ማደጉ አይቀርም።

የእያንዳንዱ ቤተሰብ ቁጥር ጨምሯል **<u>ስለዚህ</u>** የሕዝብ ቁጥር በፍጥነት ማደጉ አይቀርም።

ከቀረቡት ምሳሌዎች ነጠላ ዓረፍተነገሮችን በተለያዩ አያያዦች በማጣመር ድርብ ዓረፍተነገር መመስረት መቻሉንና የሚጣመሩት ነጠላ ዓረፍተነገሮች የሃሳብ አንድነት ሊኖራቸው እንደሚገባ መገንዘብ ያስፈልጋል።

**መልመጃ ስምንት**

**ሀ. ከላይ በቀረበው ምሳሌ መሰረት የሚከተሉትን ነጠላ ዓረፍተነገሮች ተገቢ የሆኑ አያያዥ ቃላት በመጠቀም ድርብ ዓረፍተነገሮችን መስርቱ።**

| በዚህ ምክንያት | ስለሆነም | ነገር ግን | ይሁን እንጂ |
|---|---|---|---|

1. ሁልጊዜ ያረፍዳል።
   አባቱ በጣም ይናደዱበታል።
2. የተማሩ እናቶች ልጆቻቸውን ያስጠናሉ።
   ልጆቻቸው ጎበዞች ናቸው፡፡
3. የክረምት ዝናብ በጥሩ ሁኔታ ዘንቧል።
   የተዘራው እህል በደንብ አልበቀለም።
4. በርትቶ ነግዷል።
   ብዙ ብር የለውም።

# ምእራፍ ዘጠኝ

# አርበኝነት

## የሚጠበቁ ውጤቶች

**ከዚህ ምእራፍ ትምህርት በኋላ ፡-**

- ያዳመጣችሁትን ጽሁፍ መልእክት ከነባራዊ ህይወት ጋር ታዛምዳላችሁ፡፡
- ስለአርበኝነት ጽንሰሀሳብ ትገልጻላችሁ፡፡
- ለውሱን አላማ ታነባላችሁ፡፡
- በተሰጣችሁ ስእል ላይ መግለጫ ትጽፋላችሁ፡፡
- ተዘውታሪ ላልሆኑ ቃላት ፍቺ ትሰጣላችሁ፡፡
- ድብልቅ ዓረፍተነገሮችን ትመሰርታላችሁ፡፡

**ክፍለጊዜ አንድ**

## ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

**የማዳመጥ ክሂላችሁን እንድትጠቀሙ የሚረዱ ጽሁፍ እና የመልመጃ ጥያቄዎች ቀርበዋል፡፡ በትኩረት በማዳመጥ ጥያቄዎቹን በተገቢው መንገድ ስሩ፡፡**

# ሌፍተናንት ኮሎኔል አብዲሳ አጋ



## ቅድመማዳመጥ ጥያቄዎች

ሀ. ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቄዎች በቡድን በመሆን በቃል መልስ ስጡ፡፡

1. ስለአርበኝነት የምታውቁትን ለመምህራችሁ ተናገሩ፡፡
2. አገራችን ካፈራቻቸው ጀግኖች አርበኞች እነማንን ታውቃላችሁ?
3. ስለ ሌፍተናንት ኮሎኔል አብዲሳ የምታውቁትን ለመምህራችሁ ተናገሩ?

## የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎች

1. ከምታዳምጡት ጽሁፍ አዳዲስ ቃላትን በማስታወሻ ደብተራችሁ መዝግቡ፡፡
2. ቀጥሎ የሚመጣው ምንባብ ስለምን የሚያወሳ ይመስላችኋል?

## የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች

### መልመጃ አንድ

**ሀ. ለቀረቡት ጥያቄዎች ያዳመጣችሁትን ጽሁፍ መሰረት በማድረግ ከቀረቡት አማራጮች ትክክለኛውን መልስ ስጡ፡፡**

1. ሌፍተናንት ኮሎኔል አብዲሳ አጋ የተወለዱት የት ነው?

   ሀ. ሀረር ሐ. ባሌ

   ለ. አርሲ መ. ወለጋ

2. ፋሽስት ጣሊያንን ለመመከት ከሌሎች አርበኞች ጋር በመሆን ዘመቱ፡፡ ከስሩ የተሰመረበት ቃል ፍች የሚያመለክተው

   ሀ. ለመውረር ሐ. ለመቀበል

   ለ. ለመከላከል መ. ለመሸኘት

3. "ፋሽስቶችም" የሚለው ቃል በጽሁፉ ውስጥ ማንን ያመለክታል?

   ሀ. አርበኞችን ሐ. ፋሽን ለባሾችን

   ለ. ባለአገሮችን መ. ወራሪዎችን

4. ብርድልብስ ተልትለው እየቀጣጠሉ ቋጠሩ፡፡ ከስሩ የተሰመረበት ቃል ፍቺው

   ሀ. አስረው ሐ. ጠቅልለው

   ለ. በቀጭኑ ቀደው መ. ወርውረው

5. "እስረኞች|" የሚለው በምንባቡ ውስጥ ምንን ያመለክታል?

   ሀ. ታራሚዎችን ሐ. የተለቀቁትን

   ለ. በገመድ የተቋጠሩትን መ. የተፈቱትን

**ለ. ለሚከተሉት ቃላትና ሀረጋት በጽሁፍ ተቃራኒ ፍቺ ስጡ፡፡**

1. ቂም ቋጠሩ
6. በተነች

2. ለቀቁ
3. አሰሩዋቸው
4. ጀግና
5. ቆሰሉ
7. መሬት ጥለው
8. ጠላት
9. ተማረኩ
10. አደጉ

ሐ. ያዳመጣችሁትን ጽሁፍ መሰረት በማድረግ በሌፍተናንት ኮሎኔል አብዲሳ አጋ ቦታ እናንተ ብትሆኑ ምን ታደርጉ እንደነበር በቡድን ተወያዩና ሀሳባችሁን ለክፍል ተማሪዎች አቅርቡ፡፡

ክፍለጊዜ ሶስት

## ትምህርት ሁለት፡ መናገር

**የሚከተሉት ተግባራት የንግግር ክሂላችሁን ውጤታማ በሆነ መልኩ እንድትጠቀሙ አስተዋጽኦ ስላላቸው ለተግባራቱ ተገቢውን መልስ በቃል ስጡ፡፡**

### ተግባር አንድ

ሀ. በሚከተሉት ሙያዎች የሚሳተፉ ሰዎች ለሀገር በሚያበረክቱት አስተዋጽኦ ዙሪያ መረጃ በማሰባሰብ እና በቡድን በመወያየት ዘገባውን በቃል ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ፡፡

1. ወታደር
2. ሀኪም
3. መምህር
4. ሾፌር
5. የህግ ባለሙያ

ለ. እናንተ ወደፊት ስታድጉ በምን ሙያ ለአገራችሁ አስተዋጽኦ ማበርከት እንደምትፈልጉ ሀሳባችሁን ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተራ በተራ በቃል አቅርቡ፡፡

**ክፍለጊዜ አራት**

**የተለያዩ የአርበኝነት መገለጫ ጽንሰሀሳቦች ከዚህ በታች ቀርበውላችኋል፡፡ ጽንሰሀሳቦቹን በተመለከተ ሰዎችን በመጠየቅ ያገኛችሁትን መረጃ ለመምህራችሁ ተናገሩ፡፡**

1. የግብርና አርበኛ
2. የጦርሜዳ ውሎ አርበኛ
3. የስፖርት አርበኛ
4. የትምህርት አርበኛ
5. የጤና አርበኛ
6. የንግድ መስክ አርበኛ

**ክፍለጊዜ አምስት**

## ትምህርት ሶስት፡ ምንባብ

**የማንበብ ክሂላችሁን እንድትጠቀሙ የሚረዱ ምንባብ እና የመልመጃ ጥያቄዎች ቀርበዋል፡፡ ምንባቡን በትኩረት አንብባችሁ ጥያቄዎቹን በተገቢው መንገድ ስሩ፡፡**



አቡነ ጴጥሮስ (መገርሳ በዳሳ)



የአቡነ ጴጥሮስ ሀውልት

## ቅድመምንባብ ጥያቄዎች

**ሀ. ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቄዎች በቃል መልሱ፡፡**

1. አርበኝነት ምንድን ነው?
2. የምታውቋቸውን ለአገራቸው ትልቅ ውለታ የዋሉ ሰዎችን ስም ዘርዝሩ፡፡

## አቡነ ጴጥሮስ (መገርሳ በዳሳ)

መገርሳ በዳሳ የአቡነ ጴጥሮስ ቤተሰብ ያወጡላቸው የልጅነት ስማቸው ነው፡፡ አቡነ ጴጥሮስ የሚለው ስያሜ ደግሞ በኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን በአገልግሎት ያገኙት የማእረግ ስማቸው ነው፡፡ አቡኑ በሰሜን ሸዋ በ1875 ተወለዱ፡፡

ጣሊያኖች በአድዋ ላይ ድል ከተደረጉ ከ40 ዓመት በኋላ ኢትዮጵያን በባርነት ለመግዛት መጥተው ከተማ እና ገጠሩን ሲይዙ አቡነ ጴጥሮስ ሰዎች ጠላትን ከሀገራቸው አባረው እንዲያስወጡ ይመክሩ ነበር፡፡ በመሆኑም ፋሽስት ጣሊያን ለብዙ ጊዜ የግድያ ዛቻ ለአቡኑ ይልኩላቸው ነበር፡፡ በዚህ ያልተደናገጡት አቡኑ የሀገራቸውን ህዝቦች “በርቱ ታገሉ” በማለት ሲያውጁ ጣሊያኖች በኢትዮጵያውያን ስር መቆም አልቻሉም፡፡

በአቡኑ አቋም የተረበሹት ጣሊያኖች አቡነ ጴጥሮስን “የፓትሪያሪክነት ስልጣንና የፈለከውን የግል ፍላጎትህን የሚያሟላልህን ነገር እናደርግልሃለን” በማለት ያባብሏቸው ጀመር:: አቡነ ጴጥሮስ ግን “ለሆዴ ሳይሆን ህሊናዬ ባዘዘኝ ነው የምመራው:: ስልጣን ከፈጣሪዬ ተሰቶኛል:: እናንተ አይደላችሁም የምትሰጡኝ!” በማለት በንቀት መለሱላቸው፡፡

## የማንበብ ጊዜ ጥያቄዎች

1. በመጀመሪያውና በሁለተኛው አንቀጽ የተገነዘባችሁትን ሀሳብ ለመምህራችሁ ተናገሩ፡፡
2. ቀጥሎ የሚመጣው አንቀጽ ስለምን የሚያወሳ ይመስላችኋል?

አቡነ ጴጥሮስ የጣልያኖችን ማባበል ባለመቀበላቸውና ለሆዳቸው ባለማደራቸው ታሰሩ፡፡ ሰዎች በተሰበሰቡበትም አቡኑን “የመጨረሻ እድል እንስጥህና በህዝቡ ፊት ይቅርታ ጠይቅና ከእስር ቤት እንለቅሃለን” ቢሏቸው እሳቸው ግን በቃላቸው ጸኑ፡፡ በአደባባይ የተሰበሰበውን ህዝብም ጣልያኖች ሀገሩን በባርነት ለመግዛት እንደመጡና የሀገሬውም ህዝብ አጥብቆ እንዲታገላቸው በድፍረት ተናገሩ፡፡ ጣሊያኖችም በንዴት ተቃጠሉ፡፡ እንቢ ካልክ ወዲያ በማለት ሀምሌ 22/1928 ባንዳዎችን ለቀውባቸው በጥይት ተኩሰውባቸው ገደሉዋቸው፡፡ አንድ ሰው ሲሞት ሌላው ደንግጦ ከድርጊቱ የሚቆጠብ መስሏቸው ነበር፡፡ ነገር ግን ትግሉ እየተፋፋመ እንደሚሄድ አልተረዱም ነበር፡፡

የአቡኑ ተምሳሌትነት በዚያን ጊዜ ለበርካታ ወጣት ሴቶችና ወንዶች ምሳሌ በመሆን ለጣሊያን እምቢ አንገዛም በማለት እንዲነሳሱ ምክንያት ሆነ፡፡ ጀግንነታቸውና ሀገር ወዳድነታቸው እውነቱ ስለተረጋገጠ ከዚህ አለም ካረፉ ከአስር ዓመት በኋላ ሀምሌ 16/1939 በእምነቱ በተሰጣቸው በአቡን ስም መታሰቢያ ሀውልታቸው በአዲስ አበባ ተሰራላቸው፡፡ ቦታውም አሁንም ድረስ አቡነ ጴጥሮስ አደባባይ ተብሎ ይጠራል፡፡

*(ሸለማ ካቤ፡፡2009፡፡ የኦሮሞ ጀግኖች ታሪክና ሌሎች፡፡አዲስ አበባ፤ግራፊክ ማተሚያ ቤት)*

## የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች

### መልመጃ ሁለት

ሀ. የቀረበውን ምንባብ መሰረት በማድረግ ከዚህ በታች የቀረቡት ሀሳቦች ትክክል ከሆነ እውነት ካልሆነ ግን ሀሰት በማለት መልሱ፡፡

1. አቡነ ጴጥሮስ ወላጆቻቸው ያወጡላቸው ስም መገርሳ በዳሳ ይባላል፡፡
2. የአቡነ ጴጥሮስ ትውልድ ቦታ ባሌ ነው፡፡
3. አቡኑ የተወለዱት በ1975 ዓ.ም. ነው፡፡
4. የኢጣሊያን ወራሪ ሀይል አቡነ ጴጥሮስን በጥቅም ለመደለል ፈልገው አልተሳካላቸውም፡፡
5. የአቡነ ጴጥሮስ ህይወት ያለፈው ታመው ነው፡፡
6. አቡኑ ከእምነት አስተምህሮት በተጨማሪ ሰዎች ሀገራቸውን ከጠላት እንዲከላከሉ ያስተምሩ ነበር፡፡
7. አቡነ ጴጥሮስ ሰዎች በተሰበሰቡበት ፊት ቆመው የተናገሩት ነገር ጣሊያኖችን አስደስቷቸዋል፡፡
8. ጣሊያኖች የግድያ ዛቻ ለአቡኑ ስላደረሷቸው ፈርተው ከድርጊታቸው ተቆጠቡ፡፡
9. ጣሊያኖች በአድዋ ድል ከተደረጉ ከ40 ዓመት በኋላ ነው መጥተው ኢትዮጵያን የወረሯት፡፡
10. የአቡነ ጴጥሮስ የጀግንነትና አገር ወዳድነት ተግባር ለትውልድ አርዓያ ነው፡፡

## ክፍለጊዜ ስድስት

**ለ. በ "ሀ" ስር ለቀረቡት ቃላትና ሀረጋት ከ "ለ" ስር ተመሳሳይ ፍችያቸውን በመምረጥ አዛምዱ፡፡**

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. ዛቻ | ሀ. ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ |
| 2. ተደናገጡ | ለ.ተገኘ |
| 3. ባንዳ | ሐ. የሚታቀብ |
| 4. አባበሏቸው | መ. ተረበሹ |
| 5. የመጨረሻ እድል | ሠ.ማስፈራራት |
| 6. እየተፋፋመ | ረ. አታለሏቸው |
| 7. የሚቆጠብ | ሰ. በልበ ሙሉነት |
| 8. ተምሳሌት | ሸ. እየሞቀ |
| 9. በድፍረት | ቀ. አይሆንም |
| 10. እምቢ | በ. ምሳሌ መሆን |

**ሐ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት ትክክለኛውን መልስ ምረጡ፡፡**

1. አቡነ ጴጥሮስ የአልገዛምነት አቋማቸውን የገለጹት በየትኛው አንቀጽ ነው?

   ሀ. አንቀጽ አራት  ሐ.አንቀጽ አንድ

   ለ.አንቀጽ ሶስት  መ.አንቀጽ ሁለት

2. በአንቀጽ ሶስት የአቡኑ ንግግር በትእምርተ ጥቅስ ውስጥ የተቀመጠበት ምክንያት __________ ነው፡፡

   ሀ. የታሪኩ ጸሀፊ ሀሳብ ስለሆነ

   ለ. ጸሀፊው የአቡኑን ንግግር በቀጥታ ስለተጠቀመ

ሐ. ለአቡኑ ንግግር ትኩረት ለመስጠት ስለተፈለገ

መ. ለአዲስ ጽንሰ ሀሳብ ትኩረት ለመስጠት ስለተፈለገ

3. በአንቀጽ ሶስት አቡኑ "ለሆዴ ሳይሆን ህሊናዬ ባዘዘኝ ነው የምመራው..." ሲሉ ______ ማለታቸው ነው፡፡

ሀ. አልደለልም ሐ. እገዛለሁ

ለ. ለህሊናዬ አላደርኩም መ. እታዘዛለሁ

4. "ትግሉ <u>እየተፋፋመ</u> እንደሚሄድ አልተረዱም ነበር፡፡" ለተሰመረበት ቃል ፍቺ የሚሆነው የቱ ነው?

ሀ. እየቀዘቀዘ ሐ. እየተጧጧፈ

ለ. እየደከመ መ. እያዘገመ

5. "በአቡኑ ስም <u>መታሰቢያ</u> ሀውልታቸው በአዲስ አበባ ተሰራላቸው፡፡" የተሰመረበት ቃል ፍቺ________ ነው፡፡

ሀ. መቃብር ሐ. ማልቀሻ

ለ. ማረፊያ መ. ማስታወሻ

ክፍለጊዜ ሰባት

## ትምህርት አራት፡ መጻፍ

**ከዚህ በታች የቀረቡት ተግባራት በተለያዩ ጉዳዮች ዙሪያ እንድትጽፉ የሚረዱ ስለሆኑ ለተግባራቱ ተገቢውን መልስ በጽሁፍ ስጡ፡፡**

### ተግባር ሁለት

ሀ. ከዚህ በታች አንድ ምስል ቀርቦላችኋል፡፡ የቀረበውን ምስል ተመልክታችሁ የተረዳችሁትን በሁለት አንቀጽ ጽፋችሁ ለክፍል ተማሪዎች አቅርቡ፡፡



ለ. ምስሉን በተመለከተ ሀሳቡን በጽሁፍ በደንብ ያቀረበው ማን ነው?

ሐ. በምን በምን ምክንያት ጥሩ እንደሆነ ተናገሩ፡፡

**ክፍለጊዜ ስምንት**

**ተግባር ሶስት**

**ሀ. ከሚከተሉት የምግብ አዘገጃጀት አንዱን በመምረጥ የአዘገጃጀት ቅደም ተከተሉን በጽሁፍ ለቡድን አባላት አቅርቡ፡፡**

1. ቡና አፈላል
2. እንጀራ መጋገር
3. የጠላ አጠማመቅ

**ለ. የተዘጋጃችሁበትን ጽሁፍ ከጓደኞቻችሁ ጋር በመለዋወጥ በማረም የተገኘውን ስህተት ጠቁሙ፡፡**

**ክፍለጊዜ ዘጠኝ**

# ትምህርት አምስት፡ ቃላት

**በዚህ የትምህርት ክፍል ተዘውታሪ ያልሆኑ ቃላትን እንድትጠቀሙ የሚያግዙ መልመጃዎች ቀርበዋል፡፡ በስሩ ለቀረቡት ጥያቄዎችም ተገቢውን መልስ በጽሁፍ ስጡ፡፡**

**መልመጃ ሶስት**

**ከዚህ በታች ያልተሟሉ ዓረፍተነገሮች ስለቀረቡ በሳጥኑ ውስጥ የተሰጧችሁን ቃላት በመጠቀም አሟሏቸው፡፡**

| | | | |
|---|---|---|---|
| መታሰቢያ | ማረሚያ ቤት | ጸኑ | አረፉ |
| ባንዳ | ህሊና | ዛቻ | ማእረግ |

1. ወንጀል የሰራ ሰው______ይገባል፡፡
2. ልጁ ከወለጋ ዩኒቨርስቲ በ ______ተመረቀች፡፡
3. የተጣላው ሰውዬ______ አሳሰበው፡፡
4. ሰው በጥቅም ከመደለል ለ ______ ማደር ይገባል፡፡
5. በጣሊያን ወረራ ጊዜ የአርበኞችን ትግል ያደናቅፍ የነበረው ______ ነው፡፡
6. አዛውንቱ  በተወለዱ በ120 ዓመታቸው______ ፡፡
7. ለጀግኖች______ ሀውልት ሊቆምላቸው ይገባል፡፡
8. አቡነ ጴጥሮስ በአልገዛምነት አቋማቸው_______ ፡፡

## ክፍለጊዜ አስር

**መልመጃ አራት**

**ከዚህ በታች በቀረበው ጽሁፍ ውስጥ ለተሰመረባቸው ቃላትና ሀረጋት አገባባዊ ፍች ስጡ፡፡**

አገሬ <u>ደጋ</u> ነው፡፡ እንግዳ ቀርቶ ነዋሪውም የማይለምደው <u>ውርጭ</u> ውስጥ ነው ያደግሁት፡፡ አሰላ ከተማ ሆናችሁ ቀና ስትሉ፣ <u>ባለግርማው</u> ጭላሎ ተራራ <u>ለሰማይ ለምድር ከብዶ</u> ይታያችኋል፡፡ ጉም ከላዩ ላይ

አይጠፋም፡፡ አርሲዎችም ከአሰላ ከተማ ይልቅ ከዚያ ተራራ ግርጌ ሰፍረው፣ በእርሻ ስራና በከብት እርባታ ተሰማርተው ይኖራሉ፡፡

ከግዙፉ ጭላሎ ተራራ የሚነሳው ጉም በድንገት መጥቶ ከተማዋን ሲያለብሳት፣ በጭጋጉ ምክንያት እይታችን ከአንድ እርምጃ በታች የተወሰነ ቢሆንም ብጣቂ ልብሳችንን ለብሰን እንሯሯጣለን፡፡ ሁሉም ነገር ድፍንፍን ባለበት ሁኔታ የወላጆቻችንም እለታዊ እንቅስቃሴ ለሰዓታት ይገታል፡፡

*(ቤተልሄም ታፈሰ፡፡2013፡፡እኔና የኤልተቪ ምስጥሮቼ፡፡ፋርኢስት ትሬዲንግ ሓላ.የተ.የግ ማኅበር፡፡ አዲስ አበባ፡፡)*

**ክፍለጊዜ አስራ አንድ**

## ትምህርት ስድስት፡ ሰዋስው

**የሚከተለው ማስታወሻ ስለድብልቅ አረፍተነገር የሚያወሳ ነው፡፡ በማስታወሻው መሰረት ከስሩ ለቀረቡት ጥያቄዎች ተገቢውን መልስ ስጡ፡፡**

**ማስታወሻ**

**ድብልቅ ዓረፍተነገር**

ድብልቅ ዓረፍተነገር ቢያንስ ከአንድ ጥገኛ ሐረግ (ዓረፍተነገር) እና መደበኛ ሐረግ (ነጠላ ዓረፍተነገር) ይመሰረታል። ድብልቅ ዓረፍተነገር ምን ጊዜም ቢሆን የሚኖረው አንድ ማሰሪያ አንቀጽ ወይም ግስ ብቻ ነው። ጥገኛ ሐረጋት ግን ከአንድ በላይ ሊሆኑ ይችላሉ።

ምሳሌ፡ 1. ዛሬ በጣም ስለደከመኝ ወደ ቤት መሄድ አለብኝ።

… ስለደከመኝ = ጥገኛ ሐረግ (ዓረፍተነገር)

… አለብኝ = መደበኛ ሐረግ (ማሰሪያ አንቀፅ)

2. በጊዜ ምሳዬን በልቼ፣ ቡና ጠጥቼ፣ አልጋዬ ላይ ተጋድሜ ማንበብ አለብኝ።

… በልቼ … ጠጥቼ… እና ተጋድሜ - ጥገኛ ሐረጋት

አለብኝ = ማሰሪያ አንቀጽ /መደበኛ ሐረግ

## መልመጃ አምስት

ሀ. የሚከተሉትን ዓረፍተ ነገሮች ድርብ ዓረፍተ ነገር ወይም ድብልቅ ዓረፍተ ነገር በማለት ለይታችሁ ጻፉ፡፡

1. ውሃው ስለቀዘቀዘ አሁን መታጠብ እችላለሁ፡፡
2. ጫወታውን አሸንፈዋል፤ ይሁን እንጂ ወደሚቀጥለው ውድድር አላለፉም፡፡
3. ዘወትር ያጠናል ነገር ግን ፈተናውን ማለፍ አልቻለም፡፡
4. መኪናው ስለመጣ ከቤት ቶሎ መውጣት አለብኝ፡፡
5. ትምህርት ቤት ከተዘጋ ሀረር ሄጄ ዘመዶቼን እጠይቃለሁ፡፡
6. ጥሩነሽ ፈጣን ሯጭ ስለሆነች በተወዳደረችበት መስክ ድል ትቀዳጃለች፡፡
7. መምህሬን በጣም አከብረዋለው በዚህ የተነሳ ትምህርቱ ይገባኛል፡፡
8. ዶሮዬን ስለሰረቁብኝ በጣም ተናደድኩኝ፡፡

ለ. ሶስት ድርብ እና ሶስት ድብልቅ ዓረፍተነገሮችን መስርቱ፡፡

# ምእራፍ አስር

## ቃላዊ ግጥም

### የሚጠበቁ ውጤቶች

ከዚህ ምእራፍ ትምህርት በኋላ፡-

- ያዳመጣችሁትን ምንባብ መልእክት ትናገራላችሁ፡፡
- የቀረበላችሁን ቃላዊ ግጥም የሚመስል ሌላ ቃላዊ ግጥም ታቀርባላችሁ፡፡
- ግጥምን በተገቢው የድምጽ ቅላጼ ታነባላችሁ፡፡
- የቀረበላችሁን ቃላዊ ግጥም መሰረት በማድረግ ተመሳሳይ ግጥሞችን ትጽፋላችሁ፡፡
- በተለዋጭ ዘይቤ የቀረቡትን ቃላት ትገልጻላችሁ፡፡
- በጽሁፍ ውስጥ አያያዥ ቃላትን ትጠቀማላችሁ፡፡

ክፍለጊዜ አንድ

## ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

ከዚህ በታች የሚቀርብላችሁን ጽሁፍና ጥያቄዎች የማዳመጥ ክሂላችሁን እንድትጠቀሙ የሚረዱ ናቸው፡፡ ስለሆነም ለጥያቄዎቹ ተገቢ መልስ ስጡ፡፡

### የስራ ዘፈኖች

### ቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች

ለሚከተሉት ጥያቄዎች በቡድን ከተወያያችሁ በኋላ በቃል መልስ ስጡ፡፡

1. የቃላዊ ግጥም ምንነት ለመምህራችሁ ተናገሩ፡፡
2. ሰዎች በግብርና ስራ ላይ በህብረት ሲሰሩ ከሚገጥሟቸው ቃላዊ ግጥሞች የምታውቁትን ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ፡፡

## የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎች

1. የሚነበብላችሁን ጽሁፍ እያዳመጣችሁ የየአንቀጾቹን ፍሬ ሀሳብ መዝግቡ፡፡
2. በመቀጠል የሚነበብላችሁ ጽሁፍ ስለምን የሚያወሱ ይመስላችኋል?

## የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች

### መልመጃ አንድ

**ሀ. ከስራቸው ለተሰመረባቸው ቃላት ከተሰጡት አማራጮች ትክክለኛ ፍቺ የሚሆነውን ምረጡ፡፡**

1. በአብዛኛው የገጠሩ ህዝብ በጋራም ሆነ በተናጠል አንድ ስራ <u>በሚያከናውንበት</u> ጊዜ ያንጎራጉራል፡፡
   - ሀ. በሚጨፍርበት ጊዜ
   - ሐ. በሚተገብርበት ጊዜ
   - ለ. በሚያዳምጥበት ጊዜ
   - መ. በሚያይበት ጊዜ
2. <u>በተናጠልም</u> ቢሆን ማንጎራጎር የተለመደ ነው፡፡
   - ሀ. በቡድን
   - ሐ. በህብረት
   - ለ. በግል
   - መ. በአንድነት
3. ልጅ <u>አዝላ</u> ስታባብል እንኳ እየዘፈነች ነው፡፡
   - ሀ. ተሸክማ
   - ሐ. አስተኝታ
   - ለ. አውርዳ
   - መ. አስቃ
4. የስራ ዘፈኖች ስራው <u>አሰልቺ</u> እንዳይሆንና ተሳታፊዎቹ ድካም እንዳይጫጫናቸው ያግዛሉ፡፡
   - ሀ. አስደሳች
   - ሐ. አጫዋች
   - ለ. አስቂኝ
   - መ. አድካሚ

5. የስራ ዘፈኖችን <u>በውል</u> ለማወቅ በግብርና ላይ የሚሰሙ ግጥሞችን በምሳሌነት ወስደን እንመልከት፡፡

ሀ. በጥቂቱ ሐ. በትክክል

ለ. በፍጥነት መ. ቀስ በቀስ

6. በእያንዳንዱ የስራ አይነት ላይ የሚሰሙት ግጥሞች ከስራው እንቅስቃሴ ጋር <u>የተጣጣሙ</u> ናቸው፡፡

ሀ. የማይገናኙ ሐ. የተገናኙ

ለ. የሚወዳደሩ መ. አብሮ የማይሄድ

7. ገበሬዎች <u>አያሌ</u> ግጥሞችን እየደረደሩ ያዜማሉ፡፡

ሀ. ጥቂት ሐ. ሩቅ

ለ. ትንሽ መ. ብዙ

8. ዜማውም ሆነ ግጥሙ ተሳታፊዎቹን <u>እንዲተጉ</u> ይረዳል፡፡

ሀ. እንዲሰንፉ ሐ. እንዲቀሩ

ለ. እንዲጎብዙ መ. እንዲተኙ

9. ገበሬው በሬዎቹን <u>ጠምዶ</u> በሚያርስበት ጊዜ እንደባህሉ ይዘፍናል፡፡

ሀ. ፈቶ ሐ. ከስራ አስቀርቶ

ለ. አቆራኝቶ መ. ነገር ፈልጎ

10. ከስራው እንቅስቃሴ በተገኘ <u>እውቂያ</u> ግምት በመውሰድ ጥቂት ምሳሌዎችን ማየት ይቻላል፡፡

ሀ. ቸልተኝነት ሐ. ጓደኝነት

ለ. መርሳት መ. ልምድ

ክፍለጊዜ ሁለት

**ለ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች በቃል መልስ ስጡ፡፡**

1. የገጠሩ ማህበረሰብ ግጥም እየደረደረ በመጨፈርና በማንጎራጎር ከሚሰራቸው ስራዎች ምሳሌዎችን በመጥቀስ አብራሯቸው፡፡
2. ሴቷ ምን ምን ስትሰራ እንደምታንጎራጉር ወይም እንደምታዜም ምሳሌውን መሰረት በማድረግ ሶስቱን የክዋኔ አጋጣሚዎች ዘርዝሩ፡፡
   ምሳሌ፡ እህል ስትፈጭ
3. የስራ ላይ የቃል ግጥሞችና ዜማዎች ለገበሬው ከሚሰጡት ጥቅሞች ምሳሌውን መሰረት በማድረግ ሶስቱን ዘርዝሩ፡፡
   ምሳሌ፡ ድካም እንዳይሰማቸው ወይም እንዲበረቱ

ክፍለጊዜ ሶስት

# ትምህርት ሁለት፡ መናገር

**የሚከተሉት ተግባራት የመናገር ክሂላችሁን እንድትጠቀሙ የሚያግዙ ናቸው፡፡ ስለሆነም ለተግባራቱ ተገቢ መልስ ስጡ፡፡**

## ተግባር አንድ

ሀ. በቡድን በመደራጀት በልጆች ጨዋታ ጊዜ ከሚዜሙት ግጥሞች መካከል አንዱን መርጣችሁ በማጥናት ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ፡፡

ለ. የሚከተለውን አጭር የልጆች ጨዋታ ግጥም መምህራችሁ ሲያነቡላችሁ እናንተም ደግማችሁ በሉ፡፡

ጉልበቴ በርታ በርታ
ጉልበቴ በርታ በርታ
አበላሃለሁ የሽንብራ ቂጣ
አሁንም አይደል ወደማታ
ወደማታ ወደማታ

ሐ. ሌሎች የልጆች ጨዋታ ግጥሞችን ከነዜማቸው ለጓደኞቻችሁ በቃል አቅርቡ፡፡

# ትምህርት ሶስት፡ ምንባብ

**የማንበብ ክሂላችሁን እንድትጠቀሙ የሚረዱ ቃላዊ ግጥሞችና እና የመልመጃ ጥያቄዎች ቀርበዋል፡፡ ቃላዊ ግጥሞቹን በትኩረት አንብባችሁ ጥያቄዎቹን በተገቢው መንገድ ስሩ፡፡**

## የቅድመንባብ ጥያቄዎች

**በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ በቡድን ከተወያያችሁ በኋላ ለመምህራችሁ በቃል መልስ ስጡ፡፡**

1. ሰዎች በምን በምን አጋጣሚዎች ላይ ባህላዊ ዘፈኖችን ሊዘፍኑ ይችላሉ?
2. የሰርግ ስነስርዓትን በተመለከተ የታዘባችሁትን ለክፍል ተማሪዎች ተናገሩ፡፡

## የሰርግ ግጥም

በግጥም ከሚቀርቡና ከሚዜሙ የስነቃል አይነቶች አንዱ ባህላዊ ዘፈን ነው፡፡ ባህላዊ ዘፈኖች በተለያዩ አጋጣሚዎች የሚዘፈኑ ናቸው፡፡ ከባህላዊ ዘፈኖች የስራ ዘፈን፣ የክብረበዓል ዘፈን፣ የሰርግ ዘፈን፣ የፍቅር ዘፈን ወዘተ… ይጠቀሳሉ፡፡ ከነዚህ መካከል በሰርግ ስነስርዓት ሙሽራውንና ሙሽሪትን በተመለከተ ከሚባሉ ግጥሞች የሚከተሉት ይጠቀሳሉ፡፡

## የማንበብ ጊዜ ጥያቄዎች

1. ከላይ በቀረበው አንቀጽ ምን እንደተረዳችሁ ለመምህራችሁ ተናገሩ፡፡
2. ግጥሙን በጥሩ ቃና ያነበቡ ተማሪዎችን ለይታችሁ ተናገሩ፡፡
3. ግጥሙ ሲነበብላችሁ አዳዲስ ቃላትን መዝግቡ

ጠቢብ የሠራውን በትር የሚመስል፤
ኧረ ጠይም ጠይም ጠይም ዓሳ መሳይ፣
እኔ አናቷን ብሆን ለሰውም አላሳይ፡፡
እሠይ ያገሬ ልጅ ወጣቱ ወጣቱ፤
ሲቀመጥ ጨዋታው ሲሔድ የግርባቱ፡፡
ያድንብላል ያድንብላል፣
የሙሽሪት አይን ያባብላል፡፡
ማርና ቅቤ ነው ሙሽሪት ቀለቧ፣
እንደ ፈረስ ጭራ ቀጭን ነው ወገቧ፡፡
እቴ ሙሽራዬ ተይ አይሆንልሽም፣
አዲሱ ሙሽራ ውሃ አይጠጣልሽም፡፡
ሸልሙት ሙሽራውን፣
ሸልሙት ሙሽራውን፣
የእኛን ሙሽራ ኩሩውን፡፡
ፈርሞ ሲወጣ ፈርሞ ሲወጣ፣
ያረገው ቦላሌ ያረገው ባርኔጣ፡፡
እየው ከዚያ ማዶ ንብ ወጣ ንብ ወጣ፣
ሙሽራው ነው መሰል ተሸላልሞ ወጣ፡፡
አያ ሙሽራው ታድለሀል፣
የወይን ሐረጊቱን አግብተሀል፣
እንቡጥ ፅጌረዳ መስለሀል፡፡

## የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች

### መልመጃ ሁለት

ሀ. የሚከተሉት ቃላትና ሀረጋት በግጥሙ ውስጥ የተጠቀሱ ናቸው፡፡ ለቃላቱ እና ለሀረጋቱ አውዳዊ ፍቺያቸውን ግለጹ፡፡

1. በትር
2. ጠይም አሳ መሳይ
3. የግርባቱ
4. ቦላሌ
5. ተሸላልሞ
6. እንቡጥ ጽጌሬዳ
7. ድንብላል
8. ሸልሙት

ለ. ግጥሙ ሲነበብ ዜማው ተሳክቶ የቀረበባቸው ስንኞች የትኞቹ እንደሆኑ በመለየት ደግማችሁ ለጓደኞቻችሁ አንብቡላቸው፡፡

ሐ. ግጥሙ ሲነበብ ዜማው ተሳክቶ ያልቀረበባቸው ስንኞችን ከለያችሁ በኋላ እንዲሳካ አድርጋችሁ መልሳችሁ ጻፏቸው፡፡

### ተግባር ሁለት

ከላይ የቀረበላችሁ የሰርግ ግጥም ሙሽራው ሙሽሪትን እና በተመለከተ የቀረበ ነው፡፡ በዚህ መሰረት ከዚህ በፊት የምታውቋቸውን በሙሽሪት እና ዙሪያ የሚባሉ ግጥሞችን በማሰባሰብ ለምንና መቼ እንደሚባል ለክፍል ተማሪዎች ከነዜማው አቅርቡ፡፡

**ክፍለጊዜ አምስት**

መ. የሚከተሉት ቃላዊ ግጥሞች ምን ለመግለጽ እንደሚባሉ በአከባቢያችሁ የሚገኙ ሰዎችን በመጠየቅ መልሱ፡፡

ምሳሌ፡1. በበጋ እረስ ቢሉት ጸሀይን ፈራና
በሀምሌ እረስ ቢሉት ዝናቡን ፈራና
ልጁ እንጀራ ቢለው በጅቡ አስፈራራ

መልስ፡ <u>ስንፍናን ለማውገዝ የሚቀርብ የስራ ላይ ቃል ግጥም፡፡</u>

2. ትመጫለሽ ብዬ ሳይ ማዶ ሳይ ማዶ
የልጅነት አይኔ ሚሚ እንደበረዶ

______________________________

3. ልብ አልባ ነበረ የሴት ወይዘሮ እቃ
ወርቅ እንቁ ነበረ የሴት ወይዘሮ እቃ
አወይ የቴ ነገር ሄደች ሰሌን ታጥቃ

______________________________

4. ወንድምዬ
ወንድም አበባ
ይዘህ በጊዜ ግባ
የሙሽራው እናት
ይሰማሽ ኩራት

______________________________

ክፍለጊዜ ስድስት

## ትምህርት አራት፡ መጻፍ

ከዚህ በታች የቀረቡት ተግባርና መልመጃዎች የመጻፍ ክሂላችሁን እንድትጠቀሙ የሚረዱ ናቸው፡፡ ለተግባሩና መልመጃዎቹ ተገቢውን መልስ በጽሁፍ ስጡ፡፡

### መልመጃ ሶስት

ሀ. የምታውቋቸውን የልጆች ጨዋታ ግጥሞች ጽፋችሁ ለክፍል ተማሪዎች ዜማውን ጠብቃችሁ አንብቡ፡፡

**ምሳሌ፡** *መሀረቤን ያያችሁ እባካችሁ*

*አላየንም መሀረብ አላየንም*

*መሀረቤን ያያችሁ እባካችሁ*

*አላየንም መሀረብ አላየንም*

**ለ. ከዚህ በታች የቀረበውን የስራ ቃላዊ ግጥም ምሳሌ በማድረግ በአከባቢያችሁ ከሚባሉ የስራ ግጥሞች የምታውቁትን ጻፉ፡፡**

**ምሳሌ፡** *ዝሩ በየገደሉ ስር*

*በቅሎ ተገዛ አሉ በአንድ ቁና ምስር*

*ተላላው ገበሬ ይውላል ከጥላ*

*ውርጭ የመሰለ ብር ከመሬት ሲፈላ*

*አላየኸውም ወይ የምስሩን ተራ*

*እንደክረምት አገቢ ሽልንጉ ሲፈላ*

**ሐ. ከዚህ በታች የቀረበውን የፍቅር ቃላዊ ግጥም ምሳሌ በማድረግ በአከባቢያችው የሚነገሩ የፍቅር የቃል ግጥም ጻፉ፡፡**

**ምሳሌ፡** *አስራ ሁለት ሆነን እንድ ሰው ወደን*

*እሷ ትስቃለች እኛ ተጨንቀን*

**ክፍል ሰባት**

**መልመጃ አራት**

**ሀ. የሚከተሉትን የቃል ግጥሞች በምሳሌው መሰረት ተንትኑ፡፡**

ምሳሌ፡1. *ረጅም መቀነት ሳይስቡት ይጠብቃል*

*የዘመኑ ፍቅር ሳይጀምሩት ያልቃል*

*የዚህ ግጥም አጠቃላይ መልእክት ሰዎች ከሚወዱት ሰው ጋር ጸንተው አይዘልቁም የሚል ነው፡፡*

2. አንጎራጉራለሁ የደላኝ መስዬ
   ለሊቱ እንዲነጋ ቀኑ እንዲመሽ ብዬ

3. እህህ ነው እንጂ ያከሳው ደረቴን
   መች ሳልበላ አድራለሁ እንጀራ እራቴን

**ክፍለጊዜ ስምንት**

### ተግባር ሶስት

በመጀመሪያ በቡድን ሆናችሁ የስራ፣ የክብረበአል፣ የፍቅር ሶስት ሶስት ቃላዊ ግጥሞች ሰብስቡ፡፡ በመቀጠልም የአከባቢያችሁን ሰዎች ለምን አላማ እንደሚውሉ ጠይቁ፡፡ በመጨረሻም በጽሁፍ አደራጅታችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡

**ክፍለጊዜ ዘጠኝ**

## ትምህርት አምስት፡ ቃላት

**የሚከተለው ማስታወሻና ጥያቄዎች የቃላት እውቀታችሁን ለመጠቀም የሚያግዙ ናቸው፡፡ ለጥያቄዎቹም ተገቢውን መልስ በጽሁፍ ስጡ፡፡**

### ማስታወሻ

**ዘይቤያዊ አነጋገር**

ዘይቤ አንድን ሀሳብ፣ ድርጊት ወይም ሁነት፤ የአንድን ነገር ቅርጽ ወይም ሁኔታ እንዲሁም የሰውን ባህሪ ስሜትና መልክ አጉልቶና አድምቆ ለተመልካቹም ሆነ ለሰሚው ምናባዊ ፍስህ በመስጠት የሚያቀርብ የአነጋገር ስልት ነው፡፡ የዘይቤ አይነቶች ብዙ ቢሆኑም በስፋት አገልግሎት ላይ ውለው ከምናያቸው አነጻጻሪ፣ ተለዋጭ፣ ሰውኛ

ዘይቤዎችን መጥቀስ ይቻላል፡፡

1. **አነጻጻሪ ዘይቤ፡** ይህ ሁለት ነገሮችን፣ ባህሪዎችን፣ ድርጊቶችን በመውሰድ በማነጻጸር ወይም በማወዳደር የሚፈጠር ዘይቤ ነው፡፡ ለማነጻጸርም እንደ፣ ይመስላል፣ ትመስላለች ወዘተ ቃላትን ይወስዳል፡፡

   **ምሳሌ፡** ኤልያስ እንደህጻን አለቀሰ፡፡

2. **ተለዋጭ ዘይቤ፡** ተለዋጭ ዘይቤ የአንዱን ባህሪ ለሌላ በመስጠት የሚፈጠር የዘይቤ አይነት ነው፡፡

   **ምሳሌ፡** ረሂማ ጸሀይ ነች፡፡

3. **ሰውኛ ዘይቤ፡** የሰውን ልዩ ልዩ ባህሪያት፣ድርጊትና ችሎታ ሰው ላልሆኑ ለእንስሳት፣ለተክሎችና ለግኡዛን በመስጠት የሚፈጠረው ዘይቤ ሰውኛ ዘይቤ ይባላል፡፡

   **ምሳሌ፡**ዝናቡ ከኔ ቂም ያለው ይመስል አሯሩጦ ደበደበኝ፡፡

**ክፍለጊዜ አስር**

**መልመጃ አምስት**

**ሀ. የሚከተሉት ዓረፍተነገሮች በየትኛው የዘይቤ አይነት እንደቀረቡ መልስ ስጡ፡፡**

1. ቦና እንደነብር ይዘላል፡፡
2. ከማል አንበሳ ነው፡፡
3. የጓደኛዬ ፊት እንደጸሀይ ያበራል፡፡
4. ሰማዩ አለቀሰ፡፡
5. እሱ እንደጅብ ይጮሃል፡፡
6. ጠጣዋ ከት ብላ ሳቀችብኝ፡፡
7. ጫላ በግ ነው፡፡

8. አይናለም እናቷን ትመስላለች፡፡
9. እሱ ማር ነው፡፡
10. ጨለማው ጥርሱን አገጠጠ፡፡

**ለ. ለአነጻጸሪ፣ ተለዋጭና ሰውኛ ዘይቤዎች ምሳሌ ሊሆኑ የሚችሉ ሁለት ሁለት አረፍተ ነገሮችን ጻፉ፡፡**

**ክፍለጊዜ አስራ አንድ**

## ትምህርት ስድስት፡ ሰዋስው

**የሚከተለው ማስታወሻና ጥያቄዎች የሰዋሰው እውቀታችሁን እንድትጠቀሙበት የቀረቡ ናቸው፡፡ ለጥያቄዎቹ ተገቢውን መልስ ስጡ፡፡**

### ማስታወሻ

**አያያዥ ቃላትን ተጠቅሞ ድርብ አረፍተነገር መመስረት**

ድርብ ዓረፍተነገሮችን በመመስረት ሂደት አያያገሮች ከፍተኛ ሚና አላቸው። የአያያገሮች አገባብ በአረፍተነገሮቹ ሃሳብ የሚወሰን በመሆኑ ተገቢውን አያያዥ በማጣመር ለመጠቀም በነጠላ አረፍተነገሮቹ የተገለፀውን ሃሳብ መረዳት ያስፈልጋል።

**ምሳሌ፡** የሂሳብ ትምህርት መማር እወዳለሁ።
ጥሩ ውጤት አላመጣሁም።

የሂሳብ ትምህርት እወዳለሁ <u>ይሁን እንጂ</u> ጥሩ ውጤት አላመጣሁም።

በምሳሌው መሰረት "ይሁን እንጂ" የሚለው አያያዥ ሁለቱን ነጠላ ዓረፍተነገሮች በማያያዝ ድርብ ዓረፍተነገር ለመመስረት አስችሏል። በተጨማሪም፣ ነገር ግን፣ ቢሆንም፣ ዳሩግን ወዘተ በውጤት የሚቃረኑ ሀሳቦችን ያጣምራሉ።
በሌላ በኩል ደግሞ ስለዚህ፣ ስለሆነም፣ የመሳሰሉት ወዘተ ግን በውጤት የሚዛመዱ ሀሳቦችን ያጣምራሉ።

## መልመጃ ስድስት

**ከዚህ በታች የቀረቡትን አያያዥ ቃላት በተገቢው ቦታቸው በማስገባት ድርብ አረፍተነገር መስርቱ፡፡**

ስለዚህ ምክንያቱም

ነገር ግን ለዚህም ቢሆንም

1. ሀ. በርትቶ ያጠናል፡፡
   ለ. አንደኛ ይወጣል፡፡
2. ሀ. ጨለማን ትፈራለች፡፡
   ለ. አውሬ አስደንግጧት ያውቃል፡፡
3. ሀ. ነብሰጡሮች ይመጣሉ፡፡
   ለ. ማዋለጃ ክፍሉን እናዘጋጅላቸው፡፡

## መልመጃ ሰባት

**ክፍለጊዜ አስራ ሁለት**

**ሀ. ሰንጠረዡ ውስጥ የቀረቡ መረጃዎችን በመጠቀም የተለያዩ ድርብ ዓረፍተነገሮችን መሥርቱ።**

ምሳሌ፡ ቁርስ አልበላሁም <u>ቢሆንም</u> የርሃብ ስሜት አልተሰማኝም፡፡

| ነጠላ ዓረፍተነገር | አያያዥ | ነጠላ ዓረፍተነገር |
|---|---|---|
| ቦርሳዬን አስቀመጥኩ | ይሁን እንጂ | ብዙ ማዳመጥ እችላለሁ። |
| ቁርስ አልበላሁም። | እና | እኔን አታገኙኝም። |
| ወደ ሩቅ ቦታ እሄዳለሁ። | ስለዚህ | እሱ አይወደኝም። |
| ብዙ መናገር አልወድም። | ግን | የረሃብ ስሜት አልተሰማኝም። |
| በሥራ ቦታዬ ላይ አልነበርኩም። | ስለሆነም | ዘገባ ማንበብ ጀመርኩ። |
| ታታሪነቴን አልጠላውም። | ቢሆንም | እንደሥራዬ ውጤታማ አይደለሁም፡ |
| እሱን እወደዋለሁ። | ነገርግን | ኳስ መጫወት ጀመርኩ። |
| የክፍል ጓደኞቼን እወዳቸዋለሁ። | ወይም | እነርሱን በየቀኑ ማየት ያስደስተኛል። |

| ቃል | ፍች |
|---|---|
| ሀይቅ | በአንድ ቦታ የረጋ/ የማይንቀሳቀስ/ ውሃ |
| ተፈጥሮ | ሰውሰራሽ ያልሆነ |
| የተጋረጠባቸው | እንቅፋት የሆነባቸው |
| መመከት | መከላከል |
| ጫና | ተጽዕኖ |
| ማራኪ | መስህብ፣ አስደሳች |
| ሱስ | ልማድ |
| ብሄራዊ | አገር አቀፍ |
| ፓርክ | ተክልሎ የሚገኝ የዱር አራዊቶች መኖሪያ ቦታ |
| ኮረብታ | ተራራ፣ ከፍ ያለ ቦታ |
| አምሳል | ምትክ፣ ተመሳሳይ |
| ገጽታ | መልክ |
| አንጋፋ | ቀዳሚ |
| ሙዳይ | ትንሽ አገልግል |
| አርቲስት | የኪነጥበብ ባለሙያ |
| እያጎናጸፈ | እያላበሰ፣እየሰጠ |
| ስልጣን | ሹመት |
| አርሶ አደር | በእርሻ ስራ የሚተዳደር |
| መዋዕለህጻናት | የልጆች መዋያ |
| ደቦ | በጋራ ስራን መተጋገዝ፣ ወንፈል |
| ጠጠር | ትንሽ ድንጋይ |
| ሲሰደዱ | ጥለው ሲሄዱ |
| በአፋጣኝ | በአስቸኳይ |
| እንዲስፋፋ | እንዲዛመት |
| መድልዎ | ማግለል፣መለየት፣ማበላለጥ |
| ተጨባጭ | በመረጃ የተደገፈ እውነታ |